# የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተንሣሶት ስልት አተገባበር ጥናት

## (በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድኅረምረቃ መርሀግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ክፍል

ለወየሁ አየለ

አማርኛን በማስተማር ሥነ-ዘዴ (TEAM) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ
ትምህርት ክፍል

ሐምሌ/2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድኅረምረቃ መርሀግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል

# የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተነሣሶት ስልት አተገባበር ጥናት

(በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት)

ለወዩሁ አየለ

ሐምሌ/2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የድኅረምረቃ መርሀግብር

# የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተነሣሶት ስልት አተገባበር ጥናት

## (በመንግሥትና በግልትምህርት ቤቶች ናሙናነት)

በ

ለወየሁ አየለ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

| | |
|---|---|
| ______________ | ______________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

በቅድሚያ "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሙበት የተነሳሶት ሥልት አተገባበር ፍተሻ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት" በሚል ርዕስ ጥናት እንዳካሂድ እድሉን ሰጥቶ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠልም ጥናታዊ ጽሁፌን በመከታተልና አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማማከር እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶክተር አረጋ ኀይለሚካኤል ምስጋና አቀርባለሁ። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ መካሄድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ (የቀለም) ጽሁፎችን በማንበብ፣ አስፈላጊ የሆኑ የጽህፈት ስራዎችን በመቅረጸ-ድምጽ በመመዝገብ፣ በብሬል ያዘጋጀሁትን ጽሁፍ ወደ ቀለም የእጅ ጽሁፍ በመገልበጥ ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን መስዕዋት በማድረግ እገዛ ላደረጉልኝ ወ/ሪት ገነት ዘውዱ፣ ወሪ/ት ራምዚያ ይማም፣ ወ/ት አብስራ መንግስቱ ፣ወሪ/ት ሚሚሸት አሸነፍ እንዲሁም በኮምፒዩተር ጹሁፍ እገዛ ላደረጉልኝ ወ/ሪት ጽዮን ዋሲልኝ እና ወ/ሪት ገሊላ ተስፋዬ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በተጨማሪም ጥናቱን አስተማማኝና ስኬታማ ለማድረግ በተደረገው መረጃዎችን የማሰባሰብ ሂደት መረጃዎችን በማቀበል፣ በክፍል ምልከታው ተሳታፊዎች በመሆን ቀና ትብብራቸው ላልተለየኝ በአዳማ ልዩ ዞን ለሚገኙት ለአዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ ቤት ለሆሊኢንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለአዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለአዳማ ጸሀይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን፣ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ለረዳት ተመልካቾች የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። በዚህ ሁሉ የስራ ሒደት በሀሳብና በጸሎት ከእኔ ጋር ለነበሩ ለወሪ/ት ፍቅርተ መኮንንና ለአቶ ግሩም ሶሪ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። ከሁሉም በላይ ግን እቅድና አላማውን የፈጸመ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ Vi
አህጽሮተ ጥናት ........ Viii
ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አላማ ........ 3
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4
1.4. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.5. በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች ........ 5
1.6 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት መፍቻ ........ 5
ምዕራፍ ሁለት፣ የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት
2.1 የተነሳሶት ምንነት ........ 7
2.2. የተነሳሶት አስፈላጊነት ........ 8
2.3. የተነሳሶት አይነቶች ........ 9
2.3.1. ውስጣዊ ተነሳሶት ........ 10
2.3.2. ውጫዊ ተነሳሶት ........ 11
2.4 ተነሳሶት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና ........ 13
2.5. የተነሳሶት ተላውጦዎች ........ 15
2.5.1. ማኅበረሰቡ ለቋንቋ ያለው አመለካከት ........ 15
2.5.2. ወላጆች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና ያላቸው አመለካከት ........ 16
2.5.3. ቢጤዎች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና አመለካከት ........ 16
2.5.4. የቋንቋ መምህር ........ 16
2.5.5. የማስተማሪያ ዘዴ ........ 17
2.5.6. የቋንቋ ትምህርቱ ትግበራዎች ........ 17
2.6. የተነሳሶት ብልሃቶችን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት

ክፍል ውስጥ ስለ መጠቀም ........................................................ 18
2.6.1. መሰረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን መፍጠር ........................ 19
2.6.1.1. ትክክለኛ የመምህር ባሕርይና ጥሩ
የመምህር ተማሪ ግንኙነት ........................................ 19
2.6.1.2. አስደሳችና አጋዥ የክፍል ውስጥ ሁኔታ .............. 21
2.6.1.3. ጥሩ የቡድን ሥነ-ሥርዓትን የያዘ የተማሪ
ቡድን ጥምርታ ........................................................ 21
2.6.2. ተፈላጊውን ተነሳሶት ማንቀሳቀስ ................................... 23
2.6.2.1 ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን
መልካም አመለካከት ማሳደግ ........................... 23
2.6.2.2. ውጤት የመጠበቅ ተስፋን መጨመር ................ 25
2.6.2.3. አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መርጃ
መሳሪያዎችን ማዘጋጀት .................................... 26
2.6.2.4 የተማሪዎች ፍላጐት እንዲጨምር ማድረግ ........... 27
2.6.2.5. የተማሪዎችን የዓላማ አፈፃፀም ማሳደግ ................ 27
2.6.3. የተማሪዎችን ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ ..................... 28
2.6.3.1. ተማሪዎች ያላቸውን ለራስ የተለየ ግምት መስጠት
በመንከባከብ በራስ የመተማመን ብቃት ማሳደግ . 29
2.6.3.2. በራስ መማር ................................................. 30
2.6.3.3. የተማሪዎችን እርካታ መጨመር ........................ 31
2.6.3.4. የትምህርት ትግበራዎችን በተነሳሶታዊ መንገድ
ማቅረብ .................................................................. 32
2.6.3.4.1. ትምህርቱን አነቃቂና አስደሳች ማድረግ .. 33
2.6.3.4.2. የሚያነቃቁ ምጋቤ-ምላሽና ሽልማትን
መስጠት ................................................ 34
2.7. ቀደምት ሥራዎች ........................................................................ 35

ምዕራፍ አምስት፣ማጠቃለያ አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ ........ 75

5.2 አስተያየት ........ 80

**ዋቢ ጽሑፎች ........ 81**

**አባሪ ሀ ........ 86**

**አባሪ ለ ........ 91**

**አባሪ ሐ ........ 96**

**አባሪ መ ........ 99**

ምዕራፍ ሶስት፣የአጠናን ዘዴ

3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................ 38
3.1.1.የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ ........................................ 38
3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........................................ 38
3.1.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........................................ 39
3.1.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........................................ 39
3.1.5. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................................ 39
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................ 40
3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........................................ 40
3.2.2. የፅሑፍ መጠይቅ ........................................ 41
3.2.3. ቃለ መጠይቅ ........................................ 41
3.3. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ........................................ 42
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................ 43

ምዕራፍ አራት፣ የመረጃዎች ትንተናና ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች

4.1 የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫና የመማሪያ ክፍሉ አደረጃጀት ........................................ 44
4.2 መምህሩ የሚጠቀምባቸው የተነሳሽነት ሥልቶችና አተገባበር በሚመለከት የቀረረበ ትንተና ........................................ 48
4.2.1 መልካም የሆነ የመምህር - ተማሪ ግንኙነት መፍጠር ........................................ 49
4.2.2. የመማሪያ ክፍሉን አስደሳችና አጋዥ ስለማድረግ በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 52
4.2.3 ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 56
4.2.4 የመረጃ መሣሪያዎችን መጠቀም በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 59
4.2.5 የትምህርቱን ይዘት ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 60
4.3 የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሶትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 63
4.4 በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ተላውጦዎች በሚመለከት የቀረበ ትንተና ........................................ 70
4.5 ከጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ አስተያየቶች ........................................ 72

ከመዩወ

## ጠረኘር ማውጫ

ገጽ

ሪዎች ዳራዊ መግለጫ ..........................44

ትና ክፍያ በሚመለከት የቀረበ መግለጫ. 46

ረጃጀት.............................................. 47

ከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች...... 48

ሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች 49

ሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኙ ምላሾች.............................................. 50

7፣ አስደሳች የመማሪያ ክፍል ሁኔታን መፍጠር በሚመለከት ከክፍል
ምልከታው የተገኙ ምላሾች.............................................. 52

8፣ በቡድንና በጥንድ መደራጀትን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው
የተገኙ ምላሾች.............................................. 52

9፣ ተማሪ ተኮር እና መምህር-መር ዘዴን መጠቀም ማድረግ በሚመለከት ከክፍል
ምልለታው የተገኙ ምላሾች.............................................. 54

10፣ ተማሪዎችን በተናጥል የማሳተፍ ተግባርን በሚመለከት ከክፍል
ምልከታው የተገኙ ምላሾች.............................................. 55

11፣ ለተማሪዎች የተሰጡ ምጋቤ ምጋቤ ምላሾችን በሚመለከት
ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች.............................................. 57

12፣ የመምህሩ የትምህርት መርጃ መማሪያ አጠቃቀም በሚመለከት ከክፍል
ምልከታው የተገኙ ምላሾች.............................................. 59

13፣ የትምህርቱን አላማ ማሳወቅ በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ
የተገኘ ምላሾች.............................................. 61

14፣ ስለትምህርቱ ይዘት ሳቢነት በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ
የተገኙ ምላሾች ..............................................62

15፣ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሑፍ መተይቆ
የተገኙ ምላሾች..............................................63

16፣ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ተነሳሽነት በሚመለከት ከክፍል
ምልከታው የተገኙ ምላሾች..............................................65

17፣ ተማሪዎች ለመማር ያላቸውን ፈቃደኝነት በሚመለከት ከክፍል

ምልከታው የተገኙ ምላሾች......................................................................66
18፤ የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ብቃት በሚመለከት ከክፍል
ምልከታ የተገኙ ምላሾች......................................................................68
19፡ ቢጤዎች ወላጆችና ማህበረሰቡ ያላቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት ከጽሑፍ
መጠይቁ የተገኙ ምላሾች......................................................................70

# አህጽሮተ ጥናት (Abstract)


የዚህ ጥናት ዋና አላማ በመንግሥትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቋንቋ ትምህርቱ የተነቃቁ ለማድረግ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተነሳሶት ስልት አተገባበር ምን እንደሚመስል ማጥናት ነበር:: ይህንንም ለመተግበር ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ከተነሱ በኋላ ጥናቱን ለማካሄድ ናሙናዎች ተወስደዋል:: በዚህ መሠረት በኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት ሥር በአዳማ ልዩ ዞን ውስጥ የሚገኙ አንድ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ሦስት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተወስደዋል:: የክፍል ምልከታ በማካሄድ፣ ሁለት መቶ ሰባ የናሙና ተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላትና ለስድስት መምህራን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቦአል:: መረጃዎቹም ከተሰበሰቡ በኋላ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተነሳሶት ስልትን በምን አይነት ሁኔታ በመተግበር ላይ እንዳሉ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ አማካኝነት በንፅፅር ተተንትነዋል:: የተሰበሰቡትም መረጃዎች የሚከተሉትን ውጠ ቶች አስገኝተዋል::

በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አጥጋቢ የሆነ የመምህር ተማሪ ግንኙነት ባለመፍጠ ራቸው፣ ትምህርቱን አዝናኝና አስደሳች አድርገው ባለማቅረባቸው፣ ከአወንታዊ ምጋቤ-ምላሽ ጐን ለጐን አሉታዊ ምጋቤ-ምላሾችን በመጠቀማቸው ተማሪዎቻቸውን የተነቃቁና ተነሳሶት ያላቸው በማድረግ ደረጃ በግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ያነሱ ሆነው ተገኝተዋል:: ተማሪዎቹም ያላቸው ተነሳሶት ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጦአል:: ከዚህም ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል::

በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጠር ወደ ሀምሳ ዝቅ ቢል፣ መምህራን ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ፣ ትምህርቱን አዝናኝና አስደሳች ማድረግ፣ ከአሉታዊ ምጋቤ-ምላሾች ይልቅ አዎንታዊ ምጋቤ-ምላሾችን መስጠት፣ በተነሳሽነት ለሚያስተምሩ መምህራን ማበረታቻ መስጠት የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦችን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል::

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ መምህሩና ተማሪው ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሶት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ይህም ተነሳሶት የሰዎችን ፍላጐት፣ ስሜት፣ ጉጉት. የሚያንፀባርቅ ፤ ከውስጣዊ ወይም ከውጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካከትን፣ አዎንታዊ ምላሽን፣ ጥሩ ውጤትን የሚያስገኝ፣ አንድ ድርጊት እንዲፈፀም የማበረታታት ሂደት ነው (Gardner 1985 ፣ 10 ፤ Brown 1987፣115፤ Harmer 2001 ፣ 52፤ Dornyei 2001፣8)። በመሆኑም ተማሪው አንድ አቅጣጫ ይዞ በመንገዱ ወደ አንድ ግብ እንዲደርስ የሚያደርግ ጊዜያዊና ቀጣይነት ያለው የማነቃቂያ መንግድ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ተማሪው የግል ፍላጐቱንና ምርጫውን እንዲያስተካክል፣ ምርጫውንም በሚተገብረው ስራ ማጠናከር እንዲችል፣ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። ከዚህም የተነሳ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሶነት አስፈላጊ ጉዳይ ይሆናል (Harmer 1991፣ 3፤ William and Burden 1997 ፣120)።

ሰዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ የሁለተኛ ቋንቋን ይለምዳሉ፤ ይማራሉ። ይህም የሚሆነው ግለሰቡ በአካባቢው ከሚገኘው ማህበረሰብ ጋር በሚያደርገው ተራክቦ የተነሳ ለሁለተኛ ቋንቋው ሲጋለጥና በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ ቋንቋውን ሲማር ነው። ቋንቋውን መማር ሲባል ግለሰቡ በንቃ አእምሮ በመሆን በቋንቋው ቅርፅ ላይ በማተኮር፣ በማጻመጥ፣ በማንበብ፣ ስህተቶቹን ለይቶ በማውጣት ፣ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ፣ የዕሁፍ ውጤቱን የበለጠ የሰላ ለማድረግ የሚካሄድ ሂደት ነው (Alatis 1981 ፣ 98 ፣ Stern 1983 ፣ 18፤ ተስፋዬ 1981 ፣ 19)።

ሁለተኛ ቋንቋን መማር ከማህበራዊ ተግባቦት አንፃር ሲታይ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ከመማር ይለያል። ይህም ሲባል የግለሰቡን ማህበራዊ ማንነት፣ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያለውን ተግባቦት በማመልከትና አመለካከቱን በማስተካከል ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና ማህበራዊ ባህሪ ጋር እራሱን የሚያስማማበት ሂደት ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ፣ ግለሰቡ ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሶት ሲኖረው ነው (Littlewood 1981 ፣7)።

በሀገራችን ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋዎችን እንደ አንድ የትምህርት አይነት በትምህርት ቤት ውስጥ ይማራሉ። ከነዚህም መካከል አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ነው። አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ባልሆነባቸው አካባቢዎች በትምህርትነት ይሰጣል። የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (1986፣13) እንደገለፀው፣ የአማርኛ ቋንቋ በአንደንድ ክልሎች ከ3ተኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርትነት እንዲሰጥ ሲወሰን ፤ በኦሮምያ ክልል ደግሞ ከ5ተኛ ክፍል ጀምሮ እንደአንድ የትምህርት አይነት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋው ስኬታማ እንዲሆን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በታላሚው ቋንቋ ሊያዳብር ይገባል። ይህ እንዲሆንና ተማሪው በሙሉ ፈቃደኝነት ቋንቋውን እንዲማር ተነሳሶት እንዲኖረው ያስፈልጋል። ሰለሞን (1995፣21) እንደገለፁት ባለፉት፣ በርካታ አመታት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መፃህፍት አልነበሩም። በመሆኑም ከሚማሩበት ቋንቋ ውስጣዊ ባህሪ እስከ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት፣ ከክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ዘዴዎች እስከ አመለካከት ድረስ በርካታ ችግሮች ሲያጋጥሙ ቆይተዋል። ሙሁሩ እንዳብራሩት የሁለተኛ ቋንቋውን የማስተማር አላማ ታውቆ ተማሪዎች ጥሩ ተነሳሶት እንዲኖራቸው የሚያደርግና በትምህርቱ አሰጣጥ ተማርከው ተነሳሶት እንዲያድርባቸው የሚያደርግ ጥረት አልተደረገም።

ስለሆነም የዚህ ጥናት አቅራቢ ጥናቱን ለማካሄድ መነሻ የሆኗት ምክንያቶች፡-

- አጥኝዋ ከዚህ በፊት ለሴሚናር ኮርስ ማሟያ ባካሄደችው የሙከራ ጥናት አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በኦሮሚያ ክልል በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሶት ዝቅተኛ ሆኖ በማግኘቷ፥ እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑም የተማሪዎችን ተነሳሶት ከፍ ለማድረግ በክፍል ውስጥ የሚተገብሯቸው የማነቃቂያ ስልቶች አጥጋቢ ባለመሆናቸው፣
- ከዚህ በፊት ይህንን ርዕሰ-ጉዳይ በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የተሰራ ጥናት አለማግኘትዋ፣ የሚሉት ናቸው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ጥናቱን ለማካሄድ መሠረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች ሆነው ቀርበዋል።

1. በፍተሻው ሂደት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ተነሣሶት እንዲኖራቸውና ያላቸውንም ተነሣሶት እንዲያጎለብቱ ምን አይነት ስልቶችን ይጠቀማሉ? በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን ?
2. የተማሪዎችን ተነሣሶት ሊያዳክሙ የሚችሉ ስልቶች የትኞቹ ናቸው?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ስለተማሪዎቻቸው ውስጣዊ ተነሣሶት ምን አስተያየት አላቸው? የተማሪዎቹ ውስጣዊ ተነሣሶትስ በምን ይገለፃል ? እነዚህንና በእነዚህ ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎችን ጥናቱ ለመመለስ ይሞክራል።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ በመንግስትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቋንቋ ትምህርቱ ተማሪዎችን የተነቃቁ ለማድረግ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተነሳሶት ስልት አተገባበር ምን እንደሚመስል ማጥናት ነው። ከዚህ አጠቃላይ ግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ዝርዝር አላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1. መምህራን መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪን ግንኙነት በክፍል ውስጥ መፍጠር መቻል አለመቻላቸውን መመርመር፤
2. መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ተስተምህሮት ወቅት የተማሪዎችን ተነሳሶት የሚቀሰቅሱ ቃላዊ ማበረታቻዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ማረጋገጥ፤
3. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን ተነሳሶት በቢጤና በቡድን ተሳትፎ ማጉልበት መቻል አለመቻላቸውን ማረጋገጥ፤
4. የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የተማሪዎችን ተነሳሶት የሚያዳክሙ አሉታዊ ምላሾች መስጠት አለመስጠታቸውን መመርመር፤
5. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት (ውስጣዊ)ተነሳሶት ያላቸው መሆኑንና አለመሆኑን ማረጋገጥ፤
6. የቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የተነሳሶት ስልትን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መመርመር ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ስኬታማ የመሆንም ሆነ ስኬታማ ያለመሆን ጉዳይ የሚፈጠረው ተማሪው ለቋንቋ ትምህርቱ በሚኖረው ወይም በሚያጣው ተነሳሶት አማካኝነት መሆኑን Brown (1987) ፣ Dornyei (2001) ፣ Noels, et al (2003) ገልፀዋል:: በመሆኑም ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡

- ተጠኚ በሆኑት የመንግስትና የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር–ማስተማር ሂደቱ ስለሚጠቀሙበት የተነሳሶት ስልት አተገባበር በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡና ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲያዩ ለማስቻል፡
- ስለ ተነሳሶት ለማወቅ ለሚሹ መምህራን መጠነኛ ግንዛቤ ይሠጣል፡
- የቋንቋ መምህራን ተነሳሶትን ሲተገብሩ ለሚያጋጥማቸው ችግሮች የመፍትሂ ሀሳብን ለመጠቆም አስተዋፅኦ ያበረክታል፡
- ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎችን ተነሳሶት የሚያዳክሙ ሁኔታዎችና ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ለቋንቋ መምህራን ፍንጭ ይሰጣል፡
- አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ለተነሳሶት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው የመማር ማስተማሩን ተግባር ሁኔታ እንዲያከናውኑ ያግዛል፡
- ወደፊት በዚህ ርዕስ-ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ማካሄድ ለሚሹ አጥኚዎች መነሻ ሀሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

ባጠቃላይ ይህ ጥናት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ተነሳሶትን እንደ አንድ የማስተማሪያ ስልት በመቁጠር በቂ ግንዛቤን ጨብጠው ለራሳቸው እና ለተማሪዎቻቸው ተነሳሶትን በማጉልበት ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር አተገባበርን እንዲፈፁሙ አስተዋፅኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል::

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በርካታ የመንግስትና የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ ይህ ጥናት እነዚህን ትምህርት ቤቶች በሙሉ የሚያካትት አይደለም:: በመሆኑም ትኩረቱን ያደረገው በአዳማ ልዩ ዞን፣ በአዳማ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት (የመንግሥት)፣ በሆሊኤንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የግል)፣ በአዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የግል) እና በአዳማ ዐሐይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የግል) በ2000 ዓ.ም. በማስተማር ላይ ባሉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ ነው።

ጥናቱ በአዳማ ልዩ ዞን ሊወሰን የቻለው በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ የኦሮምያ ክልል ዞኖች መካከል አንዱ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ (ኢ.አፍ ፌት) የሆኑ ተማሪዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ ባለመሆኑ ነው።

ይህ ጥናት ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ያላቸው ተነሳሶት ምን እንደሚመስል በማሳየት እና የመምህሩ የተነሳሶት አተገባበር እንዴት እንደሆነ በመቃኘት ላይ ብቻም የተወሰነ ይሆናል። በመሆኑም ሌሎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ የሚያስፈልጉ ጉዳዮችንም ሆነ የሚያጋጥሙ ችግሮችን አያካትትም።

## 1.5. በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት ሲካሄድ በጥናቱ ተተኳሪ ሆነው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አቻ የሆነ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር ማግኘት አልተቻለም። ስለሆነም ጥናቱን አስተማማኝ ለማድረግ ተጠኚ የሆነውን የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቁጥር ከአንድ ወደ ሶስት ከፍ ማድረግ ግድ ሆኗል። ለዚህም ምክንያት ጥናቱ በአንድ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በሶስት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ሊያተኩር ችሏል። ከዚህም የተነሳ በጥናቱ ሂደት የጊዜና የገንዘብ አቅም ችግር ሊያጋጥም ችሏል።

## 1.6 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት መፍቻ

ለራስ የተለየ ግምት መስጠት____ self-esteem

ምጋቤ-ምላሽ ____ feedback

በራስ መማር____ learning autonomy

በራስ መተማመን____ self confidence

ቢጤ ____ peer

ተላውጦ____ variable

ተስተምህሮት____learning

ተራክቦ____interaction

ተግባቦት____ communication

ትውረት____theory

ተነሳሶት____motivation

አመለካከት____attitude

እሴት____value

ክንውን____ activity

ውህደታዊ ተነሳሶት____integrative motivation

ውስጣዊ ተነሳሶት____ intrinsic motivation

ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ____expectancy of success

ውጫዊ ተነሳሶት____extrinsic motivation

ዘላቂ ግብ____long term goal

የነቃ አእምሮ____ conscious mind

የክዋኔ ብቃት____performance

ጊዜያዊ ግብ____ short term goal

ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሶት ____instrumental motivation

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የቋንቋ ፣ የሥነ-ትምህርት ፣ የሥነልቦና ምሁራንና አጥኝዎች ስለተነሳሶት (Motivation) የፃፏቸው ፅሁፎች ይቃኛሉ:: በመሆኑም የተነሳሶት ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ አይነቶች፣ ተነሳሶት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና የተነሳሶት ተላውጠዎች ና የተነሳሶት አተገባበር ወዘተ ይዳሰሳሉ::

## 2.1 የተነሳሶት ምንነት

"ተነሳሶት" የረቀቀና ሰፊ ጽንሰ ሐሳብን የያዘ በመሆኑ አንድ እና ውስን የሆነ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች ነው:: ይሁን እና ምሁራን የሰጧቸውን የተለያዩ ብያኔዎች ከዚህ በታች ለማቅረብ ይሞከራል::

ተነሳሶት የሚለው ቃል 'Motivation' ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ ነው:: 'Motivation' የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ደግሞ 'Move' ከሚለው የላቲን ቃል የተገኘ መሆኑን Pintrich and Schunk (2002፣4) ይገልፃሉ:: አያይዘውም ምሁራኑ ተነሳሶትን ሲገልፁ ፤ ወደ አንድ ግብ ለመድረስ የሚቀሰቅስ፣ የሚገፋፋ፣ የሚያነሳሳና የሚመራ ውስጣዊ ስሜት ነው ብለዋል:: Wiliam and Burden (1997 ፣120) ደግሞ ተነሳሶት "በነቃ አእምሮ አንድን ድርጊት ወደመፈፀም የሚያመራ ጥረትን የሚያበረታታ አእምሮታዊና ስሜታዊ ቅስቀሳ ነው" ይላሉ::

Brown (1987 ፣114) በበኩላቸው ተነሳሶት "በሰው ልጆች ላይ የሚታይ፣ ተፈጥሯዊ የሆነ፣ አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ውስጣዊ ፍላጎት ነው" ሲሉ፤ Oxford and Young (1993) ተነሳሶትን "ሰዎች አንድን ነገር ለምን እንደሚተገብሩ፣ ተግባሩ ለምን ያህል ጊዜ እየተከናወነ እንደሚቆይና ለተግባሩ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጠ ው የሚያመለክት ከውስጥ የሚመነጭ ስሜት ነው"ይሉታል::

እንደ Dornyei (2001 ፣7) አስተሳሰብ ደግሞ፣ ተነሳሶት እንደስበት ሃይል ውስጣዊ ገፅታው ረቂቅና ውስብስብ በመሆኑ ለመተንተን አስቸጋሪ ቢሆንም ላዕላይ ገፅታውንና የሚያስከትለውን ውጤት መግለፅ ይቻላል:: የተለያዩ አላማዎችን መሠረት በማድረግ

አንድ ነገር ለምንና እንዴት እንደሚተገበር የሚያሳይ፣ የባሕሪን ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ውስጣዊ ግፊት ነው።

ተነሳሶት የሰዎችን ስሜት ወይም ፍላጐት የተነቃቃ ማድረግ የሚችል፣ መነቃቃቱንም ለተወሰነ ጊዜ የሚያቆይ ሃይል እንዳለው Harmer (2001፣ 51፣ Rosser and Nicholson (1984) ይገልፃሉ። Gardnr et al (2003 ፣173). Heckhausen (1991)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ተነሳሶት ወደ አንድ ግብ ሊያደርስ የሚችል ቀጥተኛ መስመር ነው።

Ur (1996 ፣274) የተነሳሶትን ሚና ሲያብራሩ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል። ተማሪው ለመማር በሚያደርገው ጥረት፣ ባለው ፈቃደኝነት እና የውስጥ መሻት ይገለፃል። በመሆኑም ነው Gardner (1985 ፣10) ተነሳሶት የአንድን የቋንቋ ትምህርት የተስተምህሮት ግብ ስኬታማ (ስኬት አልባ) ለማድረግ ወሳኝ የሆነ የፍላጐት ፣ የቀና አመለካከትና የጥረት ድምር ነው የሚሉት።

ባጠቃላይ ከላይ የተሰጡትን የምሁራን ብያኔዎች ስንመለከት ተነሳሶት አንድን ድርጊት ለመፈፀም የሚቀሰቅስ፣ የሚገፋፋ፣ ውስጣዊ ፍላጐት፣ ስሜት (ሀይል) ነው። ተነሳሶት ቋንቋን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ስኬታማ ለማድረግና ከታለመው ግብ ለማድረስ እንደ መነሻ የሚቆጠር መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ይህም ከውስጥ በሚደረገው ግፊትና ተማሪው በሚያደርገው ጥረት ይገለፃል። በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋን ለሚማሩም ሆነ ለሚያስተምሩ ተማሪዎችና መምህራን አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል።

## 2.2. የተነሳሶት አስፈላጊነት

ሁለተኛ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ ተነሳሶት ወሳኝና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። Vanlier (1988) እንደገለፁት ተነሳሽነት በሌለበት ሁኔታ ተማሪዎች ከረጅም ግብ መድረስ ስለማይችሉ የተነሳሶት መኖር ወሳኝ ይሆናል።

Cunningsworth (1984፣ 59-60) ደግሞ የተነሳሶትን አስፈላጊነት እንደሚከተለው አብራርተውታል። በተደጋጋሚ እንደተረጋገጠው አንድን ተማሪ ካለመው ግብ የሚያደርሰው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቁ ችሎታ ያለው መምህር መኖር አለመኖር፣ መሠረታዊና ጥሩ የሆኑ የመረጃ መሳሪያዎችና የመማሪያ መፃህፍት ተሟልተው

መቅረብ አለመቅረብ ብቻ ሳይሆን ተማሪው ያለው የግል ተነሳሶት ነው:: Keller (1983) ይህንን ሀሳብ ሲያብራሩ ብዙ መምህራን የማስተማሪያ መፃህፍትን የሙጥኝ ብሎ መያዝና ስርዓት የጐደላቸውን (ረባሽ) ተማሪዎችን ስርዓት ማስያዝ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደትን እንደመፍጠር ይቆጠራል ብለው ያምናሉ:: እንደነዚህ አይነት መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስነልቦናና ውስጣዊ ጉጉት መረዳት ባለመቻላቸው የተማሪዎችን ተነሳሶት እንዲፈጠር ማድረግ አይችሉም:: ስለዚህ ተማሪዎቹ ስኬታማ የመሆን እድላቸው እጅግ አነስተኛ ይሆናል::

Bill (2000፣314) በመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚገኘው የባህሪ ለውጥ በተነሳሶት አማካኝነት እንደሆነ ይገልፃሉ:: የቋንቋን ትምህርት በተነሳሶት የሚማር ተማሪ በተማረው ትምህርት ዙሪያ ግንዛቤን፣ ትውስታንና አእምሯዊ እድገትን ያገኛል:: ይህም ሊሆን የሚችለው Harmer (2001፣ 52) እና Noels (2003፣ 38) እንደገለፁት ተነሳሶት ያለው ተማሪ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ስለሚኖረው፤ አንድን ድርጊት ለመፈፀም ይደፋፈራል፤ አእምሯዊ፣ መንፈሳዊና አካላዊ ጥረት ያደርጋል፤ ከዚህም የተነሳ ካለመው ግብ ይደርሳል:: ባጠቃላይ የቋንቋን ትምህርት ለመማር ተነሳሶት እንደ አንድ መሳሪያ የሚቆጠር፣ ለተማሪው እጅግ አስፈላጊ የሆነ መሰረታዊ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል::

## 2.3. የተነሳሶት ዓይነቶች

Brown (1987፣115)፣Harmer (1991 ፣ 3)፣Ur(1996 ፣275) እናNoels(2003 ፣ 38) እንደገለጹት ተነሳሶትን "ውጪያዊና ውስጣዊ" በማለት በሁለት ከፍለዋቸዋል:: እንደምሁራኑ ሃሳብ፣ ውስጣዊ ተነሳሶት የሚባለው ከግለሰቡ ግላዊ ፍላጐት የሚመነጭ ሲሆን ውጪያዊ ተነሳሶት ደግሞ በሌሎች አካላት አማካኝነት ከሚደረጉ ግፊቶች የተነሳ የሚፈጠር ነው:: Harmer (1991) እና Ur (1996) ውስጣዊ ተነሳሶት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያዩዋቸው ሁኔታዎች የሚመነጭ ሲሆን ውጪያዊ ተነሳሶት ግን የቋንቋ ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍሉ ውጪ በሚያጋጥሟቸው ተፅዕኖዎች አማካኝነት የሚመጣ ነው ይላሉ:: እነዚህ የተነሳሶት አይነቶች በውስጣዊ ግፊትና በውጪያዊ ግፊት አማካኝነት ትምህርታቸውን የሚማሩ ሁለት አይነት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንደሚኖሩ እንድንገነዘብ ያደርጋሉ:: እነዚህን የተነሳሶት ዓይነቶች በዝርዝር ከዚህ በታች ለማየት ይሞከራል::

### 2.3.1. ውስጣዊ ተነሳሶት

ውስጣዊ ተነሳሶት ከሰው ልጅ ውሳኔ ስሜት የሚመነጭ ተግባር መሆኑን ምሁራን ይስማማሉ:: Pintrich and Schunk (2002፣ 255) ፣ Deci (1980፣20)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት፣ ውስጣዊ ተነሳሶት የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር በተላመደ መልኩ በራሱ መወሰን የሚያስችል ሰብአዊ ፍላጐት ነው:: ፍላጐቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ውስጣዊ ሃይሉን በመጠቀም ፍላጐቱን የሚያረካበት ፣ በፍላጐቱ መካከል ያሉትን ውጥረቶች የሚያረግብበት ፣ እንዲሁም ፍላጐቱን ይዞ የሚያቆይበት ነው::

ውስጣዊ ተነሳሶት በተማሪዎች ውስጥ ለሚኖረው ፍላጐት ምላሽ የሚሰጥበት ተላውጠ ነው:: ይህም ተማሪዎች ለመማር ባላቸው ጉጉት፣ ለማወቅ ባላቸው ፍላጐትና በታላሚው ቋንቋ ብቁ ለመሆን በሚያሳዩት ስሜት ጐልቶ እንደሚታይ ቴዎድሮስ (2005፣ 20) Burden (2000)ን ጠቅሰው አብራርተዋል:: ስለዚህም ተነሳሶት አንድን ነገር ለመፈጸም የሚገፋፋ ክስተት ሆኖ ተግባሩም የሚከናወነው ከተማሪዎች በመነጨ ውስጣዊ ፍላጐትና መሻት በመሆኑ አስደሳችና መንፈስን የሚያረካ ሊሆን ይችላል (Noels 2003 ፣38)::

የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሶት ከራሳቸው የሚመነጭ በመሆኑ መምህሩ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን እንዲማሩና እንዲከታተሉ በማንኛውም መንገድ እንዲገፋፋቸውና እንዲጐተጉታቸው አይጠበቅበትም:: ተማሪዎች ፍላጐታቸውን ለመፈፀም በማንኛውም ረገድ ያላቸው ግንዛቤ የሚገኘው ከአንድ አቅጣጫ (ከራሳቸው) ስለሚሆን መድረሻ ግቡ የተወሰነ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ተነሳሶት ከመድረሻ ግብ ጋር ቁርኝነት አለው ማለት ይቻላል:: ተማሪዎች የሚደርሱበትም ግብ እውነተኛነትና ዘላቂ ውጤት ይታይበታል:: ምክንያቱም ተማሪዎች ከውጪ ከሚያገኟቸው ተነሳሶት ይልቅ በሚያስተውሏቸው ነገሮች እና ከውስጣቸው ከሚወጣው የተነሳሶት ሂደት ላይ ስለሚሳተፉ ነው:: ስለዚህ ውስጣዊ ተነሳሶት በመማር ማስተማር ሂደት ውጤት የሚያስገኝ መሳሪያ ነው (Kost 2006፣ Elliot et al. 2005) ማለት ይቻላል::

Harmer (1991 ፣4) እንደገለጹት፣ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች የሚደረግ ውጫዊ ተነሳሶት እምብዛም ባለመታየቱ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ይታያል፤ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ውስጣዊ ተነሳሶት ያስፈልጋቸዋል:: ይህም ለቋንቋ

ትምህርቱ ስኬታማነት ስለሚያግዝ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ በሚችሉ ተላውጦዎች ማለትም በመምህሩ፣ በማስተማር ዘዴው እና ተማሪዎች በሚያገኙት ውጤት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

Noels (2003 ፣38) ፣ Deci and Ryan (1985) ፣ Valerand Etall (1997) ን በመጥቀስ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍረዋል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሶት ያላቸው ሰዎች አንድን ተግባር ለመምረጥም ሆነ ለመከወን ነጻነት አላቸው፡፡ በተጨማሪም የችሎታ ብቃታቸውን ስለሚያጎለብቱ ፈታኝ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳት እና ችግሮችን ማቃለል ይችላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ተነሳሶት በሦስት ዓይነት አቅጣጫ ይከናወናል፣

1. ዕውቀትን ለማግኘት፡- ግለሰቡ ከአዳዲስ ሐሳቦች ጋር ራሱን ለማስማማት እና ተግባሮችን ለማከናወን እንዲሁም ዕውቀቱን ለማሳደግ ሲል ውስጣዊ ተነሳሶት ይኖረዋል፡፡
2. ተግባርን ለመፈጸም፡- ግለሰቡ አንድን ነገር ለማማከር ወይም ለማከናወን እንዲሁም ውጤታማ የሆነ ግብ ላይ የመድረስ ተነሳሶት ይኖረዋል፡፡
3. ለመነቃቃት፡- ግለሰቡ አንድን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት ደስታን፣ አድናቆትን፣ እርካታን ወዘተ ... ለማግኘት ውስጣዊ ተነሳሶት ይኖረዋል፡፡

እነዚህ የውስጣዊ ተነሳሶት ሂደቶች ግለሰቡ አንድን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ ከድርጊቱ ዕውቀትን ለማግኘት፣ በተገኘው ዕውቀት ውጤታማ ለመሆን እና በውጤቱ ለመርካት የሚያግዙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ውስጣዊ ተነሳሶት ከሰው ልጅ ስሜት፣ ፍላጎት፣ አንድን ነገር የማድረግ ምኞት፣ በጉጉት ላይ ተመስርቶ በሚከናወን የተግባር ሂደት ላይ ጎልቶ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ይህም ሂደት ግለሰቡን ወደአንድ የረጅም ጊዜ ግብ ያደርሳል፡፡ ይህ ውስጣዊ ተነሳሶት በተማሪዎች ላይ ከታየ የመማር-ማስተማሩ ሂደት ስኬታማ እንዲሆን የሚያግዝ ቀና መንገድ ይሆናል፡፡

### 2.3.2. ውጫዊ ተነሳሶት

ውጫዊ ተነሳሶት የተነሳሶት አንዱ አካል ሲሆን የሚፈጠርበት መንገድ እና የሚያገኘው ግብ ከውስጣዊ ተነሳሶት የተለየ ነው፡፡ Vanlier (1988:1) «ውጫዊ ተነሳሶትን በስራ ላይ ለማዋል እንደተበደሩት በኋላም እንደሚከፍሉት ገንዘብ ይቆጠራል» ማለትም ውጫዊ ተነሳሶት ከግለሰቡ ውጪ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን የትምህርት ተግባራት ለመከወን

እና ለመማር ካለ ፍላጎት እና ጉጉት የሚመነጭ ሳይሆን በተለየ ሁኔታ ከተለያዩ አካላትና ከአንዳንድ ተጽዕኖዎች ማነቃቂያዎችን በመቀበል የሚመነጭ ነው:: እነዚህም ማነቃቂያዎች ከመምህራን፣ ከወላጆችና ከጓደኞች የሚገኙ ሽልማቶች፣ ምስጋናዎች፣ ምጋቤ-ምላሾች፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ (Brown 1987፣115 ፣Ur 1996፣ 275)::

በውጫዊ ተነሳሶት አማካኝነት የሚገኘው ግብ በውስጣዊ ተነሳሶት አማካኝነት ከሚገኘው ግብ የተለየ ነው:: ተማሪዎች ውጫዊ ተነሳሶትን ያካበቱ ከሆኑ በፈተና ጥሩ ውጤት ማግኘትን፣ ጥፋትን በመቀነስ ቅጣት ማስቀረትን የመሳሰሉትን የአጭር ጊዜ ግቦችን ያገኛሉ (Elliott et al 2005፣ 14፣ Noels 2003፣ 39)::

«የራስን እድል በራስ መወሰን» በሚለው በ Deci በ Ryan (1985) ትውረት መሰረት፣ ውጫዊ ተነሳሶት ሦስት ደረጃዎች አሉት:: እነዚህም

1. **በውጫዊ ተፅዕኖ የሚፈጠር ተነሳሶት፡-** ከግለሰብ ውጪ በሆኑ ምንጮች ላይ የተመሰረቱ ተግባራት ናቸው:: ይህም ማለት ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ሊታዩ የሚችሉ ጥቅማጥቅሞችን መሠረት ያደርጋሉ:: ይህ ዓይነቱ ለጥቅማጥቅም ሲባል የሚፈጠር ተነሳሶት Gardner and Macintyre (1993) ጥቅማዊ ተነሳሶት እንደሚባል ይገልጻሉ::

2. **ከራስ በሚመጣ ጫና የሚፈጠር ተነሳሶት፡-** ተማሪዎች አንድን ተግባር ሊያከናውኑ ሲሉ ከራሳቸው ጋር የማይጣጣሙ ግለሰባዊ ግፊቶች እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ምንም እንኳን የግፊቱ ምንጮች አስፈላጊ ቢሆኑም ተማሪዎቹ የራስን እድል በራስ የመወሰን ሁኔታ አይታይባቸውም:: ተማሪዎች ከግፊቶቹ ጋር ይጋፈጣሉ እንጂ በራሳቸው ምርጫ ላይ ተመስርተው ድርጊትን አይፈፅሙም:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲለምዱ ቋንቋውን ለመናገር ስለሚያፍሩ ቋንቋውን በቶሎ መልመድ አይችሉም:: የተማሪዎች ሙከራ ሁልጊዜ ስህተት ወይም ጥፋት እንዳይፈጽሙ ብቻ ነው::

3. **በተለየ ምክንያት የሚፈጠር ተነሳሶት፡-** የራስን እድል በራስ መወሰን የሚታይበት ነው:: ይህ ዓይነቱ ተነሳሶት ተማሪዎች የሚሞክሩት የሚሰጣቸውን ተግባር ከፍ ለማድረግ ነው:: ምክንያቱም አንድን ነገር ለማድረግ ግላዊ የሆኑ አስፈላጊ ምክንያቶችን ለመፈጸም የራሳቸው ምርጫ አላቸው:: ይህም ከግብ ለመድረስ ለሚደረገው ክንውን አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ ተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርታቸውን ለማሳደግ በቃላቸው

በመደጋገም እና በመለማመድ ቋንቋውን ያዳብራሉ (William and Burden 1997፣ 123፣ Noels 2003፣ 39)::

በአጠቃላይ በውስጣዊ ተነሳሶት እና በውጪያዊ ተነሳሶት መካከል ልዩነቶች እንደሚታዩ ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መረዳት ይቻላል:: በተጨማሪም Haywood (1971) እንደሚገልፁት ውጫዊ ተነሳሶት ምቾትን፣ ደህንነትን፣ የበላይ ሆኖ መታየትን የሚያስገኝ ሲሆን ውስጣዊ ተነሳሶት ደግሞ ኀላፊነትን፣ የፈጠራ ችሎታን፣ ሥነ-ልቦናዊ እርካታን፣ በራስ ብቁ መሆንን ያስገኛል::

ከላይ እንደተገለፀው ውስጣዊ እና ውጪያዊ ተነሳሶትን በዝርዝር ለማየት ተሞክሯል:: በዚህም መሠረት ውስጣዊ እና ውጪያዊ ተነሳሶትን እንደሚከተለው ማነፃፀር ይቻላል፤

**የውስጣዊ እና የውጪያዊ ተነሳሶት**

| ውስጣዊ ተነሳሶት | ውጪያዊ ተነሳሶት |
|---|---|
| ነሶቱ ከውስጥ ፍላጎትና ጉጉት ይመነጫል:: | በሌላ አካል ከሚቀርብ ምስጋና፣ ሽልማት ወዘተ ይመነጫል:: |
| ጅም ጊዜ ግብ ወይም ዓላማ አለው:: | የአጭር ጊዜ ግብ ወይም ዓላማ አለው:: |
| ከናወነው ጉዳይ ላይ ስኬታማ ያደርጋል:: | የሚከናወነው ጉዳይ ስኬታማነቱ እንደሚኖረው የግፊት መጠን ይለያያል:: |
| ታንና እርካታን ያስገኛል:: | ምቾትን፣ ደህንነትን ያስገኛል:: |

## 2.4 ተነሳሶት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና

ቋንቋን የመማር-ማስተማር ሂደት ከዳር ለማድረስ የቋንቋ መምህሩ፣ የተማሪዎችና የሌሎች አጋዥ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው:: Stern (1983፣18) እና Ur (1996፣276) እንደገለፁት፣ በጥንት ጊዜ የቋንቋ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በመምህሩ አማካኝነት ብቻ ነበር:: ይህ ዓይነቱ መምህር-ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአሁኑ ጊዜ በተማሪው ተሳትፎ ተተክቶ ይታያል:: ተማሪው በቀጥታ ከመምህሩ ከሚማር ይልቅ በክፍል ውስጥ ለሚያደርገው ተግባራዊ ተሳትፎ ትኩረት በመስጠት የተስተምህሮቱ ሂደት ተጋሪ ሆኗል:: በተጨማሪም ተማሪው የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ሂደት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው ተግባቦታዊ ሂደት ላይም ነው:: በመሆኑም ቋንቋን መማር ለትምህርት ዓላማ ብቻ የሚካሄድ ሳይሆን አመለካከትን ለማሻሻል፣ ማኅበራዊ

እሴቶችንና ሥርዓቶችን ለማወቅ እንዲሁም ማንነትን ለመለወጥ ሳይቀር የሚተገበር ጉዳይ ነው። ይህ የሚሆነው ግን ተማሪው ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሶት ሲኖረውና በክፍል ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው። ቴዎድሮስ(2005፣20 ) Warden and Lin (2000)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት፣ የተነቃቁና ተነሳሶት ያላቸው ተማሪዎች በቋንቋ ክንውን ላይ ሙሉ ለሙሉ ተሳትፎ ስለሚያደርጉ ተነሳሶት ከሌላቸው ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ክሂላቸውን ለማሳደግ የተሻለ እድልና አጋጣሚ አላቸው። ተነሳሶት የሌላቸው ተማሪዎች ግን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ዝቅተኛ ችሎታ ይኖራቸዋል።

በሌላ በኩል Gardener and Lambert (1972) እንደሚያመለክቱት በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል ሁለተኛ ቋንቋን መልመድ ወይም መማር ማለት ካለው ጠ ቀሜታ አንፃር ሲታይ ማኅበረሰቦችን እንደሚያገናኝ ድልድይ ይቆጠራል። በተግባቦቱም ረገድ ግለሰቡ ያለው ተነሳሶት ለሁለተኛ ቋንቋው ማደግም ሆነ ውድቀት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ተመራማሪዎች ተለምዶአዊ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ ውስጥ በግልፅ የሚታወቁ ሁለት ሞዴሎች እንዳሉ አስረድተዋል። እነሱም ውሕደታዊ ተነሳሶትና ጥቅማ-ጥቅማዊ ተነሳሶት የሚባሉ ናቸው። እነዚህን የተነሳሶት ዓይነቶች Ellis (1994፣ 75)፣Harmer (2001)፣ Gardner (1985) ፣Dornyei (2001)እና ሌሎች የሥነትምህርትና የሥነ ልቦና ባለሙያዎች በዝርዝር አብራርተዋል።

በውሕደታዊ ተነሳሶት ግለሰቡ ከኅብረተሰቡ ጋር ተግባቦት ማድረግ ሲፈልግ ወይም ግለሰቡ ከህብረተሰቡ ጋር በቋንቋው ተመሳስሎ መኖር ሲያስብ ራሱን ለቋንቋው በማጋለጥ ቋንቋውን ይለምዳል፤ ያውቃልም።

በአንፃሩ ጥቅማ-ጥቅማዊ ተነሳሶት ሲባል ግለሰቡ በታላሚው ቋንቋ አስፈላጊ ጽሑፎችን ለማንበብ፣ የሥራ እድገትና የመሳሰሉትን ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት ሲባል ቋንቋውን የሚለምድበት ሁኔታ ነው። ይህ አይነቱ ተነሳሶት በብዙዎቹ ምሁራን ዘንድ እንደ ደካማ የተነሳሶት ዓይነት ተደርጎ ይወሰዳል። ምክንያቱም የረጅም ጊዜ ውጤትንና ጥሩ ውጤት ማስገኘት ባለማስቻሉና የተማሪውን ስብዕና የመለወጥ አቅሙ ዝቅተኛ በመሆኑ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የቋንቋና የሥነ ልቦና ምሁራኑ እንዳብራሩት፣ እንዳንድ ተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብ ባህልና አኗኗር ይማርካቸውና በዚያ ማኅበረሰብ

ውስጥ መቀላቀልና በቋንቋው ብቁ ችሎታ ያላቸው መሆን ይፈልጋሉ። ይህ ዓይነቱ ፍላጐት ደግሞ ውሕደታዊ ተነሳሶትን ያስከትላል።

ባጠቃላይ ተነሳሶት ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን ለመማርና በቋንቋው ብቁ ለመሆን በሚደረግ ተራክቦና ከመማሪያ ክፍል ውጪ በሚደረግ ተግባቦታዊ ክንውን እንዲሳተፉ የሚያደርግ ኃይል ነው። ተነሳሶት ያለው ተማሪ ከቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ ጋር ውኅዶትን በመፍጠር የቋንቋው ተጠቃሚ ለመሆን ወይም ደግሞ እንደ ሥራ እድል ማግኘት፣ ሽልማት መቀበል፣ ወዘተ የመሳሰሉ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ሲል ቋንቋውን ሊማር ይችላል። በመሆኑም በማንኛውም መንገድ ቢሆን ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሶት ዋና ጉዳይ መሆኑ የማያጠራጥር ነው።

## 2.5. የተነሳሶት ተላውጠዎች

የሁለተኛ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት የቋንቋ ተነሳሶትን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ተላውጠዎች አሉ። ተላውጠዎቹ በተስተምህሮቱ ወቅት ወይም ከተስተምህሮቱ ውጪ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው። ሀብታሙ (1999)፣ Ur (1996) ፣ Harmer (2001) ፣ Petty(2004) ፣ Dornyei (2003)እና Pintrich and Schunks (2002) የተነሳሶት ተላውጠዎችን እንደሚከተለው በዝርዝር አስፍረዋቸዋል፤

### 2.5.1. ማኅበረሰቡ ለቋንቋ ያለው አመለካከት

ማኅበረሰቡ ምንም እንኳን በክፍል ውስጥ ተገኝቶ የቋንቋ ትምህርቱን ባይከታተልም በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት የራሱ የሆነ አመለካከት ይኖረዋል፤ ማኅበረሰቡ ለታላሚው ቋንቋ ምን ያህል ግምት ይሰጠዋል? ተማሪዎችስ ቋንቋውን ለመማር ምን ያህል ፍላጐት አላቸው? ለምን? የሚሉት ጥያቄዎች የኅብረተሰቡ አመለካከት ምን ዓይነት እንደሆነ ሊያንፀባርቁ ይችላሉ። ተማሪዎች ማኅበረሰቡ ለቋንቋው የሚሰጠውን አመለካከት በመያዝ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸው ተነሳሶት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል፤ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ከማኅበረሰቡ ጋር ለረጅም ግዜ አብረው የኖሩ በመሆናቸው የማኅበረሰቡ አመለካከት በእነሱ ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል (Harmer 2001፣ 52)።

### 2.5.2. ወላጆች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና ያላቸው አመለካከት

ወላጆች በቤት ውስጥ ስለታላሚው የቋንቋ ትምህርት የሚሰጡት አስተያየት በተማሪዎቹ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል፡፡ ይህ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ ተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርታቸው ተነሳሶት እንዲጨምር ወይም እንዲዳከም ያደርጋል ይህ አይነቱ ጉዳይ በቋንቋ ተስተምህሮት ወቅት ጉልቶ ሊታይ ይችላል (ሀብታሙ 1999፣25እና Petty 2004)፡፡

### 2.5.3. ቢጤዎች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምትና አመለካከት

በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የቋንቋ ትምህርቱን የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ና ግምት የተለያየ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ የቢጤዎቻቸውን አመለካከት እየተላመዱ ይሄዳሉ፡፡ ይህም ማለት ቢጤዎቻቸው ትጉና ታታሪ ከሆኑ ጓደኞቻቸውም ትጉህ ለመሆን በመሞከር ተነሳሶታቸውን ይቀስቅሳሉ፡፡ የቢጤዎቻቸው ተነሳሶት የተዳከመ ከሆነ የጓደኞቻቸውም ተነሳሶት እየተዳከመ ሊሄድ ይችላል በሌላ በኩል በተስተምህሮቱ ወቅት ተማሪዎች በቢጤወቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ግምትን (ዋጋን) ማግኘት ይሻሉ፡፡ ስለሆነም ቢጤዎቻቸው በነሡ ላይ የሚኖራቸው አመለካከት በተነሳሶታቸው ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያደርስ ይችላል (Harmer 2001፣53 Petty 2004 ፣45)፡፡

### 2.5.4. የቋንቋ መምህር

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱን የሚያስተምረው መምህር በተለየ መልኩ የማሪዎቹን ተነሳሶት ሊያጠናክር ወይም ሊያዳክም ይችላል፡፡ ይኸውም የቋንቋ መምህሩ ትጋት፣ ድክመት፣ ስብዕና፣ የትምህርት አቀራረብ ስልቱ ወዘተ በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ትልቅ ሚና አለው ማለት ይቻላል (Ur 1996፣ Pintrich and Schunk 2002 ሀብታሙ 1999)፡፡

በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ አራት ዓይነት የመምህር ባኽሪያት መኖራቸውን Parrott (1993) ያስረዳሉ። እነዚህም ባኽሪያት የሚከተሉት ናቸው።

1. ትጉነት ወይም ቆራጥነት የሚታይበት፣
2. ተማሪዎችን በተስፋ የሚጠባበቅ፣
3. ከተማሪዎች ጋር በጐ የሆነ ግንኙነትን የሚፈጥር፣ እና
4. ከተማሪ ወላጆች ጋር በጐ የሆነ ግንኙነት የሚያደርግ፣ መምህር ሊሆን ይችላል።

ሙሁሩ አክለው እንዳብራሩት የቋንቋ መምህሩ ለትምህርቱ ያለውን ተነሣሽነት ለተማሪዎቹ በማሣየት ተማሪዎቹ የሡን ፍላጎትና ተነሣሶት በመመልከት እንዲነቃቁ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም ለትምህርቱ ውስጣዊ ተነሣሶት ለማይታይባቸው ተማሪዎች የተለያዮ ስልቶችን በመለዋወጥ መሠረታዊ ውስጣዊ ተነሣሶት እንዲኖራቸው በትጋት ማስተማር ይጠበቅበታል። የቋንቋ መምህሩ የተማሪዎችን ስነ ልቦና በመረዳት ከምን አይነት ቤተሠብ መሀል እንደመጡ ክትትል በማድረግ ከተማሪዎች ወላጆች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ለትምህርቱ ፍላጐት እንዲያድርባቸውና ተነሣሶት እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላል። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት መምህር ጠቀስ ባህሪዎች በተማሪዉ የቋንቋ ተነሣሶት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

### 2.5.5. የማስተማሪያ ዘዴ

በመማር-ማስተማር ወቅት የቋንቋ ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል። እነዚህ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከተማሪዎቹ ፍላጐት፣ስሜት እና ችሎታ ጋር ሊጣጣሙ ወይም ደግሞ ላይጣጣሙ ይችላሉ። በመሆኑም የተማሪዎቹ ተነሳሶት ለማስተማያ ዘዴውእንደሚሰጡት ግምት ከፍ ወይመ ዝቅ ሊል ይችላል (Harmer 2001)።

### 2.5.6. የቋንቋ ትምህርቱ ትግበራዎች

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ የተግባር ክንውኖችን እና መልመጃዎችን እንዲተገብሩ ይደረጋሉ። ለነዚህ ትግበራዎች የተሰጣቸው ርዕስ፣ የሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ ያላቸው ርዝማኔና ያቀራረብ ስልታቸው መስህብነት ያላቸው ወይም የሌላቸው

ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም የተነሳ በትግበራዎቹ አማካኝነት የተማሪዎቹ ተነሳሶት ሊጠ ናከር ወይም ሊዳከም ይችላል ማለት ነው (Petty 2004 ፣ Ur 1996፣ Pintrich and Schunk 2002 እና ሀብታሙ 1999)።

ባጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ማኀበረሰቡ፣ ወላጆች፣ ቢጤዎች፣ የቋንቋ መምህሩና በክፍል ውስጥ የሚኖሩ ሁኔታዎች ማለትም መምህሩ የሚጠቀምበት የማስተማሪያ ዘዴና ትምህርቱን ለማስፈፀም ተዘጋጅተው የቀረቡት የተግባር ክንውኖችና መልመጃዎች ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን የተነሳሶት ደረጃ ሊያጐለብቱና ሊያዳክሙ ፣ተማሪዎቹን ውጤት ሊያስገኙ ወይም ውጤት ሊያሳጡ የሚችሉ ተላውጦዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

## 2.6. የተነሳሶት ብልሃቶችን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ስለመጠቀም

የሁለተኛን ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ሰፊ ድርሻ የሚሰጠው ተነሳሶት ከትምህርት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው መሆኑን አጥኚዎች ያስረዳሉ። Dornyei (2001) እና Young (1999) እንደሚያብራሩት ፣ ተማሪዎችን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ ለማድረግ በመጀመሪያ ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሊሆን የሚችለው የቋንቋ መምህሩ የተለያዩ ብልሃቶችንና ስልቶችን መጠቀም ሲችል ነው። የሚጠቀምባቸው የተነሳሶት ብልሃቶች ከቋንቋ ትምህርቱ፣ ከተማሪዎች አካባቢና የአኗኗር ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ ቢሆኑ ውጤትና ለውጥን ለማምጣት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

Ur (1996)፣Girard (1977)ን ጠቅሰው እንደገለፁት፣ በአሁኑ ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሶት ለመፍጠር እንደዋንኛ መሣሪያ የሚጠቀሙበት ስልት “ተማሪ -ተኮር” የማስተማር ዘዴ ነው። ይሁንና ተማሪዎቹ የተነሳሱ የሚሆኑት መምህራኑ ተግባራቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያበረታቱበትን መንገድ የቀየሱ እንደሆነ ነው። ለዚህም የቋንቋ መምህራኑ ኃላፊነትን መውሰድ ይኖርባቸዋል። Pintrich and Schunk (2002፣4) እንዳመለከቱት፣ መምህራን መጨነቅ ያለባቸው “ተነሳሶት ምንድን ነው?” በሚለው ጉዳይ ላይ ሳይሆን “ምን፣ መቼና እንዴት አስተምረን የተማሪዎችን ተነሳሶት ማምጣት እንችላለን” በሚለው ሐሳብ ላይ ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ Dornyei (2001) ና Petty (2004) ሐሳቡን እንዳብራሩት፣ መምህራን “Carrot and Stick”

“ሽልማትና ቅጣት” የሚለውን የማበረታቻ ስልት በመቀነስ በቂና ምቹ በሆኑ የማነቃቂያ ወይም የማበረታቻ ስልቶች ቢጠቀሙ ወደሚፈለገው ውጤት ማምራት ይችላሉ:: በመሆኑም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚከተሉትን ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፤

1. መስረታዊ የተነሳሶት ጉዳዮችን መፍጠር
2. ተፈላጊውን ተነሳሶት ማንቀሳቀስ
3. የተማሪዎችን ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ ናቸው::

እነዚህን ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ይሞከራል::

### 2.6.1. **መሠረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን መፍጠር**

Dornyei (2001) መሰረታዊ የተነሳሶት ሁኔታዎችን በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች አስፍረዋል:: የተነሳሶት ብልሃቶችን ሁሉንም በአንድ ጊዜ መጠቀም አይቻልም:: ተነሳሶትን ከፍ ለማድረግና ከውጤት ለማድረስ በቅድሚያ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ያስፈልጋል:: እነሱም

- ትክክለኛ የመምህር ባህሪና ጥሩ የመምህር ተማሪ ግንኙነት፣
- አስደሳችና አጋዥ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ፣
- ጥሩ የቡድን ስርአትን የያዘ የተማሪ ቡድን ጥምርታ ናቸው::

#### 2.6.1.1. **ትክክለኛ የመምህር ባሕሪና ጥሩ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት**

የመምህራን ባሕርይ ጉልህ የሆነ የተነሳሶት መሳሪያ ነው:: በመምህራኑ የሚደረግ ማንኛውም ነገር በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ ተፅዕኖን ያሳድራል:: የተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚያሳየውን ባሕርይ በመከተል የሚመጣ ሊሆን ይችላል Dornyei (2001) በተጨማሪም ተማሪዎች ለተስተምህሮቱ የሚያደርጉት ጥረት የላቀ የሚሆነው በመምህሩ አማካኝነት ነው:: ይኸውም መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር የሚያደርገው መልካም የሆነ ግንኙነትና “ተማሪ-ተኮር” በሆነው የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር በሚያሳየው ቀረቤታ ነው (Rodgers 1991)::

Alison (1993) መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚያደርጉት የእርስ በእርስ መተማመንና መከባበር በክፍል ውስጥ በሚካሄደው የተግባር ክንውን ላይ ወሳኝነት እንዳለው ይገልፃሉ። በተጨማሪም የመተማመኑና የመከባበሩ ሁኔታ ትጋትንና የትምህርት ጉጉትን በመምህሩ ላይ ይፈጥራል። ለማስተማር የሚተጋው መምህር ራሱን መሥዋዕት በማድረግ በቃልና ቃል-አልባ በሆኑ ስልቶች አማካኝነት ትምህርቱን ያቀርባል። ይህንንም በማድረጉ መምህሩ በተማሪዎቹ ዘንድ እንደ ጥሩ አርአያ ሊወሰድ ይችላል።

በአንፃሩ Wright (1987) ከተማሪዎቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌላቸውን መምህራን እንዲህ በማለት ይግልጿቸዋል። መምህራን እንደ አለቃና መሪ ብቻ ሆነው የመማር-ማስተማር ሂደቱን የሚያከናውኑ ከሆነ አቀባይና መጋቢ ብቻ ስለሚሆኑ የተማሪዎቹ ተሳትፎና ለትምህርቱ ያላቸው ጉጉት ጐልቶ ሊታይ አይችልም።
የሚከተሉት ነጥቦች የመምህር-ተማሪ መልካም ግንኙነት መገለጫ መንገዶች እንደሆኑ Dornyei (2001)ያስረዳሉ፤

- ተማሪዎች የመምህሩን እርዳታ ሲጠይቁ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣
- ተማሪዎችን እንደረዳት ሆኖ መቅረብ፣
- ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን በግል ለመወያየት መፍቀድ፣

ከነዚህ በተጨማሪ ሰብለ ወንጌል (2007) Walodkowski (1986)ን ጠቅሰው እንደገለፁት፣ ተማሪዎች በመምህራቸው ትኩረት እንደተሰጣቸው ሲያውቁ ጥሩ የሆነ ስሜትና የመማር ፍላጐት ሊኖራቸው ይችላል።
ለዚህም እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው፤

- የተማሪዎችን ስም በማስታወስ ሰላምታን መስጠት፣
- ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ማሳየት፣
- በክፍል ውስጥ ከአንደኛው ረድፍ ወደሌላኛው ረድፍ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ የመሳሰሉት የመምህር- ተማሪ መልካም ግንኙነት መገለጫ መንገዶች፣ ናቸው።

እነዚህን የመልካም ግንኙነት መገለጫ መንገዶች መምህራን ቢተገብሯቸው ተማሪዎቹ ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ የሆነ ምላሽን ሊያሳዩ ይችላሉ።

#### 2.6.1.2. አስደሳችና አጋዥ የክፍል ውስጥ ሁኔታ

የክፍል ውስጥ ሁኔታ ማለት Dunkin and Biddle (1994)ን Pintrich and Shunk (2002:322) ጠቅሰው እንዳስፈሩት፣ ማኀበራዊ ሥነልቦናዊና ስሜታዊ ባሕሪን የተላበሰ የመማሪያ ክፍል ማለት ነው። የክፍል ውስጥ ሁኔታ ንቁ ወይም ፍዝ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው ደግሞ አብዛኛውን ግዜ በመምህር ተማሪ ተራክቦ አማካኝነት ነው። የመምህር-ተማሪው ተራክቦ የሚካሄደው ተማሪዎቹ ነፃነት እንዲሰማቸው በሚያስችል መልኩ ከሆነ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ይኖራል የንቁ ተሳትፎ መኖር ደግሞ ተነሳሶት እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል። ነገር ግን የመምህር-ተማሪው ተራክቦ ነፃነትን የሚያሳጣና መምህሩ በበላይነት የሚመራው ከሆነ የክፍሉ ተሳትፎ ፍዝ ይሆናል። ይህ ደግሞ የተማሪዎቹ ተነሳሶት እየተዳከመ እንዲሄድ ያደርጋል።

Young (1999) የክፍል ውስጥ ሁኔታን በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል። የክፍል ውስጥ ሁኔታ በተማሪዎች ተነሳሶት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል። ይህም ማለት ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ ካለ ተማሪዎቹ በተስተምህሮቱ ወቅት ሃሳባቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ እምነታቸውን ለመግለፅ አይቸገሩም። ተማሪዎቹ አመለካከታቸውን በነፃነት መግለፅ መቻላቸው የቋንቋ ችሎታ የማሻሻል ጥረታቸውን ከፍ እንዲል ያደርግላቸዋል። ስለሆነም የቋንቋ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ሊያውኩና የመማር-ማስተማር ሂደቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተላውጠዎችን መቆጣጠርና ምቹ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ለመፍጠር መጣር ይኖርባቸዋል።

ያልተመቻቸ የመማሪያ የክፍል ውስጥ ሁኔታ ማለትም የቋንቋ ትምህርቱ አቀራረብ፣ የተማሪዎች የእርስ በርስ አለመደማመጥ፣ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ አሉታዊነት፣ ተማሪዎችን ጭንቀትና ብቸኝነት እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል። ስለሆነም በተማሪዎች ላይ የሚፈጠሩ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን አዝናኝና የሚያነቃቁ ማድረግ ይጠበቅበታል (Ur 1996፣ 277 ፣Good and Brophy 1994 ፣215)።

#### 2.6.1.3. ጥሩ የቡድን ሥነ ሥርዓትን የያዘ የተማሪ ቡድን ጥምርታ

Pintirich and Schunk (2002 ፣309) በክፍል ውስጥ የሚደረግ የተማሪዎችን አደረጃጀት የቡድን አወቃቀርን በተመለከተ ሦስት ዓይነት እንደሆኑ ይገልፃሉ።

እነሱም፡ ትብብራዊ፣ ውድድራዊና ግለሰባዊ ናቸው፡፡ በነዚህ ተሳትፎዎች ውስጥ ተማሪዎች አንዱ ከአንዱ የመማማርና የመተጋገዝ፣ አዎንታዊ ገፅታ ያለው የፉክክርና የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዲሁም በግል የመጣርን ልምድ ተማሪዎች ያካብታሉ፡፡ እነዚህ የአወቃቀር ስልቶች ለተማሪዎች ተነሳሶት ጠቀሜታ አላቸው፡፡

በሌላ በኩል Dornyei (2001) የቡድን ሥራን በተመለከተ የሚከተለውን ኀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ በማንኛውም የቡድን አደረጃጀት ውስጥ ተነሳሶትን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁለት ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ጉዳዮች የቡድን ጥምርታና የቡድን ሥነ-ሥርዓት ናቸው፡፡ የቡድን ጥምርታ "የእኛነት" ስሜት የሚታይበትና አባላቱ ለቡድናቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩበት ነው፡፡ በአንፃሩ ይህ ካልሆነ ግን የትብብር መንፈስ እጦትን ከማሳየቱም በላይ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ቁርጠኝነት እንዲቀንስ በማድረግ ውጤትን ወደማጣት ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ያደርጋል፡፡

የቡድን ጥምርታን ከፍ የሚያደርጉ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች መኖራቸውን Dornyei (1998) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፤

1. የቡድኑ አባላት እርስ በርሳቸው ይማማራሉ፤ መምህሩም ተማሪዎቹ ልምዳቸውን እንዲለዋወጡና ዕውቀት እንዲያገኙ እገዛ ያደርጋሉ፣
2. መደበኛ የሆነ የክፍል ውስጥ የመቀመጫ ቦታ ሥርዓትን በማስቀረት ተማሪዎች በቢጤ ውይይት፣ በአነስተኛ ቡድን ምሥረታ፣ በሚና ጨዋታ፣ ወዘተ. በማደራጀት እርስ በርሳቸው ተራክቦ እንዲያደርጉ ያግዛል፡፡
3. ተማሪዎች ለጋራ ዓላማቸው እርስ በርስ በመተባበር ችግሮችን በማቃለል መፍትሄዎችን ይፈልጋሉ፡፡
4. በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ አባላት እርስ በርሳቸው እየተወዳደሩ በመካከላቸው መልካም የሆነ ግንኙነትን ይፈጥራሉ

የቡድን ሥነ-ሥርዓትን በተመለከተ Dornyei (1998 ፣142) የሚከተለውን ኀሳብ አስፍረዋል፡፡ የቡድን ስርዓት ሲወጣ የቡድኑ አባላት የተስማሙበትን ሃሳብ በማፅደቅ ይሆናል፡፡ ስርዓቱም ተማሪዎቹ በእርስ በርስ ተራክቦ ወቅት ተግባራዊ የሚያደርጉት ነው፡፡ ባጭሩ መምህራን መልካም ግንኙነት ያለው ቡድን እንዲመሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ተሳትፎ ቢያጉለብቱ ተነሳሶታቸው እየጨመረ ይሄዳል ማለት ይቻላል፡፡

### 2.6.2. ተፈላጊውን ተነሳሶት ማንቀሳቀስ

Rogers (1991), Rosser and Nicholson (1984) እና Brophy (1998) እንደገለፁት፣ ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ አንድን ነገር የማወቅ ጉጉትና አካባቢውን የመመርመር ፍላጐት አለው። ተማሪዎችም ከሚማሩት ትምህርት ውስጥ የሚያስደስታቸውን ነገር ስለሚፈልጉ ለትምህርቱ ጉጉት ያላቸው ይመስላሉ። ነገር ግን የተማሪዎች አንድን ነገር የማወቅ ፍላጐት ለውጥን በማያሳዩ አንዳንድ የትምህርት ቤት ተፅዕኖዎች ምክንያት ሊዳከም ይችላል። ለምሳሌ የትምህርት ቤት ተማሪውን የመከታተያ ቅፆች (የስም መጥሪያ ቅፆች)፣ ለዚህ ተጠቃሽ ማስረጃ ይሆናሉ።

Brophy (1998) አያይዘው እንዳብራሩት፣ ምንም እንኳን ሌሎች አማራጮች ቢኖሩም፣ ብዙ መምህራን ትክክለኛ ተነሳሶትን ከፍ የማድረጊያ መንገድ ነው ብለው የሚያምኑት በክፍል ውስጥ የተሰጡትን ክንውኖች ለማሳካት የሚያደርጉትን ጥረት ነው። ይሁንና እነዚህን የክፍል ውስጥ ክንውኖች ተማሪዎች ምናልባት ላይመርጧቸው ወይም ደግሞ ላይደሰቱባቸው ይችላሉ። መምህራን አነቃቂ የሆኑ ሁነቶችን በክፍል ውስጥ ካላመቻቹ ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን በጐ አመለካከት ከፍ እንዲያደርጉ የተለያዩ መንገዶችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረቡት ነጥቦች ተፈላጊውን የተማሪዎች ተነሶሶት በመቀስቀስ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ጉዳዮች መሆናቸውን ምሁራኑ ጠቁመዋል።

#### 2.6.2.1 ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን መልካም አመለካከት ማሳደግ

Dornyei (2001) እንደገለፁት፣ ሁለተኛ ቋንቋን ለረጅም ጊዜ በፍላጐት መከታተል መልካም ወደሆነ አመለካከት በማሻገር ተማሪዎችን ውጤታማ ሊያደርጋቸው ይችላል። ለዚህም ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ከሁለተኛ ቋንቋ ጋር ትስስሮሽ ያላቸው ሦስት ጉዳዮች መኖራቸውን ምሁሩ ገልጸዋል። እነዚህንም ጉዳዮች ከዚህ በታች በዝርዝር ለማየት ይሞከራል፤

1. ከታላሚው ቋንቋ የትምህርት ሂደት ጋር አዎንታዊ ትስስርነት ያለው አመለካከት፡-

የተማሪዎችን ፍላጐት ለመቀስቀስና ከፍ ለማድረግ ዋናው ጉዳይ ትኩረታቸውንና መሻታቸውን በማነቃቃት ጥሩ ምስልን በአእምሯቸው ውስጥ መፍጠር ነው። ይህም ለውስጣዊ ተነሳሶት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ያሳያል።

2. ለአመለካከትና ለተነሳሱቱ የሚሰጠው ዋጋ ከታላሚው ቋንቋና ከተናጋሪዎቹ ጋር ያለው ተዛምዶ:-

ይህ ዓይነቱ ሂደት በማኅበራዊና በባህላዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ውህደታዊነትን የሚያመለክት ነው:: ይህም ከባህሉ፣ ከተናጋሪዎችና ከሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች ጋር ትስስሮሽ ያለው ነው:: የሚከተሉት ኀሳቦች ባህላዊ ዕውቀትን ለማግኘትና ውህደታዊነትን ከፍ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው::

- ✓ አስፈላጊ ከሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ባህል ፍላጐቶች ጋር ተማሪዎችን ማስተሳሰር፣
- ✓ በባህል ተመሳስሎዎች ላይ በማተኮር የባህል እውቀትን ማሳደግና ትስስርነትን መፍጠር፣
- ✓ ሁለተኛ ቋንቋ በክፍል ውስጥ ያለውን አዎንታዊ ተግባር ለተማሪዎች ማካፈል፣
- ✓ ስለ ቋንቋ ትምህርት አስፈላጊነት የተነገሩ፣ በህዝብ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸውን አባባሎችንና ጥቅሶች በመሰብሰብ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ማካፈል፣
- ✓ ስለ ሀገሪቱ ጥሩ መረጃ የያዙ በሁለተኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን እንዲፈልጉ በማበረታታት ያገኟቸውን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ከታላሚው ቋንቋ ባህል ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በማወቅ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሳደግ መጣር ተገቢ ይሆናል::

3. ታላሚው ቋንቋ ለተማሪዎች ያለው ጠቀሜታና ውጤት:-

ይህ የሁለተኛ ቋንቋን ማወቅ ሊያስገኝ ከሚችለው ማህበራዊ ጥቅምና ተግባራዊ ክንውን ጋር ትስስርነት አለው:: ይህ ለጥቅማጥቅም ዋጋን የመስጠት ሂደት፡- የገንዘብ ክፍያን፣ የስራ እድገትን የተሻለ የትምህርት እድልን በታላሚው ቋንቋ መረጃዎችን የማግኘት አጋጣሚ ወዘተ የመሳሰሉ ጥቅሞችን ያስገኛል::

Alison (1993) ይህንን ኀሳብ ሲያብራሩ፣ ጥቅምን የሚያስገኙ ብልሃቶች የተነሳሶቱን ዋጋ የሚያመላክቱ ዘዴዎች መሆናቸውን ገልፀዋል:: እነዚህንም ዘዴዎች ተማሪዎቹ ለሚጠቀሙባቸውና ውጤታማ ለመሆን የሚፈፅሟቸው ተግባራት አስቀድመው ዋጋ

የከፈሉባቸው በመሆናቸው ሁነቶቹን መለወጥም ሆነ ማሻሻል አይፈልጉም፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ብቃት ላይና በሚፈለገው ውጤት መካከል ትስስሮሽ ለመፍጠር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት፣ ጠቃሚ የሆነ ውጤትና ስኬታማ የሆኑ ብልሀቶች ይኖራሉ፡፡ መምህራንም ተማሪዎቹ በቋንቋው እንዴት እንደሚጠቀሙበትና በቋንቋው የመጠቀም ብቃታቸው እስከምን ድረስ እንደሆነ መቃኘት ይችላሉ፡፡

ባጠቃላይ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት በማሳደግና ለቋንቋው የሚሰጡትን ዋጋ ከፍ በማድረግ ተፈላጊውን ተነሳሶት ካለበት ደረጃ በማንቀሳቀስ ወደ ውጤት እንዲደርስ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡

#### 2.6.2.2. ውጤት የመጠበቅ ተስፋን መጨመር

ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ የሚለው ኀሳብ ላለፉት አርባ ዓመታት ያህል ጥናት ከተደረገባቸው የተነሳሶት ስነልቦናዊ ተፅኖዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ Bronphy (1998) ይህን ኀሳብ በተመለከተ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡ ሰዎች በአንድ ነገር ላይ ስኬታማ እንደሚሆኑ ተስፋ ካደረጉ ድርጊቱን ለመፈፀም ወደኋላ እንደማይሉ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጥሩ ሁኔታ ከተማሩ ውጤትን መጠበቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይሁንና ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ብቻውን በራሱ በቂ ባለመሆኑ በመልካም እሴቶች መታገዝ እንደሚገባው አጥኚዎች ይስማማሉ በመሆኑም ውጤትን የመጠበቅ ተስፋና ለአንድ ነገር የምንሰጠው ዋጋ ወይም ግምት በአንድነት የሚሄዱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምሁሩ አያይዘው፣ አንድን ነገር የመጠበቅ ሂደት የሚከናወነው በአእምሮ ውስጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚነሳሱ ተማሪዎች አንድን ነገር የመጠበቅ ተስፋቸውን የሚያሳድጉት፣ በነቃ አእምሮ ሁነቶችን በትክክለኛው መንገድ ሲያስተካክሉና በአዎንታዊ ሁኔታ ሲተገብሩ ነው፡፡ በተጨማሪ ለተማሪዎች ከባድና አስቸጋሪ የሆኑ ትግበራዎችን መስጠት ተገቢ አይሆንም፡፡

Dornyei (2001)ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ከፍ እንዲል የሚከተሉትን ዘዴዎች ይፋ አድርገዋል፤

1. አስቸጋሪ ለሆኑ ትግበራዎች ብቻ ሳይሆን ትግበራዎቹን መከወን እንደሚገባቸው ለተማሪዎቹ በቂ ግንዛቤ መስጠት፤

2. መምህራን የክፍሉን ሁኔታ በመምራት ላይ ላሉ፣ ተማሪዎቹ ወደ ተግባር ክንውኑ በቀጥታ እንዲገቡና አስቸጋሪ ትግበራዎችን ማከናወን እንዲችሉ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው እርዳታ ማድረግ፤
3. በትብብራዊና በአነስተኛ ቡድን ተደራጅተው ትግበራን በሚያከናውኑበት ወቅት ተማሪዎች የሚያውቁትን ነገር ለተመሳሳይ አላማ ከቢጤዎቻቸው ጋር አብሮ በመስራት እርስ በርሳቸው እንዲተጋገዙ ማድረግ፤
4. በትምህርት ክንውን ወቅት የሚጠበቁ የሌሎች ተማሪዎችን ስኬታማ ክዋኔዎች በምሳሌነት /በሞዴልነት/ ማቅረብ፤ ይህ የተግባር ሞዴል በጥራት የተሰራው በቢጤዎቻቸው ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም በነበሩ ተማሪዎች ሊሆን ይችላል። ተማሪዎቹ ከውጤቱ ምን እንደሚጠበቁ ለማሳየት ሲባል የምስልና የድምፅ መቅረጫዎችን በመጠቀም የውጤት ሞዴሎችን ማቅረብ ያስፈልጋል።

ባጭሩ ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ ምሁሩ እንደገለፁት በአእምሮ ውስጥ የሚከናወን ሂደት ሆኖ፣ ተማሪዎች ከሚያዩዋቸው የክንውን ውጤቶች የተነሳ ሊፈጠር የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህንንም ለማጠናከር ተማሪዎችን በበቂ ሁኔታ ለትግበራው ማዘጋጀት፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን መርዳት፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲተጋገዙ ማድረግና የተለያዩ ስኬቶችን በሞዴልነት ወስዶ ማየት ውጤትን የመጠበቅ ተስፋ እንዲጨምርና ተነሳሶት ከፍ እንዲል እገዛ እንደሚያደርግ መገንዘብ ይቻላል።

### 2.6.2.3. አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት

ስብለ ወንጌል (2007) Wodowsky (1966)ን ጠቅሰው እንደገለፁት፤ ተማሪዎች ትምህርቱ ሳቢና ማራኪ ቢሆንም ባይሆንም የተለያዩ የክፍል ውስጥ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን መሥራታቸው ያስፈልጋል። ይሁንና ከተማሪዎች ፍላጐትና መምህራን ካካበቱት ልምድ በመነሳሣት ተማሪዎች ምን ዓይነት ፍላጐትና ዝንባሌ እንዳላቸው መረጃ በመሰብሰብ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ። መምህራን የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግም ከተማሪዎቹ ልምድና ሕይወት ጋር የተዛመዱ ርዕሶችንና ትግበራዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ማራኪና ሳቢ ሆነው የሚዘጋጁት የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን ተነሳሶት ከፍ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ይቻላል።

#### 2.6.2.4 የተማሪዎች ፍላጐት እንዲጨምር ማድረግ

Gardner and Macintyre (1993) እና Petty (2004)ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ያላቸው ፍላጐት ከፍ ብሎ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ለማድረግ መምህሩ የሚከተሉትን ሐሳቦች ተግባራዊ ቢያደርግ የተሻለ እንደሆነ ያስረዳሉ፤

- መምህሩ በሚያበረታታ መልኩ የራሱን የትምህርት ፍላጐት ለተማሪዎቹ ማሳየት፤
- መምህሩ አጓጊና ጥያቄ ሊፈጥሩ በሚችሉ ነጥቦች ላይ በማተኮር ተማሪዎቹ እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ተጨባጭ በሆነ መንገድ መምህሩ የሚያስተምረው ትምህርት ጠቃሚ መሆኑን ለተማሪዎቹ ማሳወቅ፣
- ተማሪዎቹ የራሳቸውን ፈጠራና ገለፃ እንዲጠቀሙበት እድል መስጠት
- የተማሪዎችን የትምህርት ክንውኖች መደበኛ በሆነ መንገድ እየለዋወጡ እንዲሠሩ ማመቻቸት፣
- የሚያስደንቁና የሚያስገርሙ ሃሣቦችን በትምህርቱ መሃል ጣልቃ በማስገባት ተማሪዎችን ማነቃቃት፣
- በክፍል ውስጥ በትምህርት ክንውን ወቅት በቡድን ሆነው ሲሠሩ የተወዳደሪነት መንፈስን በመካከላቸው መፍጠር፣
- በተስተምህሮቱ ወቅት የሚቀርቡ ምሳሌዎችን ከኑሮአቸውና ከሕይወት ልምዳቸው ጋር በማያያዝ ማቅረብ፤

መምህሩ እነዚህን ኀሳቦች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ባግባቡ ከተጠቀመ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ላይ ፍላጐት አድሮባቸው ወደ ውጤት ሊያመሩ ይችላሉ፡፡

#### 2.6.2.5. የተማሪዎችን የዓላማ አፈፃፀም ማሳደግ

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ጥሩ ዓላማን ይዘው ለመማር ከተነሱ ለትምህርቱ ያላቸው የተነሳሶት ደረጃ ከፍ ያለ እንደሚሆን Gardner and Macintyre (1993፣ 133)፣Chanbers (1999፣34) Elliotet et al. (2005፣16) ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና በተስተምህሮቱ ተግባር ውስጥ ለምን እንደተሳተፉ በውል የማይገነዘቡ አንዳንድ ተማሪዎች ይኖራሉ፡፡ ስለሆነም መምህራኑ ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው የክፍል ውስጥ ተግባራት ተማሪዎቹ ሊያውቋቸውና ሊቀበሏቸው የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ትግበራዎቹን

ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር እያጣጣሙ የሚተገብሩ ካልሆኑ መምህሩ ተነሳሶትን ለመፍጠር የሚያደርገው ሙከራ ከንቱ ልፋት ይሆናል።

በሌላ በኩል Janet (1997) ተነሳሶትን በተመለከተ Kuyken Dall (1992)ን ጠቅሰው እንዳስፈሩት፣ ተማሪዎች ውጤታማ መሆን እንዲችሉ የራሳቸውን እቅድና ዓላማ መንደፍ ይኖርባቸዋል። መምህሩም የቋንቋ ትምህርቱን ከተማሪዎቹ ግላዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ የሚጠቀሙባቸውን የማስተማሪያ ስልቶች ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። William and Burden (1997) እንዳመለከቱት፣ የክፍል ውስጥ ትግበራዎችን መርጦ ባስፈላጊው ጊዜና ሁኔታ መጠቀም ተማሪዎቹ ወደ አንድ የትምህርት ዓላማ እንዲያመሩ ያግዛል።

### 2.6.3. **የተማሪዎችን ተነሳሶት መጠበቅና መንከባከብ**

Dornyei (2001፣71)የተማሪዎች ተነሳሶት በጥንቃቄ ሊያዝ እንደሚገባ በዝርዝር አስፍረዋል። ተነሳሶት በጥንቃቄ ካልተያዘና ካልተጠበቀ ድርጊቱ በሚከናወንበት ጊዜ የተማሪዎቹ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ እየተዳከመና በተግባር ክንውኑ ላይ መስላቸት ይታይባቸዋል። በዚህ ጊዜ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው ተነሳሶት እየቀነሰ ይሄዳል። ስለዚህ የቋንቋ መምህሩ በርካታ የተነሳሶት እንክብካቤ ብልሃቶችን መጠቀም ይገባዋል። ተማሪዎቹ በተፈጥሮ ያላቸው ዝንባሌ እየተዳከመ ሲሄድ የትምህርት አላማውን አቅጣጫ ይስታሉ። በዚህ ግዜ ተፈላጊው የተማሪዎች ተነሳሶት ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል። በተጨማሪም አዎንታዊና አሉታዊ ጎን ያላቸው ተፅዕኖዎች በትምህርቱ ላይ ይከሰታሉ። ስለዚህ ያላቸውን ተነሳሶት በጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልጋል። Raymond (1986 ፣144) ፣በበኩላቸው የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል።

በማንኛውም ሰው ውስጥ አንድን ፍላጎት የማሟላት ምኞት እንዳለ ሁሉ በትምህርት ትግበራዎችም ወቅት በተማሪዎች ላይ አንድን ፍላጎት የማሟላት ምኞት ይንፀባረቃል። በተነሳሶት ጥበቃና አፈፃፀም ዙሪያ የተለያዩ ብልሃቶች አሉ። እነዚህም ብልሃቶች የሰው ልጅ ባህርይ በሂደት ላየ እያለ በተለያዩ መንገዶች እንዲሻሻልና እንዲለዋወጥ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል የትምህርት ትግበራዎችን በማስተማር ሂደት ወቅት የተማሪዎችን ተነሳሶት እንዴት ከፍ ማድረግ እንደሚቻል እና ያለን

### 2.6.3.1. ተማሪዎች ያላቸውን ለራስ የተለየ ግምት መስጠት በመንከባከብ በራስ የመተማመን ብቃት ማሳደግ

በራስ መተማመን የሚለው ሕሳብ ለራስ የተለየ ግምት መስጠት፣ የራስ ብቃት፣ ራስን ማስጨነቅ ከሚሉት ፅንሰ ሀሣቦች ጋር ተዛምዶ አለው ፅንሰ ኀሳቦቹ በራሳቸው ውስብስብነት ቢኖራቸውም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተነሳሱታቸው አማካኝነት ወደ ትምህርት እንዲያተኩሩና ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ እንዲችሉ ያደርጋሉ። ይህ እንዲሆን ግን በራስ መተማመንና ለራስ የተለየ ግምት መስጠት የሚሉት ፅንሰ ኀሳቦች ጤናማ የሆነ የእርስ በርስ መደጋገፍ ሊያሳዩ ይገባል (Raymond 1986)። ይሁን እንጂ Hedge (2000) እንደሚጠቁሙት፣ እነዚህ ፅንሰ ኀሳቦች ምንም አይነት እንክብካቤ ቢደረግላቸው አስተማማኝ የሆነ መረጋጋት አይታይባቸውም። ምክንያቱም ምንም እንኳን መምህሩ ፈጠራዊ የተነሳሶት ኀሳቦች ቢያክሉላቸውም ተማሪዎች የጥርጣሬ መንፈስ ካላቸው በራስ መተማመናቸው ከፍ ሊል የማይችል በመሆኑ ነው።

Scheidecker and William (1999፣122) እንደሚየብራሩት፣ ተማሪዎች የራስ ብቃታቸው አነስተኛ ሆኖ አስቸጋሪ ክንውኖች ሲሰጣቸው ክንውኖቹን በስኬታማነት እንዴት መተግበር እንደሚገባቸው ከማተኮር ይልቅ ከችግራቸው እና ከብቃት ማነሳቸው ጋር አብረው ይኖራሉ። ከዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ችሎታቸው እየቀነሰ ይሄድና ከራስ አለመታመማናቸው ጋር አብረው ይኖራሉ፤ በራስ የመተማመን ብቃታቸውም ከውስጣቸው ይጠፋል።

በአንፃሩ ጠንካራ የሆነ የራስ ብቃት:- የተማሪዎችን የሥራ ክንውን ባሕርይ ማለትም በክንውን ተሳትፎ ወቅት ስለራስ ማንነት ከሚስብ ይልቅ ስለክንውኑ የማሰብ፣ በራስ ተማምኖ ተስማሚ ሁኔታዎችን የማቅረብ ፣ ውድቀት በሚያጋጥምበት ጊዜ ጥረትን የማጉልበት ችሎታን ያሳድጋል፤ ከፍ ያደርጋል።

Dornyei (2001፣87)ታዳጊ ወጣቶችን አስመልክተው የራስ መተማመን ብቃታቸው ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ገልፀዋል። ታዳጊ ወጣቶች በአካባቢያቸው በሚደርሱባቸው ግፊቶች አማካኝነት ለተለያዩ ጥቃቶች ይጋለጣሉ። ከዚህም የተነሳ ስለ እፅኝነት፣ ስለቡድናዊነት፣ ስለዘር፣ ስለአለባበስ፣ እንዲሁም ስለትምህርት ውጤታቸው ሊያስቡና ሊጨነቁ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ የራስ መተማመን ብቃታቸው ዝቅተኛ ይሆናል። Scheidcker and William (1999) ይህን ኀሳብ አስመልክተው

የሚከተለውን ብለዋል። በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባሉ ተማሪዎች ለራስ የተለየ ግምት መስጠት፣ በራስ መተማመን፣ በራስ ብቃት፣ ለራስ መጨነቅ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ታዳጊ ወጣቶች በመሆናቸው አንድ ነገር ሲያጋጥማቸው በራሳቸው ከመተማመን ይልቅ የስሜት ተለዋዋጭነት ፣ ጥረጣሬ እና ጭንቀት ስለሚታይባቸው ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርታቸው ወቅት በራሰ የመተማመን ብቃታቸውን እንዴት ማሳደግና መንከባከብ እንደሚቻል ማስብ አስፈላጊ ጉዳይ ሆኗል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ጥረታቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙበትና ቋንቋቸውን ለማሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አምስት መርሆችን Dornyei (2001፣ 130) ይፋ አድርገዋል።

- የተማሪዎች በራስ የመተማመን ብቃት ለውጥን እያሳየ እንዲሄድ እምነታቸውን ማበረታት ይቻላል፤
- መምህራን ንቁ የሚያደርግ መደበኛ ልምምድን በመስጠት ለቋንቋ ትምህርቱ ብቃት ምቹ የሆነ አመለካከትን መፍጠር ይችላሉ፤
- ተማሪዎች ለትምህርቱ ጥሩ ስሜት ከኖራቸውና አስተዋያዎ ካበረከቱ የሚሰጠውን የትግበራ ክንውን ለመሥራት ፍላጐት ያድርባቸዋል፤
- ተማሪዎችን ለማበረታታት ከግለሰቦች የሚወጡ ጥቂት ቃላት በቂ ናቸው፤
- መምህራን የትምህርቱን ዓውድ አዝናኝ በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚታየውን የተማሪዎች ጭንቀትና ተስፋ ማጣት መቀነስ ይችላሉ፤ በአጭሩ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በሚያደርጉት እንክብካቤና ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር በሚያደርጉት ጥረት አማካኝነት በራስ የመተማመን ብቃታቸው ከፍ ሊል ይችላል።

### 2.6.3.2. በራስ መማር

እንደ Benson (2000) አመለካከት፣ ትምህርት በሰዎች ባሕርይ ላይ ተፅእኖን ሊያስከትል የሚችል ጉዳይ ነው። ምሁሩ በራስ ላይ እድገትን ለማምጣት የሚያለማምዱና የሚያበረታቱ አምስት ነጥቦችን ለያይተው አሳይተዋል፣

1. **ተማሪ-ተኮር አቀራረብ፡-** ይህ ግልፅ የሆነ ስነ ልቦናዊና የባህርይ ለውጥ በተማሪው ላይ ያመጣል።
2. **የመረጃ ምንጭ-ተኮር አቀራረብ፡-** ይህ ደግሞ በትምህርቱ የመረጃ ምንጮች ላይ ነፃ የሆነ ተራክቦ እንዲኖር ያደርጋል።

3. **ቴክኖሎጂ-ተኮር አቀራረብ፡-** ተማሪዎች ቴክኖሎጅን በመጠቀም ከትምህርቱ ጋር ነፃ የሆነ ተራክቦን ያደርጋሉ::
4. **የክፍል ውስጥ-ተኮር አቀራረብ፡-** ይህ የሚያመለክተው በመምህሩና በተማሪው መካከል ያለው ግንኙነት አወንታዊ ለውጥን እያመጣ ሲሄድ ነው::
5. **መርሐ ትምህርት-ተኮር አቀራረብ፡-** ይህ የተማሪዉን ሀሳብ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር በማገናዘብ ትምህርቱ እንዴካሄድ ያደርጋል::

በራስ መማር ማለት Ushioda (1997፣41) እንደጠቀሙት፣ በራስ የሚደረግ ተነሳሶት ስለ ትምህርት ልምድና ስለትምህርት ዓላማ ምንነት መመርመር የሚያስችል ነው:: በመሆኑም ተነሳሶት የአውንታዊ ሀሳብ ተግባርና የእምነት መዋቅር ነው:: በተጨማሪም በትምህርቱ ውስጥ ጐልቶ የሚታይ ዘላቂነት ያለው አዎንታዊ ሀሳብ ነው::

### 2.6.3.3. የተማሪዎችን እርካታ መጨመር

Covington (1999 ፣127)ስለ እርካታ ሲገልፁ፣ የእርካታ ስሜት የተነሳሶት ዋነኛ አካል ሆኖ አስፈላጊና የሚያበረታታ የሥራ ክንውን ባሕርይ ነው:: የመምህራን የተነሳሶት ብልሀቶች አላማቸው የተማሪዎችን እርካታ በመጨመር ስራቸውን በፈቃደኝነት በመተግበር ላይ ያተኮረ ነው:: ማበርታት ልክ እንደ ሽልማት የሚያኮራና የሚያስከብር ውጤትን ያስገኛል:: ተማሪዎች በትክክል እና በስርዓቱ ባይስሩም እንኳን የመጨረሻ የሆነውን የመውደቅ ወይም የማለፍ ግብ ውጤታቸው እርካታቸው የተለያየ እንዲሆን ያደርጋል:: አንድ ውጤት የሚያተኩረው ከመማር ሂደት ይልቅ በክዋኔ ብቃት ላይ ነው:: በርካታ ተማሪዎች አሁን ያሉበት ደረጃ ያደረሳቸው በመጀመሪያ ያገኙት ውጤት ነው::

በሌላ በኩል Haris (1991) ውጫዊ ተነሳሶት በውስጣዊ ተነሳሶት አማካኝነት ኀይል አግኝተው መነቃቃት ላልቻሉ ተማሪዎች እንደ ሽልማት ሊረዳ የሚችል ጉዳይ እንደሚሆን ገልጸዋል:: ለመጥፎ ባኀርያት የሚሰጡ ትችቶችና ለጥሩ ባህርያት የሚቀርቡ ምስጋናዎች እንደ ሽልማት ይቆጠራሉ:: Haris (1991) አክለው እንደአብራሩት፣ በትምህርት ቤቶችም ሆነ በኮሌጆች ውስጥ ለጥሩ የክዋኔ ብቃቶች ምሳሌ የሚሆኑ ሰርተፍኬቶች፣ መጽሐፍቶች፣ ቃላዊ ምስጋናዎች ይሰጣሉ:: ዋናው ነገር ውጫዊ ተነሳሶት በትክክለኛ ጊዜው ከተሰጠ ውስጣዊ ተነሳሶትን ማስገኘት ይችላል:: ባጭሩ ለጥሩ ስራ የሚሰጥ ሽልማት ጥሩ ስሜትንና አመለካከትን አስገኝቶ ለእርካታ ያበቃል ማለት ይቻላል::

### 2.6.3.4. የትምህርት ትግበራዎችን በተነሳሶታዊ መንገድ ማቅረብ

Good and Brophy (1994) ለትግበራዎች የሚደረግ ተነሳሶቶች ውጫዊና ውስጣዊ ባህርይ ያሏቸው በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ከተማሪዎች ተነሳሶት ጋር ግንኙነት ያለው ትግበራ እውነተኛ ተግባቦትን የሚያሳድግ ነው፡፡ Nunan (1989) በበኩላቸው ደግሞ ጥሩ ትግበራዎች የሚያካትቷቸው ክንውኖች በተማሪዎች መካከል የሚካሄደውን እውነተኛ ተግባቦታዊ ተራክቦ የሚያሳድግና በሐሳቦች ላይ ለመስማማት ተማሪዎችን የሚያበረታታ ነው ሲሉ ፣Parrott (1993) ደግሞ የሚከተለውን ሐሣብ ስንዝረዋል፣ ክንውኖችን መምረጥ የሚገባን የቋንቋ ትምህርቱን ለማካሄድ ብቻ ሳይሆን አዎንታዊ የጋራ ስሜቶችንና አመለካከቶችን ለመደገፍ ጭምር ነው፡፡ Hutchinson (1988) ደግሞ በበኩላቸው የቢጤና የቡድን ሥራዎች አሉታዊነት የሚታይባቸውን የተማሪዎችን ውስጣዊ ስሜቶች ለማነሳሳት እንደሚጠቅሙ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ክንውኖቹ ዓላማዎችን ግልፅ ለማድረግ ይጠቅማሉ፡፡ ተማሪዎች የትምህርት ተግበራዎችን ግብ ከተረዱ ከውስጥ በመነጨና በጠነከረ ፍላጐት ክንውኑን ይፈፅማሉ፡፡

Good and Brophy (1994) እንደገለፁት፣ ጥሩ ትግበራዎች ለዕውቀት ዋጋን ይስጣሉ፡፡ በተጨማሪም በክንውኑ ወቅት ክሂሎች እንዲዳብሩ ይረዳሉ፡፡ ይህም ማለት ትግበራዎቹ ለተማሪዎች ጊዜያዊና ቀጣይ ሕይወታቸው የሚሆኑ ዕውቀቶችን ያስጨብጣሉ፡፡

Harmer (1991) እንደገለፁት፣ ትግበራዎች ውጤታማ መሆን አለባቸው፡፡ መምህራን በጣም ከፍተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ የሆኑ ትግበራዎችን መቅረፅ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ መሆንና ሙሉ ለሙሉ ውጤት አልባ መሆን ተነሳሶትን ሊያዳክም ይችላል፡፡

Conningsworth (1984) የተለምዷዊ ትግበራ መመሪያ ዓላማዎችን እንደሚከተለው በዝርዝር አስፍረዋል፤

1. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚፈፅሙት ተግባር ምንድን ነው?
2. ትግበራዎቹንስ መቼ ይጨርሳሉ?
3. እነዚህ አፈፃፀሞች እንዴት ይገመገማሉ?

በሌላ በኩል ወደ ተነሳሶት የሚያስገቡ ክንውኖች ቢያንስ ሦስት ተግባራት ይኖራቸዋል፤

1. የትግበራዎችን ዓላማና አጠቃቀም ይገልፃሉ፡፡

2. ተማሪዎቹ በትግበራው ላይ ያላቸውንና የሚኖራቸውን ተሳትፎ ያሳያሉ::
3. ትግበራዎችን ለመሥራት የሚበጅ ትክክለኛ ብልሀቶችን ይጠቁማሉ:: በአጠቃላይ በተነሳሶታዊ መንገድ ትግበራዎችንና ክንውኖችን ማቅረብ፣ ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግ፣ እንዲሁም አመቺ የሆኑ መመሪያዎችን መቅረፅ የተማሪዎቹ ፍላጐት ሙሉ እንዲሆንና ክንውኑን እንዲሰሩ ያደርጋል::

2.6.3.4.1. ትምህርቱን አነቃቂና አስደሳች ማድረግ

Keller (1983) እንደገለፁት፣ ሰዎች የወደዱትን ሥራ ኃይላቸውንና ጊዜያቸውን ተጠቅመው ለመሥራት ፍቃደኞች ናቸው:: ተማሪዎችም የሚወዱትን ትምህርት በክፍል ውስጥ ለመማርና ትግበራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ:: Dornyei (2001) የትምህርት ክንውኑን የተዋጣለት ለማድረግ ሦስት ዓይነት ብልሃቶች እንዳሉ ይጠቁማሉ፣

1. የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመርና ክንውንን የበለጠ አስደሳች ለማድረግ የተናጠል ሥራን አለማዘውተር:: መምህራን የትምህርት ክንውኖችን በመለያየት ተማሪዎችን ማስተማር ይችላሉ:: ለምሣሌ የቋንቋ ክሂልን በተመለከተ ሲያስተምሩ የፅህፈት ክሂልን ከንግግር ክሂል በመለየት፣ ተግባቦታዊ ክንውንን ሲያካሂዱ የማዳመጥን፣ የመመልከትንና የመዳሰስን መግባቢያዎች በመለያየት ያቀርባሉ፣፡ ተማሪዎችን በማደራጀት ረገድ ደግሞ የቡድን ሥራን ከቢጤ ሥራ ለይተው ያቀርባሉ::
2. ለትግበራው የሚሆኑ አስፈላጊ ሂደቶችን በየዓይነቱ አቀናጅቶ ማቅረብ:: መምህሩ ትምህርቱን የሚያቀርብበት ስልት፣ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ፣ የተማሪዎች በተሳትፎ ወቅት ያላቸው ቆይታ፣ የመማሪያ ክፍሉ የወንበርና የጠረጴዛ አቀማመጥ ወዘተ... ትምህርቱ አሰልቺ እንዳይሆን እርስ በርስ ተቀናጅተውና የመማሪያ ክፍሉ ተደራጅቶ የሚሰጠውን ትግበራ ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል::
3. የተመረጡ ይዘቶችን ለትግበራ ክንውኑ መጠቀም Good and Brophy (1994) እንዳመለከቱት የትምህርት ትግበራው ማራኪና አነቃቂ ሊሆን የሚችለው ትግበራው የያዘው ይዘት የተመረጠ ሲሆን ነው:: ሳቢና የተነሳሶት ባሕሪያት የሚታይባቸው የትግበራ ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. ተማሪዎቹ ችግርን እንዲያቃልሉ፣ አዳዲስ ግኝቶችን እንዲያገኙ፣ የተሸሸጉ መረጃዎችን እንዲያወጡ የሚያደርጉ የትግበራ ይዘቶች፣

ለ. ተማሪዎች በርዕሱ አማካኝነት ተገፋፍተው መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርጉ ተወዳጅ ይዘቶች፣

ሐ. አሰልቺነትን የሚያስወግዱ አዳዲስ ወይም ያልተጠበቁ እንግዳ የሆኑ ይዘቶች፣

መ. እያንዳንዱን ተማሪ የግል ሕይወቱን እየነካ ሊያነቃቃ የሚችል ግለሰባዊነት የሚታይበት ይዘት፣

ሠ. ደስታን በመስጠት ለእርካታና ለሽልማት የሚያበቃ የአወዳዳሪነት መንፈስ የሚታይበት ይዘት፣

በአጭሩ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የትግበራ ይዘቶች ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ትምህርቱን አስደሳች ለማድረግ ጉልህ ሚና አላቸው::

2.6.3.4.2. **የሚያነቃቁ ምጋቤ-ምላሽና ሽልማትን መስጠት**

በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ምጋቤ ምላሽ አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: Harmer (2001) እና Pintrich and Schunk (2002) ምጋቤ ምላሽን እንደሚከተለው ገልፀውታል፤ "ምጋቤ ምላሽ ከአንድ ድርጊት ወይም መልስ በኋላ ተከትሎ የሚሰጥ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ሊያመጣ የሚችል ምላሽ ነው::"

በተጨማሪም በተስተምህሮቱ ወቅት ዓይነተኛ የማስተማሪያ ተግባር Pintrich and Schunk (2002፣322) መምህሩ ምጋቤ ምላሽን ለተማሪዎች ሲሰጡ ለተለየ ዓላማና ተግባር ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል:: ለምሳሌ፡ በሚያግባባ መልኩ ተማሪውን ለማበረታታት አንድን ስሕተት ለይቶ ለማሳየት ወይም እንዲያሻሽል ለማድረግ ወዘተ ሊሆን ይችላል:: Rosenshine and Stevens (1986) ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ የሚከተለውን ኀሳብ ሠንዝረዋል:: ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አንድን ተግባር ሲፈፅሙ ትክክለኛ መረጃን የሚሰጥ ወይም ስሕተቶችን የሚያስተካክል ነው:: ትክክለኛ መረጃን ሊሰጥ የሚችል ፈጣን ምጋቤ-ምላሽ የተማሪዎችን ተነሳሶት ከፍ ከማድረጉም በላይ የተወዳዳሪነትን መንፈስ እያዳበሩ እንዲሄዱ ያደርጋል:: ለምሣሌ፡ "ይህንን ስራህን /ሽን/ በጥንቃቄ አስቀምጠው /ጭው/" ወይም "ይህን መስራት እንደምትችል /ይ/ አውቃለሁ"

የሚሉ ምጋቤ ምላሾችን መምህሩ ቢሰጡ ተማሪው የበለጠ እንዲነሳሳና የተሻለ ነገር እንዲሰራ የሚገፋፋ ሊሆን ይችላል::

Brophy (1998) ምጋቤ ምላሽ በምስጋና ሊቀርብ እንደሚችል አመልክተዋል:: ምስጋና አዎንታዊ ምላሽን የሚያንፀባርቅ ሲሆን የተሰራውን ሥራ ትክክለኛነት ማረጋገጫ መንገድ ነው:: Wittrock (1986) ምስጋናን በተመለከተ ሲያብራሩ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ተደጋጋሚ ምስጋና ተማሪዎች ትክክለኛ ባህሪን እንዲያመጡ ከማድረግ ይልቅ የመምህሩን ምስጋና ጠባቂ እንዲሆኑ ያደርጋል ሲሉ Brophy (1998) ይህን ሀሳብ በመቃወም ምስጋና ማለት መምህሩ ለተማሪው ያለውን እምነት የሚያመለክትበት መረጃ ነው:: በተጨማሪም ተማሪው ስህተት ሲሰራ "አንተ/ቺ በደንብ እንደምትሰራ /ሪ/ አውቃለሁ፤ ምነው ዛሬ?" የሚል ምጋቤ ምላሽ መምህሩ ቢሰጥ ተማሪው ከስህተቱ ታርሞ እንደገና እንዲሰራ የሚገፋፋ ይሆናል::

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ምጋቤ ምላሽ በተማሪው እምነት፣ ጥረትና ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል፣ መምህሩም በአግባቡ ሊጠቀምበት የሚገባ በመማር-ማስተማር ወቅት የተማሪው ተነሳሶት እየጨመረ እንዲሄድ የሚያደርግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው::

## 2.7. ቀደምት ሥራዎች

በመማር ማስተማሩ ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበትን የተነሣሶት ስልት በሚመለከት ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎችን አጥኝዋ ማግኘት አልቻለችም ይሁንና እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ዙሪያ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የተነሣሶት ስልት አተገባበር ምን እንደሚመስል የሚያሣዩ ጥናቶችን ማግኘት ተችሏል ጥናቶቹም ከዚህ ጥናት ጋር የይዘት ዝምድና የሚታይባቸው በመሆኑ እንድነታቸውና ልዩነታቸው ከዚህ በታች ለመቃኘት ተሞክሯል::

1. ሙሉጌታ (1997) "motivation in listening class of college English." በሚል ርዕስ በማዳመጥ ክሂል ጊዜ የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሣሶት ምን ያህል እንደሆነ የሚመረምር ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ አመት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ አካሂደዋል:: በጥናቱም ለተማሪዎችና

ለመምህራን የቀረቡ የፅሑፍ መጠይቆች በዋናነት የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያ ሆነው ተግባር ላይ ውለዋል። በተጨማሪም ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሠብሠቢያነት አገልግሏል። በዚህ ጥናትም ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል ያላቸው ተነሣሾት ዝቅተኛ በመሆኑ ለማዳመጥ ክሂል ያላቸው ግንዛቤ ከፍ እንዲልና መምህራኑም ተማሪዎችን ለማነሣሣት ጥረት እንዲያደርጉ መፍትሄ ተጠቁሞአል።

2. ባዮሽ (2007) "A study of the motivation techniques employed by EFL Teachers: In the case of two schools the primary schools in bure wereda, west Gojjam." በሚል ርዕስ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የተነሣሾት ስልትን እንዴት እንደሚተገብሩ በምዕራብ ጐጃም፣ በቡሬ ወረዳ በሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት አካሂደዋል። በጥናቱም ለመምህራንና ለተማሪዎች ያዘጋጁትን የፅሁፍ መጠይቅ በቀዳሚ የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያነት በመጠቀም፣ በአጋዥነት ደግሞ ለመምህራን ያዘጋጁትን ቃለ መጠይቅ ተግባር ላይ አውለዋል። ከጥናቱም የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል። መምህራን መልካም የሆነ የመምህር ተማሪ ግንኙነት በመፍጠር፣ ተማሪዎች ያለ ፍርሃት የክፍል ተሣትፎ እንዲያደርጉ በመገፋፋት፣ አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች በመስጠት የተነሣሾት ስልቶችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ቢሞክሩም በተማሪዎች ተነሣሾት ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ችግሮች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተከስተዋል። እነዚህም ችግሮች በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት የማስተማሪያ መሣሪያዎች እጥረት ናቸው። ከዚህም የተነሣ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመቆጣጠርና የሁሉንም ተማሪዎች ተነሣሾት ከፍ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመልክቷል።

3. ሠብለ ወንጌል (2007) ደግሞ "An Assessment of teachers, motivational strategies in ELT classroom: two government universities and two colleges in Oromia Region infocus." በሚል ርዕስ በነቀምቴና በአዳማ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና መምህራን ማሠልጠኛዎች የሚያስተሣሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የተነሣሾት ስልቶችን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አጥንተዋል። በጥናቱም ለመምህራኑ የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ዋና የመረጃ መሠብሠቢያ ሲሆን ቃለ መጠይቅና የክፍል ምልከታ በደጋፊነት መረጃዎችን ለመሠብሠብ ግልጋሎት ላይ ውለዋል። ከጥናቱም የሚከተለው ውጤት

ተገኝቷል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና አስደሣች የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታን በመፍጠር በራስ መተተማመንን በማጐልበት ወዘተ የመሣሠሉት አንዳንድ የተነሣሶት ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ባለመሆኑ ስርዐተ ትምህርቱ ከአካባቢው ባህልና ከኢትዮጵያ የቋንቋ ስነ ልሣናዊ አውድ ጋር ተዋህዶ የመማሪያ መፅሀፎቹ እንዲዘጋጁና መምህራኑም ተማሪዎቻቸውን ማነቃቃት እንዲችሉ ስልጠና እንዲሠጣቸው በጥናቱ ተጠቁሞአል።

ከላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች በተነሣሶት ላይ በማተኮራቸው ከዚህ ስራ ጋር በጥቂቱም ቢሆን ተመሣሣይነት ይታይባቸዋል። በተለይ በተራ ቁጥር ሁለትና ሦስት ላይ የተጠ ቀሡት ሥራዎች የተነሣሶት ስልቶች በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገበሩ ያጠኑ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ናቸው። ይሁንና በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሠው ሥራ በተናጠል በአንድ ክሂል ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ሊለይ ችሏል። በተጨማሪም ጥናቱ በዮኒቨርሲቲ የተካሄደ በመሆኑ በክፍል ደረጃው ሊለይ ችሏል። ከዚህም ሌላ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሠው ስራ በመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛ እርከን ትምህርት ላይ የተካሄደ ጥናት ሲሆን በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተጠቀሠው ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሚያስተምሩ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረገው የክፍል ደረጃ ከቀደምቶቹ ስራዎች የተለየ ሆኗል።

በሌላ በኩል ከላይ የተጠቀሡት ጥናቶች በዋናነት ለመረጃ የተጠቀሙበት የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያ የፅሁፍ መጠይቅ በመሆኑ ከዚህ ጥናት የተለዩ ያደርጓቸዋል። በተጨማሪ ጥናቶቹ የተካሄዱት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶችን በንፅፅር የተመለከተ ነው። በመሆኑም ከዚህ ጥናት በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተነሣሶት ስልቶችን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሚያሣይ ውጤት አስገኝቷል። ባጠቃላይ ይህ ጥናት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ከተሠሩት ቀደምት ስራዎች ሊለይ ችሏል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱን ፍተሻ ሥራ ከዳር ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ የመረጃ አሰባበሰብ ሂደትና የጥናቱ አተናተን ስልት በዝርዝር የቀረበበት ነው። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡም ገለፃዊ በሆነ መንገድ ነው።

## 3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.1.1.የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ ሃያ ሰባት ዞኖች መካከል አንዱ በሆነው በአዳማ ልዩ ዞን ነው። ዞኑ ተተኳሪ ሊሆን የቻለው በአመቺ የናሙና ዘዴ ነው። ይህም የሆነው የአዳማ ልዩ ዞን በአዲስ አበባ አካባቢ በቅርብ ርቀት ከሚገኙት ዞኖች መካከል አንዱ በመሆኑና አጥኚዋ ተንቀሳቅሳ ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ ቦታ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙበት፣ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በትምህርትነት የሚሰጥበት አካባቢ በመሆኑ ነው።

### 3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በአዳማ ልዩ ዞን ውስጥ ከሚገኙት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ የመንግስትና ሦስት የግል ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተወስደዋል ትምህርት ቤቶቹም አዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት፣ ሆሊ ኢንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግል አዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግል አዳማ ፀሐይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግል ናቸው። ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡት በታላሚ ናሙና የአመራረጥ ዘዴ ነው። ምክንያቱም የአዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በልዩ ዞኑ ከሚገኙት ሦስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ብዛት ያላቸው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚገኙበት በመሆኑና ተፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንደሚያስችል በመታመኑ ነው። በተጨማሪም ሦስቱ የግል ትምህርት ቤቶች በተቀራረበ ሥፍራ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ከጊዜ ዓንፃር ጥናቱን ለማካሔድ አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ነው።

### 3.1.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ እርከን በሆነው በዘጠነኛ ክፍል ላይ ያተኮረ ነው። የክፍል ደረጃው መመህራን ተማሪዎቻቸውን ለሁለተኛ ደረጃ አጠቃላይ ሀገር አቀፍ ፈተና የሚያዘጋጁበትና ከወዲሁ ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸወ የሚያደርጉበት በመሆኑ በታላሚ የናሙና ዘዴ ሊመረጥ ችሏል።

### 3.1.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በሆሊ ኤንጅልስ፣ በአዋሽ እና በአዳማ ፀሐይ የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሙሉ ለሙሉ በጠቅላይ የንሞና ዘዴ የጥናቱ ተተኳሪ ሆነው ሲወሰዱ፣ በአዳማ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙት አምስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ሦስቱ በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተጠኚ ሊሆኑ ችለዋል። ይህም ሊሆን የቻለው በምልከታው ወቅት የማይደራረቡ የክፍለ ጊዜ ድልድሎችን በማየት እና በመምረጥ ነው።

### 3.1.5. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ከአራቱ የናሙና ትምርህት ቤቶች ውስጥ ሁለት መቶ ሰባ የሚሆኑ የዘጠ ነኛ ክፍል ተማሪዎች በስርዓታዊ የንሞና ዘዴ ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። ተግባራዊ የሆነውም በአዳማ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምርህርት በት ከሚገኙት ሰላሳ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ከያንዳንዳቸው አምስት አምስት ተማሪዎችን በንሞና በመውሰድ ነው። የናሙና አወሳሰዱም ሂደት እንደሚከተለወ ነው። በቅድሚያ በእያንዳንዱ የዘጠነኛ ክፍል ምድብ ውስጥ ከሠባ ሁለት እስከ ሠባ ስባት የሚደርሱ ተማሪዎች እንደሚገኙ ምክትል ርዕሰ መመህሩ በሰጡት መረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በተማሪቹ የሥም መጥሪያ ተራ ቁጥር መሰረት አስራ ሦስት አስራ ሦስት ቁጥሮችን በማለፍ (13፣ 26፣ 39፣ 52፣ 65) በድምሩ አንድ መቶ ሰማንያ ተማሪዎች ተመርጠ ዋል።

በሌላ በኩል ተተኳሪ በሆኑት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች እንዳሉ በትምህርት ቤቶቹ ርእሳነ መምህራን አማካኝነት ተረጋግጧል። በዚህም መሰረት በሆሊኢንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙት ሦስት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ሐምሳ ሦስት ሐምሳ ሦስት

ተማሪዎች በአዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙት በሦስቱም የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ከሃምሳ ሁለት እስከ ሃምሳ አራት የሚደርሱ ተማሪዎች፣ በአዳማ ፀሀይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ሃምሳ አራት ሃምሳ አራት ተማሪዎች በመገኘታቸው ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ ምድብ በሥም መጥሪያ ተራ ቁጥራቸው መሠረት አምስት አምስት ቁጥሮችን በማለፍ አሥር አሥር ተማሪዎች ከየምድቡ፣ ሰላሳ ሰላሳ ተማሪዎች ከየትምህርት ቤቱ በድምሩ ዘጠና ተማሪዎች በሥርዓታዊ የናሙና ዘዴ ተወስደዋል። ይሁንና በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር እጅግ የተራራቀ በመሆኑ በናሙናነት የተመረጡት የተማሪዎች ቁጥር ሊለያይ ችሏል። ያለው (1998፣ 146) "የአካላዩ ቁጥር በበዛ ቁጥር የናሙናውም ቁጥር መብዛት ይኖርበታል" በማለት እንደገለፁት ከመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተወሠደው የናሙና ቁጥር ሊበዛ ችሏል።

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጥናቱን ለማካሄድ የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፅ፣ (Checklist) ያቃለ መጠይቅና የፅሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት በሥራ ላይ ውለዋል። እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተደጋጋፊነት ያላቸው በመሆናቸወ ለጥናቱ ተፈላጊውን አስተማማኝ መረጃ ያስገኛሉ ተብሎ ይታመናል።

### 3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በዚህ ጥናት የክፍል ውስጥ ምልከታ እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ተደርጎ የተወሰደ ሲሆን እያንዳንዱን ተጠኚ መምህር ለመመልከት ሲባል ምልከታው በሁለት ዙሮች ተከናውኗል። የክፍል ምልከታው በዋና የመረጃ መሠብሠቢያነት ሊመረጥ የቻለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በቀጥታ የሚያሣይ በመሆኑ ነው። የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፁም Dornyei (2001) ባቀረበው 'Checklist' መሠረት የተነሣሶት ስልትን የሚያመለክቱ ነጥቦች በዝርዝር ተዘጋጅተው ቀርበዋል። በመሆኑም በምልከታው የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታና አደረጃጀት፣ መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የመምህሩን የተነሳሶት ስልት አተገባበር እና የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚመረምሩ ጥያቄዎች በመቆጣጠሪያ ቅፁ ላይ ሰፍረዋል። ጥያቄዎቹም «አዎ» ወይም «አይደለም» የሚሉ አማራጭ መልሶችን ይዘዋል። በተጨማሪም

ተመልካቾቹ አስተያየቶችን እንዲያሰፍሩ እድል የሚሰጡ ጥያቄዎች በምልከታ መከታተያ ቅፁ ላይ ተካተዋል፡፡ የመቆጣሪያ ቅፁ በሁለት «አማርኛን ማስተማር» ክፍለ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ከታየ በኋላ በአጥኝዋ አማካሪ ተገምግሞና አስተያየት ተሰጥቶበት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ ከምልከታው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ ከአጥኝዋ በተጨማሪ አንድ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህርና አንድ በእንግሊዘኛ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህርት ምልከታው በሚካሄድባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተገኝተው የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፁን በመሙላት በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ አጥኚዋም በክፍል ምልከታው ወቅት መረጃው አስተማማኝ እንዲሆን በማሰብ በመቅረፀ-ድምፅ በመታገዝ ምልከታውን አካሂዳለች፡፡

### 3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት የፅሁፍ መጠይቅ ከምልከታው የተገኘውን ውጤት ለማጠናከር በአጋዥነት የቀረበ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን የተመረጠበትም ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ማሰባሰብ የሚያስችል በመሆኑና መምህራኑ በየጊዜው የሚጠቀሙባቸው የተነሳሶት ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ ሊጠቁም የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ መጠይቁ ተዘጋጅቶ የቀረበው በናሙናነት ለተመረጡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ነው፡፡ አዘገጃጀቱም የDornyei (2001) ሀሣብን መሠረት ያደረገ ሲሆን በመጠይቁ የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታን የመመምህሩ የክፍል ውስጥ የተነሳሶት ስልት አተገባበርን የሚያወሱ ሠላሣ አንድ ዝግ ጥያቄዎች የሊከርት እስኬልን መሰረት አድርገው ቀርበዋል፡፡ አቀራረቡም በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ መወሰን ያስቸግረኛል፣ አልስማማም እና ምንም አልስማማም የሚሉ አማራጮችን በማስፈር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የንሞና ተማሪዎቹ አስተያየታቸውን የሚሰጡበት ሦስት ክፍት ጥያቄዎች በፅሁፍ መጠይቁ ላይ ተካተዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ በሁለተ «አማርኛን ማስተማር» ሁለተኛ ዲግር ባላቸው መምህራን ታይቶ በአጥኝዋ አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶበት ከተስተካከለ በኋላ በስራ ላይ ውሏል፡፡

### 3.2.3. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቁ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙት ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ አላማውም መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በቋንቋ ትምህርቱ ለማነቃቃት የሚጠ

ቀሙባቸውን ስልቶች ለመለየትና ስልቶቹ እንዳይተገበሩ እንቅፋት የሆኑባቸውን ተላውጦዎች በመለየት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በቃለ-መጠይቁም የመምህራኑ ጳራዊ መግለጫ፣ መምህራንን ምን አይነት የተነሳሶት ስልቶችን በምን አይነት መንገድ እንደሚተገብሯቸው እንዲሁም የተማሪዎቻቸው የተነሳሶት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ የሚያውሱ ጥያቄዎች በዝርዝር ተካተዋል፡፡ ከቃለ-መጠይቁ የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ በመቅረፀ ድምፅ አጋዥነት መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት ተከናውኗል፡፡ የቃለ መጠይቁም እንደ ሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች "አማርኛን በማስተማር ሥነ ዘዴ" ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ታይቶ በአጥኚዋ አማካሪ ከተገመገመ በኋላ በተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 3.3. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በአዳማ ልዩ ዞን በአንድ የመንግሥትና በሶስት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የንሞና ተማሪዎች ነው፡፡ የመረጃ አሰባሰቡም ሂደት ለአራት ሳምንታት ያህል የተካሄደ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚዋ በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚያስተምሩበትን የክፍል ምድብና የክፍለ ጊዜ ድልድልን በመመዝገብ፣ የተደራረቡ ክፍለ ጊዜያትን ለይቶ በማወቅ፣ የክፍል ምልከታውን ለማካሄድ አመቺ የሆኑት ክፍለ ጊዚያት ተመርጠዋል፡፡

በዚህም መሠረት በክፍል ምልከታው የመቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ የሠፈሩት የመገምገሚያ ነጥቦች ለሁለቱ ረዳት ተመልካቾች በአጥኚዋ አማካኝነት ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ በተመረጡት ምድቦች የመማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታው በሁለት ዙር ተከናውኗል፡፡ በዚህም ተጠኚ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ለማነቃቃት የተጠቀሙበትን የተነሣሶት ስልትና አተገባበሩን ለማየት ተሞክሮአል፡፡

ከዚህም ሌላ ለመረጃ መሠብሠቢያነት የተዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ከየትምህርት ቤቱ ለተመረጡት ተተኳሪ ተማሪዎች ተበትኖ እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ የአሞላሉም ሂደት በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩት ተተኳሪዎች የትምህርት ሠአታቸውን በማይነካ ሁኔታ በየትምህርት ቤታቸው እንዲሠባሠቡ በማድረግ የመጠይቁ አሞላል ተገልፆላቸው መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ በተጨማሪም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ

ለሚያስተምሩ የዘነጠኛ ክፍል ተተኳሪ መምህራን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ቃለ ምልልሳቸውም በመቅረፀ-ድምፅ ተመዝግቦ ወደ ፅሑፍ ተቀይሯል፡፡

ከክፍል ምልከታው የተገኙት ውጤቶችም በአጥኝዋና በረዳት ተመልካቾቹ ከታዩ በኋላ ልዩነት የተፈጠሩባቸው ነጥቦች ተለይተው ከሦስቱ ተመልካቾች ሁለቱ የተስማሙባቸው ነጥቦች በውጤትነት ተይዘው ለትንታኔ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከየትምህርት ቤቶቹ መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት ተከናውኗል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከክፍል ምልከታው፣ ከፅሑፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎችን በማጠናቀር ይተነተናል፡፡ በምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፅና በመጠይቆቹ የቀረቡትን የጥያቄ ይዘቶች ከሚያስተላልፉት መልእክት አንፃር በማደራጀት የተገኙት ውጤቶች ለትንተና ቀርበዋል፡፡ ትንተናውም አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ይቀርባል፡፡ ከሁሉም የመረጃ ምንጮች የተገኙት መረጃዎች በመማር-ማስተማር ሂደት መምህራን የሚጠቀሙባቸውን የተነሳሶት ስልቶች በዝርዝር የሚያሳዩና አተገባበራቸውን የሚያመለክቱ በመሆናቸው የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረዋል፡፡ በዚም መሠረት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ከተመረጡት ተጠኝዎች የተገኙት ውጤቶች በንፅፅር ተተንትነዋል፡፡ አተናተናቸውም በክፍል ምልከታው የተገኙት ውጤቶች በድግግሞሽ መጠናቸው ሲገለፁ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኙት ውጤቶች ደግሞ በጣም 'እስማማለሁ፡ እስማማለሁ' የሚሉትን አወንታዊ ምላሾች በአንድነት በማጣመር እንዲሁም 'አልስማማም፣ ምንም አልስማማም' የሚሉትን አሉታዊ ምላሾች በአንድነት በማቀናጀት በፐርሠንት ተሠልቶ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤቶች

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጡት መሣሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን ለጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከመንግሥትና ከግል ትምህርት ቤቶች የተገኙት ውጤቶች በመቶኛ ተሰልተውና የተግባር ድግግሞሽ መጠናቸው በቁጥር እየተገለፁ በገላጭ የምርምር ዘዴ አማካኝነት በንፅፅር ቀርበዋል፡፡

### 4.1 የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫና የመማሪያ ክፍሉ አደረጃጀት

ሠንጠረዥ አንድ፣ የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ

| ትምህርት ቤቶች | የመምህራን ዳራዊ መግለጫ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፆታ | ብዛት | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የሥራ/የአገልግሎት ዘመን |
| አዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | 2 | 35<br>37 | ቢ.ኤ<br>ዲፕሎማ | 12 ዓመት<br>15 ዓመት |
| | ሴ | 1 | 32 | ቢ.ኤ | 10 ዓመት |
| | ድ | 3 | - | | - |
| አዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | 1 | 30 | ዲፕሎማ | 5 ዓመት |
| | ሴ | | - | | - |
| | ድ | 1 | - | | - |
| ሆሊ. ኤንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | 1 | 27 | ቢ..ኤ | 4 ዓመት |
| | ሴ | | - | | - |
| | ድ | 1 | - | | - |
| አዳማ ፀሐይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | 1 | 28 | ቢ..ኤ | 6 ዓመት |
| | ሴ | | - | | - |
| | ድ | 1 | - | | - |

ከላይ በሠንጠረገፑ እንደተገለፀው፣ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የተጠኚ መምህራን ቁጥር ስድስት ሲሆን ከመንግሥት ትምህርት ቤት የተገኙት ሁለት ወንድና አንድ ሴት፣ ከግል የተገኙት ደግሞ ሦስት ወንዶች ናቸው፡፡ በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት መምህራን መጠነኛ የእድሜ ልዩነት የሚታይባቸው ሲሆን በትምህርት ደረጃቸው ግን ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡

የተጠኚ መምህራንን የአገልግሎት ዘመን ስንመለከት በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉት አነስተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን ዳራ ሲታይ በእድሜና በአገልግሎት ዘመናቸው መጠነኛ የሆነ ልዩነት ቢኖራቸውም በትምህርት ደረጃቸው ተመጣጣኝ እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የተጠኚ ተማሪዎችን ዳራ ከፅሁፍ መጠይቁ ምላሽ ለማረጋገጥ እንደተቻለው፣ በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙት ተማሪዎች 51 ፐርሰንት ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ 49 ፐርሰንት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ከግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተወሠዱት የናሙና ተማሪዎች መካከል ደግሞ 50% ወንዶች ሲሆኑ 50 ፐርሰንት ደግሞ ሴቶች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሠረት ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች የተወሠዱት የንሞና ተማሪዎች በፆታ ቁጥራቸው ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙት ተጠኝ ተማሪዎች ከ 16-18 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ከ 50% በላይ ሲሆኑ በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ደግሞ ከ 54 ፐርሰንት በላይ የሚሆኑት ከ 13-15 እድሜ ያላቸው መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በናሙናነት ከተመረጡት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች 45 ፐርሰንት ያህሉ አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው መሆኑ ከመጠይቁ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡በግል

ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት ተጠኝ ተማሪዎች 63 ፐርሰንቱ አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ሲሆን የቀሩት ደግሞ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑ ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ ሁለት፣ የመምህራንን ፍላጎት፣አገልግሎትና ክፍያ በሚመለከት የቀረበ መግለጫ

| ትምህርት ቤቶች | | የመምህራን ብዛት | የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት | በሳምንት የሚያስተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት | አጫጭር ስልጠና ያገኛሉ | በቂ ክፍያ ያገኛሉ | ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመንግስት ትምህርት ቤት | አዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | አማርኛ | 24 | የለም | የለም | ከፍተኛ |
| | | 1 | አማርኛ | 21 | የለም | የለም | ከፍተኛ |
| | | 1 | አማርኛ | 24 | የለም | የለም | ከፍተኛ |
| የግል ትምህርት ቤቶች | አዋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | አማርኛ | 24 | የለም | አዎ | ከፍተኛ |
| | ሁሊ ኢንጅልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | አማርኛ | 24 | የለም | አዎ | ከፍተኛ |
| | አዳማ ፀሐይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | አማርኛ | 25 | የለም | አዎ | ከፍተኛ |

ከላይ ከሠንጠረዡ ለማየት እንደተቻለው፣ በመንግሥትም ሆነ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል ተጠኚ መምህራን አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ሲሆኑ በሳምንት ያላቸው የክፍለ ጊዜ ብዛት ተመሣሣይ መሆኑ ተረጋግጧል። በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ተጠኚዎች ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም ሙያቸውን ለማሻሻል የሚያግዙ አጫጭር ሥልጠናዎችን አግኝተው እንደማያውቁ ከምላሻቸው ለማወቅ ተችሏል። በሌላ በኩል በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚዎች ለሙያቸው በቂ የሆነ ክፍያ እንደማያገኙ ሲገልፁ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት ተጠኚ መምህራን ግን በሙያቸው የተሻለ ክፍያ እንደሚከፈላቸው ገልፀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ተጠኚዎቹ ከኃላፊዎቻቸው ዘንድ አድናቆትን እንደሚያገኙና በዓመቱ መጨረሻ ለማነቃቂያ የሚሆን ተጨማሪ ክፍያ እንደሚሰጣቸው ከቃለ መጠይቁ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከሦስቱ የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ትምህርት ቤት የሚገኙት ተጠኚ መምህር የመጓጓዣ አገልግሎት ከትምህርት ቤታቸው እንደሚቀርብላቸው ከቃለ መጠይቁ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተጠኚዎች በሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት የክፍለ ጊዜ ብዛት ባላቸው የማስተማር ፍላጎት እንዲሁም የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ባለማግኘታቸው ምስስሉሽ የሚታይባቸው ሲሆን በሚያገኙት ክፍያና ጥቅማጥቅም በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት ተጠኚዎች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ ሦስት፣ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና አደረጃጀት**

| ተራ ቁጥር | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ | አማራጭ መልሶች | ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግስት በቁጥር | የግል በቁጥር |
| 2.1 | የመማሪያ ክፍሉ በቂ ስፋት አለው? | አዎ | - | 6 |
| | | አይደለም | 6 | - |
| 2.2 | በመማሪያ ክፍሉ የሚገኙ መቀመጫዎች ለተማሪዎች በቂ ናቸው? | አዎ | - | 6 |
| | | አይደለም | 6 | - |
| 2.3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህና የተጠበቀ ነው? | አዎ | - | 6 |
| | | አይደለም | 6 | - |
| 2.4 | ንፁህ አየር በመማሪያ ክፍሉ መስኮት ይገባል? | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |
| 2.5 | በመማሪያ ክፍሉ የሚገኘው ሠሌዳ ለሁሉም በሚታይ መልኩ ተቀምጧል? | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው፣በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙት የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎቹ ቁጥር ጋር ሲነፃፀሩ በቂ ስፋት የሌላቸው ሲሆን በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎቹ ቁጥር ጋር ሲነፃፀሩ በአብዛኛው በቂ ስፋት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በክፍል ምልከታው እንደተረጋገጠው፣ በግል ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ 54 የሚደርሱ ተማሪዎች በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ

የሚማሩ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ግን እስከ 77 የሚደርሱ ተማሪዎች በመገኘታቸው ነው ከዚህም የተነሳ በመንግስት ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት መቀመጫዎች አነስተኛ ሲሆኑ ችለዋል በተጨማሪም የመማሪያ ክፍሎች ንፅህና ያልተጠበቀ መሆኑ በምልከታው ተረጋግጧል።

በአንፃሩ በግል ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት መቀመጫዎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀሩ በቂ ሲሆኑ የክፍሎቹም ንፅሕና የተጠበቀ ነው ይሁን እንጂ በመማሪያ ክፍሎቹ መስኮት ንፁህ አየር ቢገባም እንኳን በመንግሥት ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ብዛት ያላቸው በመሆኑ መተፋፈግና መጨናነቅ መኖሩ በክፍል ምልከታው ወቅት ሊረጋገጥ ችሏል። በአንፃሩ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት የጥቁር ሰሌዳዎች ለተማሪዎች በሚታይ መልኩ በተገቢው ስፍራ ተቀምጦ ይታያል። በዚህም መሠረት በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙት የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት ይልቅ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት የተሻለ መሆኑ ታውቋል።

### 4.2 መምህሩ የሚጠቀምባችው የተነሶት ሥልቶችና አተገባበር በሚመለከት የቀረበ ትንተና

ሠንጠረዝ አራት፣ የመምህሩን እርእያነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግስት በቁጥር | የግል በቁጥር |
| 3.1 | መምህሩ/ሯ በሠዓቱ ወደ መማሪያ ክፍሉ ገብተዋል? | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | - |
| 3.2 | መምህሩ/ሯ የደንብ ልብሣቸውን ለብሠዋል? | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደታየው፣በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ተጠኚ መምህራን የደንብ ልብሣቸውን ለብሠው በሠዓቱ በማስተማሪያ ክፍላቸው ውስጥ የተገኙ ሲሆን በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን ሁሉም የደንብ ልብሣቸውን ለብሰው ቢገኙም ወደ ማስተማሪያ ክፍላቸው በሠዓቱ ሲገቡ የታዩት በአራት ጊዜ ድግግሞሽ ብቻ ነበር።

አንድ መምህር የመማር-ማስተማር ሂደቱ የተቃና እንዲሆንለት ጥሩ የመምህር ባሕሪን ሊላበስ ይገባል፡፡ መምህሩ በወቅቱ በማስተማሪያ ክፍሉ ተገኝቶ ሥራውን በትጋት እያከናወነ ለተማሪቹ አርአያ ከሆነ የተማሪዎቹ የመማር ፍላጎት እየጨመረ ሊሄድ ይችላል፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪው መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር አመቺ መንገድ ይሆናል፡፡

### 4.2.1 መልካም የሆነ የመምህር - ተማሪ ግንኙነት መፍጠር

በክፍል ውስጥ በሚደረገው በመምህር-ተማሪ ተራክቦ መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ሡብለ ወንጌል (2007) Walodkowski (1986)ን ጠቅሰው እንደገለፁት፣መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ማሣየት ከተማሪዎቻቸው ለሚነሡ ጥያቄዎች በትህትና መልስ መስጠት የተማሪዎቻቸውን ስም ለይተው በመጥራት ማሣተፍና ስራቸውን መከታተል በመምህርና ተማሪ መካከል ያለውን ግንኙነት አዎንታዊ ጎን እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በአንፃሩ Good and Brophy (1994: 215) እንደገለፁት፣የመምህር-ተማሪ ተራክቦ አሉታዊ ከሆነ ተማሪዎቹ ለጭንቀትና የትምህርት ፍላጎት ማጣት ስለሚዳረጉ መሠረታዊ ተነሳሽነትን መፍጠር አዳጋች ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በተጠኚ ትምህርት ቤቶቹ ከተካሄደው የክፍል ምልከታ የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ አምስት፣ የመምህር- ተማሪን ግንኙነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 3.3 | የአማርኛ መምህሩ/ቷ ለተማሪዎቻቸው ትሕትና ያሣያሉ? | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |
| 3.4 | የአማርኛ መምህሩ/ቷ ለተማሪዎቻቸው ፈገግታን ያሳያሉ? | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | - |
| 3.5 | የአማርኛ መምህሩ/ቷ የቁጡነት ባሕሪ ይታይባቸዋል? | አዎ | 1 | - |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 3.6 | የአማርኛ መምህሩ/ቷ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እየተንቀሣቀሡ ተማሪዎቻቸውን ይከታተላሉ? | አዎ | 2 | 5 |
| | | አይደለም | 4 | 1 |
| 3.7 | የአማርኛ መምህሩ/ቷ ተማሪዎቻቸው ጥያቄ ሲጠይቋቸው ለመመለስ ፈቃደኛ ናቸው? | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |

ከላይ በሠንጠረገፎ እንደተገለፀው፣በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት ተጠኚ መምህራን ፈገግታን ትህትናንና ፈቃደኝነትን ለተማሪዎቻቸው በማሣየት መልካም የመምህር-ተማሪ ግንኙነት ሲፈጥሩ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙት ተጠኚ መምህራን ምልከታው በተካሄደባቸው ቀናት ተግባራቱን በአብዛኛው ሲፈፅሙ አልታዩም። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ እየተንቀሣቀሱ ተማሪዎችን የመከታተል ተግባር በግል ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ የተከናወነ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት ግን ተግባሩ በአራት ጊዜ ድግግሞሽ ታይቷል ከዚህ መረዳት የሚቻለው በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥሩ የሆነ የመምህር-ተማሪ ግንኙነትት መኖሩን ሲሆን በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንየመምህር ተማሪ ግንኙነቱ አሉታዊ ጎን እንደሚታይበት ነው። ይህን የመምህር ተማሪ ግንኙነት ለተማሪዎች በቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ ስድስት፣ የመምህር- ተማሪን ግንኙነት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | ጥያቄዎች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በስሜ ጠርተው መልስ እንድመልስ ያደርጉኛል። | | | | | | | | |
| 3.8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በፈገግታ ጥያቄዎቼን ይመልሱልኛል። | | | | | | | | |
| 3.14 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የክፍሉን ሁኔታ እንዳስፈላጊነቱ ይቆጣጠራሉ። | | | | | | | | |
| 3.15 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የተሳሳተ መልስ ስመልስ በትሕትና እርማት ይሰጡኛል። | | | | | | | | |
| | አማራጭ መልሶች | የመላሽ ብዛት | | | | | | | |
| | | የመንግስት/አዳማ/ | | የግል /አዋሽ/ | | የግል /ሆሊ እንጂልስ/ | | የግል /አዳማ ፀሀይ/ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 3.7 | በጣም እስማማለሁ | 40 | 22.3 | 8 | 26.7 | 4 | 13.3 | 11 | 36.7 |
| | እስማማለሁ | 61 | 33.8 | 13 | 43.3 | 16 | 53.3 | 9 | 30 |
| | ለመወሰን ያስቸግራል | 33 | 18.3 | 1 | 3.3 | 2 | 6.6 | 1 | 3.3 |
| | አልስማማም | 24 | 13.3 | 7 | 23.3 | 6 | 20 | 7 | 23.3 |
| | ምንም አልስማማም | 22 | 12.3 | 1 | 3.3 | 2 | 6.7 | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 3.8 | በጣም እስማማለሁ | 30 | 16.7 | 10 | 33.3 | 8 | 26.6 | 9 | 30 |
| | እስማማለሁ | 47 | 26.2 | 13 | 43.3 | 14 | 46.7 | 15 | 50 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 34 | 18.8 | 5 | 16.7 | 2 | 6.7 | 4 | 13.3 |
| | አልስማማም | 52 | 28.8 | 2 | 6.7 | 5 | 16.7 | 2 | 6.7 |
| | ምንም አልስማማም | 17 | 9.5 | - | - | 1 | 3.3 | - | - |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 3.14 | በጣም እስማማለሁ | 26 | 14.4 | 14 | 46.7 | 9 | 30 | 10 | 33.4 |
| | እስማማለሁ | 75 | 41.6 | 12 | 40 | 8 | 26.6 | 12 | 40 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 31 | 17.3 | 0 | 0 | 5 | 16.7 | 4 | 13.3 |
| | አልስማማም | 17 | 9.4 | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 |
| | ምንም አልስማማም | 31 | 17.3 | - | - | 4 | 13.3 | - | - |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 3.15 | በጣም እስማማለሁ | 48 | 26.7 | 8 | 26.7 | 10 | 33.3 | 8 | 26.7 |
| | እስማማለሁ | 88 | 48.8 | 16 | 53.3 | 13 | 43.4 | 11 | 36.6 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 14 | 7.7 | 4 | 13.3 | 3 | 10 | 2 | 6.6 |
| | አልስማማም | 20 | 11.2 | 2 | 6.7 | 6 | 33.3 | 6 | 20 |
| | ምንም አልስማማም | 5 | 2.7 | 0 | - | - | - | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | 5 | 2.8 | 0 | - | - | - | 1 | 3.3 |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው፣ በመምህር-ተማሪ መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙት መምህራን ፈገግታን እንደሚያሳዩ 76.6% ያህሉ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ደግሞ 43% ያህሉ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን ይልቅ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተሻለ አቀራረብ እንደሚያደርጉ ነው። በሌላ በኩል የተማሪዎቻቸውን ሥም በመጥራት መልስ እንደሚያስመልሷቸው 67.7% የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ከመንግሥት ትምህርት ቤት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት 56% ያህሉ ብቻ ናቸው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙት መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስም በመጥራት ለማግባባት የሚጥሩ መሆናቸውን ነው። መምህራን በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን ይቆጣጠራሉ ለሚለው ጥያቄ 72.2% ያህል ከግል ትምህርት ቤት አዎንታዊ ምላሽ ሲገኝ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 56% ያህል አዎንታዊ ምላሽ ተገኝቷል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲሰጡ በትህትና እርማትን የሚሰጡ መምህራን መኖራቸውን ከምላሹ ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት ከግል ትምህርት ቤት 73.1% ያህል አዎንታዊ ምላሽ ሲገኝ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 75.5% አዎንታዊ ምላሽ ሊገኝ ችሏል። ከፅሁፍ መጠይቁ ምላሽ ለማወቅ የሚቻለው በግልም ሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ትህትናን በማሳየት የመማር-ማስተማሩን ሂደት እንደሚያከናውኑ ነው። ይሁንና በክፍል ምልከታው ወቅት በትህትና ለተማሪዎቻቸው መልሶችን የመስጠት ተግባር በመንግስት ትምህርት ቤት በከፊል ሲጓደል ታይቷል። በመሆኑም በምልከታው ውጤትና በመጠይቁ ውጤት መካከል ተቃርኖ ሊታይ ችሏል።

### 4.2.2. የመማሪያ ክፍሉን አስደሳችና አጋዥ ስለ ማድርግ በሚመለከት የቀረበ ትንተና

ሠንጠረዥ ስባት፣ አስደሳች የመማሪያ ክፍል ሁኔታን መፍጠርን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | የቀረበው ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 3.7 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ በየትምህርቱ ጣልቃ አዝናኝ ቀልዶችን ያቀርባሉ | አዎ | 2 | 4 |
| | | አይደለም | 4 | 2 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው በትምህርቱ ጣልቃ ቀልድን እያስገቡ ትምህርቱን አዝናኝ ለማድረግ ጥረት የማድረግ ሂደት የተከናወነው በግል ትምህርት ቤቶች አራት ጊዜ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤቶች ግን ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ከላይ በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው ከፍ እያለ እንዲሄድ ማነቃቂያና ወደትምህርቱ ይዘት በሚያደርሱና በሚያዝናኑ ቀልዶች መምህሩ መጠቀም ይጠበቅበታል ይህንን ተግባር ለማረጋገጥ ከዕሁፍ መጠይቁ የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው 39 ፐርሰንት ያህሉ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 61ፐርሰንት የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ትምህርቱን አዝናኝ ለማድረግ በተቻለ ሁኔታ ጥረት የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው፡፡

ሠንጠረዥ ስምንት፣ በቡድንና በጥንድ መደራጀትን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራራ ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግስት | የግል |
| 4.1 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎችን በቡድን እንዲደራጁ አድርገዋል | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |
| 4.2 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በጥንድ እንዲደራጁ አድርገዋል | አዎ | 1 | 3 |
| | | አይደለም | 5 | 3 |
| 4.3 | በቡድን ሥራ ወቅት የቡድን መሪ ነበር | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 4.4 | በቡድን ሥራ ወቅት የሚሳተፉት ሁሉም ናቸው | አዎ | - | 1 |
| | | አይደለም | 6 | 5 |

ከላይ በሠንጠረገፉ ለማየት እንደተሞከረው፣ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ከመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ መምህራን በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸውን በቡድንና በጥንድ ሲያደራጁ ታይተዋል። በመማር-ማስተማሩ ሂደት አጋዥ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታን ለመፍጠር የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እርስ በርስ እንዲረዳዱና እንዲተጋገዙ በማድረግ ንቁ የሆነ የተማሪ-ለተማሪ ተራክቦ መፍጠር ይችላል (Dornyei ፣ 2001)። ይሁንና በመንግሥት ትምህርት ቤት የታየው በቡድንና በጥንድ ተማሪዎችን የማደራጀት ተግባር ከግል ትምህርት ቤት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም በመንግሥት ትምህርት ቤት በቡድን የማደራጀት ተግባር አንድ ጊዜ ሲፈፀም በግል ትምህርት ቤት ደግሞ በሁለት ጊዜ ድግግሞሽ መተግበሩ በክፍል ምልከታው ተረጋግጧል። የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በጥንድ በማደራጀት እርስ በእርስ ሃሳብ እንዲለዋወጡ የማድረግ ተግባር ምልከታ በተካሄደባቸው ቀናት አንድ ጊዜ ብቻ ሲተገበር በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ሶስት ጊዜ ተግባራዊ ሲሆን ታይቷል። በመሆኑም የግል ትምህርት ቤት በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸውን በቡድንና በጥንድ እንደሚያደራጁ መገንዘብ ይቻላል በሌላ በኩል በቡድን ሥራ ወቅት የቡድን መሪ መርጦ በራስ የመተማመንን ብቃት ለማጎልበት በሁለቱም ትምህርትቤቶች አልተሞከረም።

በቡድንና በጥንድ መደራጀትን በሚመለከት ከተማሪዎች የተገኘው የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ እንደሚያስረዳው በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቡድን የሚያሳትፉት 22 ፐርሰንት ያህል ሲሆን በግል ትምህርት ቤት ደግሞ 58 ፐርሰንት ያህል ነው በተጨማሪም በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን 46 ፐርሰንት ያህል በጥንድ አደራጅተው እንዲሳተፉ ሲያደርጉ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ደግሞ 63 ፐርሰንት ያህል ተማሪዎቻቸውን በጥንድ እንደሚያሳትፉ ከተማሪዎች የተገኘው የመጠይቅ ምላሽ ያሳያል። ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ በሰጡት ምላሽ ለማረጋገጥ እንደተቻለው፣ የቡድን መሪ ወይም ፀሐፊ በመሆን ተነሳሽነትን ከፍ የማድረግ ተግባር በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የማይተገበር መሆኑን ነው ስለሆነም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ምስስሎሽ ይታያል።

በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የቡድን ሥራን ለማከናወን የሚቸገሩባቸውን ነጥቦች በቃለ መጠይቁ ሲያስረዱ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ወንበሮች ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ መሆኑ የተማሪዎቹ ቁጥር መብዛትና በክፍል ውስጥ ጫጫታ እንዳይፈጠር በመስጋት መሆኑን ገለፀዋል። የቡድን ሥራን በሚመለከት ምሁራን እንዳብራሩት ጥሩ የሆነ የቡድን ጥምርታ መኖር በተማሪዎች መካከል እርስበርስ የመተጋገዝና የመተባበር መንፈስ በማምጣት እያንዳንዱ ለቡድኑ በቁርጠኝነት እንዲሠራና የትምህርት ፍላጎቱን እያጎለበተ እንዲሄድ ይረዳል። ይሁንና የቡድን ሥራ ክንውን በመንግስት ትምህርት ቤት ዝቅተኛ መሆኑ ከምልከታውና ከመጠይቆቹ ውጤቶች ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፣ ተማሪ ተኮር እና መምህር-መር ዘዴን መጠቀም በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | ጥያቄዎች | አማራጭ | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 4.5 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ የውይይት መንፈስ እንዲኖር አድርገዋል | አዎ | 1 | 5 |
| | | አይደለም | 5 | 1 |
| 4.6 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ እንዲኖር አድርገዋል | አዎ | 1 | 3 |
| | | አይደለም | 5 | 3 |
| 4.14 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪ ተኮር ዘዴን ተጠቅመው አስተምረዋል | አዎ | 2 | 5 |
| | | አይደለም | 4 | 1 |
| 4.15 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ መምህር-መር ዘዴን ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምረዋል | አዎ | 4 | 1 |
| | | አይደለም | 2 | 5 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመላክተው፣ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በቡድን እና በጥንድ በማሳተፍ በአምስት ጊዜ ድግግሞሽ እንዲወያዩና በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ በመካከላቸው የእርስበርስ የውድድር መንፈስ እንዲኖር በማመቻቸት ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ሲያደርጉ በመንግሥት ትምህርት ቤት ግን ተግባሩን ሁለት ጊዜ ብቻ ማከናወናቸው በምልከታው ተረጋግጧል የተማሪዎች መጠይቅ ምላሽም ይህንን አጠናክሯል። በሌላ በኩል ከክፍል ምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በአራት ጊዜ ድግግሞሽ መምህር - መር ዘዴን ተጠቅመው የቋንቋ

ትምህርቱን ያስተማሩ ሲሆን በግል ትምህር ቤት የሚገኙ መምህራን ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ የመምህር- መር ዘዴን ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምረዋል። በመሆኑም በመንግስት ትምህርት ቤት ተግባራዊ የሆነው የማስተማሪያ ዘዴ መምህር- መር መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

ሠንጠረዥ አስር፣ ተማሪዎችን በተናጥል የማሳተፍ ተግባርን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራራ ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 4.10 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲፅፉ ተማሪዎች አድርገዋል | አዎ | 2 | 3 |
| | | አይደለም | 4 | 3 |
| 4.11 | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በተራ በተራ ጥያቄ በመመለስ እንዲሳተፉ እድል ሰጥተዋል | አዎ | 3 | 6 |
| | | አይደለም | 3 | 0 |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተገለፀው፣ በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን ይልቅ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቻቸው ከመቀመጫቸው እየተነሱ በጥቁር ሰሌዳው ላይ መልሶቻቸውን እንዲፅፉ አድርገዋል። ይህም ተግባር በግል ትምህርት ቤት በአራት ግዜ የድግግሞሽ መጠን ሲታይ በመንግሥት ትምህርት ቤት ግን ሁለት ጊዜ ብቻ ታይቷል። በተጨማሪም ተማሪዎቻቸው ተራ በተራ እንዲሳተፉ እድሉን የመስጠት ተግባር በመንግስት ትምህርት ቤት በከፊል የተፈፀመ ሲሆን በግል ትምህርት ቤት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሆኖአል። ይህንን ተግባር በሚመለከት ከጽሑፍ መጠይቁ የሚከተለው ምላሽ ተገኝቶአል።

በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ተራ በተራ እንዲሳተፉ እድል የሚሰጧቸው መሆኑን 64% ያህሉ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በግል ትምህርት ቤት ደግሞ 75.6% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው ከመንግስት ትምህርት ቤት ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ተራ በተራ የመሳተፍ እድልን በመስጠት ተግባራዊ

እንደሚያደርጉ ነው። ይህንን ተግባር በተመለከተ የግል ትምህርት ቤት መምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ምላሻቸውን ሲሰጡ እንደሚከተለው ብለዋል።

በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸው ከ 54 ያልበለጠ በመሆኑ ተራ በተራ ለማሳተፍ አመቺ መሆኑን ሲገልፁ በአንፃሩ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማሳተፍ ፍቃደኝነት የሚታይባቸው ተማሪዎች ጥቂት በመሆናቸው ተሳትፎው ዝቅተኛ መሆኑን ከቃለመጠይቁ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህሩ የፈጠራ ችሎታቸውን እንደሚያበረታቱላቸው አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት የገለፁት ከመንግስት ትምህርት ቤትና ከግል ትምህርት ቤት 51 51ፐርሰንት የሚሆኑት ሲሆኑ አሉታዊ ምላሻቸውን የሰጡት ደግሞ 18.3ፐርሰንት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና 21 ፐርሰንት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ናቸው ለዚህ ሃሳብ 23.8 ፐርሰንት የሚሆኑ የመንግሥትና 18.6% የሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚል አማካይ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎቹ ያላቸውን የፈጠራ ችሎታ የቋንቋ መምህራኑ በክፊል እንደሚያበረታቱላቸው ነው። ይህ ሁኔታ በመንግሥትም ሆነ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ መሆኑ ከመጠይቁ ውጤት ሊረጋገጥ ችሏል።

### 4.2.3 ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና

ምጋቤ ምላሽ በመማር - ማስተማሩ ሒደት ተማሪዎች አንድን ተግባር ከፈፀሙ ወይም ሐሳባቸውን ከገለፁ በኋላ ከመምህሩ የሚቀርብ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ ተሞክሯል። ይህም ምላሽ የማበረታቻ ቃላትን፣ የምስጋና ቃላትን፣ የነቀፌታ ቃላትን፣ ጭብጨባንና ሽልማትን ያጠቃልላል። እነዚህ ምጋቤ ምላሾች በቋንቋ መምህሩ መተግበራቸውን ከምልከታውና ከመ ጠይቁ ውጤቶች እንደሚከተለው ለማየት ይሞከራል።

ሠንጠረዥ አሥራ አንድ፣ ለተማሪዎች የተሰጡ ምጋቤ ምላሾችን በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተራ ቁጥር | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግስት | የግል |
| 3.9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ የማበረታቻ ቃላትን ይጠቀማሉ | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |
| 3.10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ የምስጋና ቃላትን ይጠቀማሉ | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |
| 3.11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ የነቀፌታ ቃላትን ይጠቀማሉ | አዎ | - | - |
| | | አይደለም | 6 | 6 |
| 3.12 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ጥያቄ ጠይቀው ከተማሪዎቻቸው መልስ ሲያጡ የነቀፌታ ቃላትን ይጠቀማሉ | አዎ | 1 | - |
| | | አይደለም | 5 | 6 |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተቻለው፣ በመንግሥትም ሆነ በግል ትምህርትቤቶች የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥያቄ ሲጠይቋቸው የማበረታቻ ቃላትን በሦስት በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ በመጠቀማቸው ምስስሎሽ ታይቶባቸዋል። ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን የምስጋና ቃላትን ተጠቅመዋል ይሁንና በመንግስት ትምህርት ቤት የመስጋና ቃላትን የመጠቀም ተግባር በአንድ የክፍል ምልከታ ወቅት ሳይታይ በመቅረቱ መምህራኑ ተግባሩን ሲያጓድሉ ታይተዋል።

በሌላ በኩል በመንግሥትም ሆነ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለተጠየቁት ጥያቄ የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ በነቀፌታ ቃላት እንደማይጠቀሙ በክፍል ምልከታው ታይቷል። ይሁን እንጂ መምህራኑ ጥያቄ ጠይቀው ለጥያቄዎቻቸው መልስ ሲያጡ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህራን በአንድ የክፍል ምልከታ ወቅት “የዚህ ክፍል ተማሪዎች ሰነፎች ናቸው” የሚል የነቀፌታ ቃል መጠቀማቸውን ከምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል። መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡትን የማስጨብጨብና የሽልማት ምጋቤ ምላሾችን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረቡት የፅሁፍ መጠይቆች የሚከተሉት ምላሾች ተገኝተዋል።

በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ 23.3 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ እንደሚጨበጨብላቸው በመግለፅ አዎንታዊ ምላሻቸውን ሲሰጡ 56.1 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ የማይጨበጨብላቸው መሆኑን በመግለፅ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በግል ትምህርት ቤት የሚገኙት ተማሪዎች ደግሞ ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ 31 ፐርሰንት ያህሉ እንደሚጨበጨብላቸው በመግለፅ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 50.1 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ እንደማይጨበጨብላቸው በመግለጽ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በሌላ በኩል 28 ፐርሰንት የሚሆኑት የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሚሰጡን ሙከራዎች ጥሩ ውጤት ስናመጣ ከመምህሮቻችን ሽልማት እናገኛለን በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 51 ፐርሰንት የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም በግል ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ 11.5 ፐርሰንት የሚሆኑት ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ከመምህሮቻቸው ሽልማት እንደሚሰጣቸው ሲገልፁ 67 ፐርሰንት የሚሆኑት መላሾች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ይሁንና በክፍል ምልከታው ወቅት ለማየት እንደተቻለው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ትክክለኛ መልስ ለሚመልሱ ተማሪዎች ሲያስጨበጭቡም ሆነ ሲሸልሙ አልታዩም ለመምህራን በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚ መምህራን የክፍሉ ፀጥታ እንዳይታወክ በመስጋት ትክክለኛ መልስ ለሚመልሱ ተማሪዎች እንደማያስጨበጭቡ ሲገልፁ ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎችም ሽልመው እንደማያውቁ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ከጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ላይ የተገኘው አዎንታዊ ውጤት ከመምህራኑ የቃለመጠይቅ መልስ ተቃርኖ እንደሚያሳይ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከተገኘው ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በተማሪዎቹ የሥነ ሥርዓት መጓደል የተነሳ አንዳንድ የነቀፌታ ቃላትን እንደሚጠቀሙ ሲረጋገጥ በአንፃሩ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን

እንደ "በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ፣ በርታ፣ አመሰግናለሁ፣ አግኝተሸኛል፣ አንበሳ" የመሳሰሉየማበረታቻና የምስጋና ቃላትን በተስተምህሮቱ ወቅት እንደተጠቀሙ ከምልከታውና ከቃለመጠይቁ ምላሽ መገንዘብ ተችሏል።

### 4.2.4 የመርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም በሚመለከት የቀረበ ትንተና

የመማር-ማስተማሩ ሂደት ተፈላጊ የሆነውን ተነሳሽነት ለማሳደግ ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱ በመርጃ መሣሪያዎች ተጠቅሞ ማስተማር ነው። የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሲባል በመቅረፅ ድምፅ የተቀረፁ ንግግሮችን፣ የተለያዩ መፃሕፍትን፣ መፅሔቶችንና ጋዜጦችን መጠቀም ያካትታል በዚህም መሰረት በክፍል ምልከታውና በጽሑፍ መጠይቁ አማካኝነት የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ታይቷል።

**ሠንጠረዥ አሥራ ሁለት፣ የመምህሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 4.7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ከማስተማሪያ መፅሐፍ ሌላ በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ ተጠቅመው አስተምረዋል። | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |
| 4.8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ መቅረፀ-ድምፅ ተጠቅመው ትምህርቱን አስተምረዋል። | አዎ | - | 6 |
| | | አይደለም | - | 6 |
| 4.9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ሌሎች ጽሑፎችን በመረጃነት ተጠቅመው አስተምረዋል። | አዎ | 3 | 3 |
| | | አይደለም | 3 | 3 |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተቻለው፣ በመንግሥትም ሆነ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን መቅረፀ-ድምፅን ተጠቅመው እንዳላስተማሩ ከክፍል ምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል። ይሁንና ሌሎች" ሰዋስውን፣ ድርሰትን፣ እንቆቅልሽን፣ ቅኔን፣ ልብወለድን" የሚያወሱ ፅሁፎችን በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን በተስተምህሮቱ ወቅት በከፊል ተጠቅመው ሲያስተምሩ ታይተዋል።

በመሆኑም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መካከል ተመሳሳይ የሆነ የመረጃ መሳሪያ አጠቃቀም መኖሩን በምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስቸጋሪ የሆኑ ትግበራዎችን ግልፅና ቀላል፣ ሳቢና ተወዳጅ ለማድረግ እንደሚያግዙ ሰብለወንጌል(2007) Walodkowski (1986)'ን ጠቅሰው ገልፀዋል። ይህንንም ተግባር ከተማሪዎች ከተገኘው የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ለማረጋገጥ እንደተቻለው መምህራኑ መቅረፀ ድምጽን ተጠቅመው እንደማያስተምሩ 54% ያህል የሚሆኑት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲገልጹ በተመሳሳይ መልኩ 57.6% የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መምህሮቻቸው መቅረፀ ድምፅን ተጠቅመው እንደማያስተምሯቸው በምላሻቸው አረጋግጠዋል። የቀሩት 16% የሚሆኑት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና 14% የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መምህሮቻቸው መቅረፀ- ድምፅን በትምህርት መርጃ መሳሪያነት ተጠቅመው እንደሚያስተምሩዋቸው ገልፀዋል። ተጠኚ መምህራኑ እንደገለፁት ካለው የክፍለ ጊዜ ማነስ አኳያ መቅረፀ ድምፅን በትምህርት መርጃ መሳሪያነት ተጠቅመው እንደማያውቁ ማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል "ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ሌላ የተዘጋጁ ጽሁፎችን በትምህርት መርጃነት መምህሮቻችን ይጠቀማሉ" በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡን የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች 60% ሲሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ 72.2% ናቸው ከዚህም ውጤትና ከክፍል ምልከታው መረዳት የሚቻለው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ጽሑፎችን በትምህርት መርጃ መሳሪያነት መምህራኑ እንደሚጠቀሙ ነው ይህን ሁኔታ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው ምላሽም አጥናክሮታል።

### 4.2.5 የትምህርቱን ይዘት ተስማሚ በሆነ መንገድ ማቅረብ በሚመለከት የቀረበ ትንተና

የመማር-ማስተማሩ ሂደት አንዳንድ ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶችና ትግበራዎች ለምን ዓላማ እንደተዘጋጁ ግልፅ ላይሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ የትምህርቱን ይዘቶችና ክንውኖች ዓላማ ለተማሪዎቹ ማሳወቅ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው ተነሳሶት ከፍ እንዲል የትምህርቱን ይዘቶች ተስማሚ

በሆነ መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል። በመሆኑም የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የትምህርቱን ይዘቶች ምን ያህል ተስማሚ እንደሚያደርጉና አላማውንም ለተማሪዎቹ ምን ያህል እንደሚያሳውቅ ለተማሪዎች በቀረበ የፅሑፍ መጠይቅ ለማየት ተሞክሮአል

ሠንጠረዥ አሥራ ሦስት፣ የትምህርቱን አላማ ማሳወቅ በሚመለከት ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ እያንዳንዱን የትምህርት ክንውን አላማ ያሳውቁኛል። | | | | | | | | |
| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
| | | የመንግሥት /አዳማ/ | | የግል /አዋሽ/ | | የግል /ሆሊ.ኤንጅልስ/ | | የግል /አዳማ ፀሀይ/ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| | በጣም እስማማለሁ | 43 | 23.9 | 9 | 30 | 8 | 26.6 | 13 | 43.3 |
| | እስማማለሁ | 37 | 20.6 | 9 | 30 | 11 | 36.7 | 3 | 10 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 33 | 18.3 | 2 | 6.7 | 2 | 6.7 | 7 | 23.3 |
| | አልስማማም | 25 | 13.9 | 2 | 6.7 | 5 | 16.7 | 2 | 6.7 |
| | ምንም አልስማማም | 35 | 19.4 | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 | 5 | 16.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | 7 | 3.9 | 4 | 13.3 | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |

ከላይ ከሠንጠረገፉ ማየት እንደሚቻለው የቋንቋ መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የትምህርቱን ክንውን አላማ ያሳውቃሉ በማለት 44.5 ፐርሰንት የሚሆኑ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 59 ፐርሰንት የሚሆኑ አዎንታዊ ምላሽ ሠጥተዋል። በአንፃሩም አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ከመንግስት ትምህርት ቤት 33.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 24.4 ፐርሰንት የሚሆኑት ናቸው። ከዚህ የመጠየቅ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ከመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይልቅ በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የትምህርቱን ክንውን አላማ ለተማሪዎቻቸው እንደሚያሳውቁና ግልፅ እንደሚያደርጉ ነው።

ሠንጠረዥ አሥራ አራት፣ የትምህርቱን ይዘት ሳቢነት በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.12 | በአማርኛ ትምህርት ወቅት የሚቀርቡት ይዘቶተ በህይወት ልምዴ ከማውቃቸው ጋር ዝምድና አላቸው:: | | | | | | | | |
| 3.13 | በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉት ምንባቦች ያስደስቱኛል። | | | | | | | | |
| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
| | | የመንግሥት /አዳማ/ | | የግል /አዋሽ/ | | የግል /ሆሊኤንጅልስ/ | | የግል /አዳማ ፀሃይ/ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 3.12 | በጣም እስማማለሁ | 44 | 24.5 | 8 | 26.7 | 9 | 30 | 5 | 16.7 |
| | እስማማለሁ | 61 | 33.8 | 12 | 40 | 10 | 33.3 | 11 | 36.7 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 26 | 14.5 | - | - | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 |
| | አልስማማም | 18 | 10 | 7 | 23.3 | 6 | 20 | 3 | 10 |
| | ምንም አልስማማም | 21 | 11.7 | 3 | 10 | 1 | 3.3 | 4 | 13.3 |
| | መልስ ያልሰጡ | 10 | 5.5 | - | - | - | - | 3 | 10 |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 3.13 | በጣም እስማማለሁ | 45 | 25 | 8 | 26.7 | 6 | 20 | 6 | 20 |
| | እስማማለሁ | 62 | 34.4 | 9 | 30 | 9 | 30 | 9 | 30 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 33 | 18.3 | 7 | 23.3 | 5 | 16.7 | 8 | 26.7 |
| | አልስማማም | 18 | 10 | 3 | 10 | 6 | 20 | 4 | 13.3 |
| | ምንም አልስማማም | 20 | 11.2 | 3 | 10 | 4 | 13.3 | 3 | 10 |
| | መልስ ያልሰጡ | 2 | 1.1 | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው “ የትምህርቱ ይዘቶች በሕይወት ልምዴ ከማውቃቸው ጋር ዝምድና አላቸው” በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት ከመንግስት ትምህርት ቤት 58.3 ፐርሰንት ያህል ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 61.1 ፐርሰንት ያህሉ ናቸው። በዚህ መሠረት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ የሆኑ ውጤቶች ተገኝተዋል። የትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች ባሕል፣ አካባቢና ከህይወት ልምዳቸው ጋር እየተዛመዱ አዝናኝና ቀላል በሆነ መንገድ መቅረብ ከቻሉ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት እና ተነሳሶት እየጨመረ እንደሚሄድ Garder and Macintyre (1993) William and Burden (1997) ገልፀዋል። የቋንቋ መምህራኑም ይህንን ተግባር እንደአስፈላጊነቱ የሚያከናውኑ መሆናቸውን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል። ይሁንና በክፍል ምልከታው ወቅት የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ከሚያውቃቸውና በአካባቢያቸው ከሚያዩዋቸው ነገሮች ጋር እያዛመዱ ለማስተማር የሞከሩት በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ሁለት መምህራንና

በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ አንድ መምህር ብቻ ናቸው ስለሆነም ከፅሑፍ መጠይቁ የተገኘው ምላሽ በክፍል ምልከታው ከታየው እውነታ ጋር ተዛምዶ ሊታይበት አልቻለም።።

4.3 **የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሶትን በሚመለከት የቀረበ ትንተና**

ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተነሳሶት እንዲኖራቸው በቅድሚያ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። የተማሪዎቹ ፍላጎት ተነሳሽነትን፣ በራስ መተማመንን፣ ድፍረትን ሊያስገኝ ወይም ሲያሳጣ ይችላል። ይህንንም ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆችና ምልከታዎች እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል።

**ሠንጠረዥ አሥራ አምስት፣ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ፍላጐት አለኝ። | | | | | | | | |
| 2.2 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ይቀለኛል። | | | | | | | | |
| 2.3 | የአማርኛ ቋንቀ መምህሩ/ሯ ሲያስተምሩ ትምህርቱ ይገባኛል። | | | | | | | | |
| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
| | | የመንግሥት /አዳማ/ | | የግል /አዋሽ/ | | የግል /ሆሊ ኢንጅል ስ/ | | የግል /አዳማ ፀሃይ/ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 2.1 | በጣም እስማማለሁ | 56 | 20 | 11 | 36.7 | 10 | 33.4 | 12 | 40 |
| | እስማማለሁ | 78 | 19.5 | 13 | 43.3 | 15 | 50 | 10 | 33.4 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 18 | 10 | 3 | 10 | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 |
| | አልስማማም | 15 | 8.3 | 3 | 10 | 1 | 3.3 | 3 | 10 |
| | ምንም አልስማማም | 11 | 6.1 | - | - | - | - | 1 | 3.3 |
| | መልስ ያልሰጡ | 2 | 1.1 | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 2.2 | በጣም እስማማለሁ | 17 | 9.4 | 8 | 26.7 | 8 | 26.7 | 5 | 16.7 |
| | እስማማለሁ | 33 | 18.3 | 6 | 20.2 | 13 | 43.3 | 7 | 23.3 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 63 | 35 | 8 | 26.6 | 2 | 6.7 | 11 | 36.6 |
| | አልስማማም | 32 | 17.8 | 8 | 26.6 | 4 | 13.3 | 5 | 16.7 |
| | ምንም አልስማማም | 18 | 10 | - | - | 2 | 6.7 | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | 17 | 9.5 | - | - | 1 | 3.3 | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 2.3 | በጣም እስማማለሁ | 43 | 23.8 | 8 | 26.7 | 7 | 23.3 | 11 | 36.6 |
| | እስማማለሁ | 62 | 34.5 | 11 | 36.7 | 11 | 36.7 | 8 | 26.7 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 26 | 14.5 | 4 | 13.3 | 7 | 23.3 | 5 | 16.7 |
| | አልስማማም | 27 | 15 | 4 | 13.3 | 4 | 13.3 | 3 | 10 |
| | ምንም አልስማማም | 22 | 12.2 | 3 | 10 | 1 | 3.3 | 3 | 10 |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው፣ 74.4 ፐርሰንት የሚሆኑት የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና 78.9 ፐርሰንት የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት እንዳላቸው በማመልከታቸው ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ እና 14.4 ፐርሰንት ከሚሆኑ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና 8.8 ፐርሰንት ከሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለትምህርቱ ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያመለክት አሉታዊ ምላሽ ተገኝቷል። "የአማርኛቋንቋ ትምህርቱ ይቀለኛል" በማለት አዎንታዊ ምላሻቸውን የሰጡት ከመንግሥት ትምህርት ቤት 27.7 ፐርሰንት ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 52.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ናቸው። ለዚህ ሃሳብ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ደግሞ ከመንግሥት ትምህርት ቤት 27.8 ፐርሰንት ያህሉ ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት 23.3 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ 58.3 ፐርሰንት የሚሆኑት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች "ትምህርቱን ስንማር ይገባናል" በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 62.3 ፐርሰንት አዎንታዊ ምላሽ መስጠታቸውን ከመጠይቁ ምላሽ መገንዘብ ተችሏል። በአንፃሩ 27.2 ፐርሰንት ከመንግሥት ትምህርት ቤትና 19.9 ፐርሰንት የሚሆኑት ከግል ትምህርት ቤት ለዚህ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው በመንግስትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ሆኖም ግን የቋንቋ ትምህርቱ እንደሚቀላቸው የገለጹት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥቂቶች ናቸው። ለመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን በተደረገውየቃለ መጠይቅ የተማሪዎቹን ፍላጎት በሚመለከት የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል።

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል ለዚህም በምክንያትነት የተገለፀው፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር ከአምስተኛ ክፍል ስለጀመሩ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑት ከአፍ ፊት ተማሪዎች ጋር እኩል መወዳደር ባለመቻላቸው ነው። በግል ትምህርት ቤት የሚገኙት መምህራን ደግሞ ስለተማሪዎቻቸው የቋንቋ ፍላጎት ሲገልፁ ተማሪዎቹ ፍላጎታቸው መካከለኛ ነው። ምክንያቱም ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር

ሲያወዳድሩት በሚያውቁት ቋንቋ የሚማሩት በመሆኑ ትኩረት ሰጥተው ስለማይከታተሉት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽና ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ሊ.ቃረን ችሏል፡፡

ሠንጠረዠ አስራ ስድስት፣ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ተነሳሽነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 5.1 | ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተዋል፡፡ | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | - |
| 5.2 | ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ሲያስተምሩ በፀጥታ ያዳምጣሉ፡፡ | አዎ | 5 | 6 |
| | | አይደለም | 1 | - |
| 5.3 | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ወቅት እርስ በርሳቸው በሹክሹክታ ይነጋገራሉ፡፡ | አዎ | 1 | - |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 5.4 | ተማሪዎች መምህራቸው ሲያስተምሩ የግል ሥራቸውን የሚሠሩ አሉ | አዎ | 1 | - |
| | | አይደለም | 5 | 6 |
| 5.5 | መምህሩ ሲያስተምሩ ማስታወሻ የሚይዙ ተማሪዎች ብዙ ነበሩ | አዎ | 3 | 5 |
| | | አይደለም | 3 | 1 |
| 5.13 | ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቻቸው መልስ ሲመልሱ በጥንቃቄ ይከታተላሉ | አዎ | 4 | 6 |
| | | አይደለም | 2 | - |

ከላይ በሠንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው፣ የመማር-ማስተማሩ ክንውን ሂደት በተወሰነለት ጊዜ እንዲጠናቀቅና ተማሪዎችም ተገቢውን ዕውቀት እንዲያገኙ ተማሪዎቹ በመማሪያ ክፍላቸው በሰዓቱ መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ተግባር በግል ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚነትን ሲያገኝ በመንግስት ትምህርት ቤት ግን በሁሉም ጊዜ ድግግሞሽ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቶአል፡፡ በተስተምህሮው ወቅትም ተማሪዎች እርስበርሳቸው ሳያንሾካሽኩ በፀጥታ የማዳመጥ ተግባር ሙሉ ለሙሉ በግል ትምህርት ቤቶች የተተገበረ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት ተግባሩ አንድ ጊዜ ተጓድሎ ታይቶአል፡፡ በተጨማሪም በነበሩት የምልከታ ጊዜያት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች መምህሮቻቸው ሲያስተምሩ በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ ማስታወሻ ሲይዙ ታይተዋል፡፡ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ግን ማስታወሻ የመያዝ ተግባርን አንድ

ጊዜ ብቻ ሲያጓድሉ ለመመልከት ተችሏል። በተጨማሪም በመንግስት ትምህርት ቤት በአንድ የምልከታ ጊዜ የግል ስራቸውን የሚሰሩ ተማሪዎች እንደነበሩ ለማማጋገጥ ተችሏል። ተማሪዎች ከመምህራቸው በተጨማሪ የክፍል ጓደኞቻቸው የሚያቀርቡትን ሃሳብ በመከታተል ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ማሳየት ይኖርባቸዋል። ይሁንና ይህ ተግባር በግል ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ ሲተገበር ቢታይም በመንግስት ትምህርት ቤት በሁለት ጊዜ ድግግሞሽ ሳይተገበር ቀርቷል። ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው የመማር ማስተማሩን ሒደት በአትኩሮት የመከታተል ተግባር በግል ትምህርት ቤት በአብዛኛው ሲከናወን በመንግስት ትምህርት ቤት ግን አልፎ አልፎ መተግበሩን ነው ስለሆነም በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ትምህርቱን መከታተላቸው ተረጋግጧል።

ሠንጠረዥ አስራ ስባት፣ ተማሪዎች ለመማር ያላቸውን ፈቃደኝነት በሚመለከት ከክፍል ምልከታው የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግሥት | የግል |
| 5.6 | በፈቃደኝነት እጃቸውን በማውጣት መልስ የሚመልሱ ተማሪዎች አሉ። | አዎ | 6 | 6 |
| | | አይደለም | - | - |
| 5.7 | በፈቃደኝነት ጥያቄ የሚመልሱ ተማሪዎች ጥቂት ናቸው። | አዎ | 6 | 4 |
| | | አይደለም | - | 2 |
| 5.8 | ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች አሉ። | አዎ | 3 | 6 |
| | | አይደለም | 3 | - |
| 5.12 | ተማሪዎች በቡድን ለመሳተፍ ፈቃደኝነት ይታይባቸዋል። | አዎ | 3 | 4 |
| | | አይደለም | 3 | 2 |
| 5.16 | የቤት ሥራቸውን ሰርተው የመጡት ሁሉም ተማሪዎች ናቸው | አዎ | 2 | 3 |
| | | አይደለም | 4 | 3 |
| 5.17 | የቤት ሥራቸውን ሰርተው የመጡት ተማሪዎች ጥቂቶች ናቸው። | አዎ | 3 | 1 |
| | | አይደለም | 3 | 5 |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ በቋንቋ ትምህርቱ ወቅት በሁለቱም ትምህርት ቤቶች እጃቸውን በማውጣት በፈቃደኝነት ጥያቄዎችን የሚመልሱ ተማሪዎች መኖራቸውን ከምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል። ይሁንና እጃቸውን በማውጣት መልሶችን የሚመልሱ ተማሪዎች በመንግስት ትምህርት ቤት በተካሄደው ምልከታ ጥቂቶች መሆናቸው ተረጋግጧል። በግል ትምህርት ቤት ግን በሁለት ጊዜ ድግግሞሽ በክፍል ውስጥ የሚገኙ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ጥያቄ

ለመመለስ በፈቃደኝነት ሲሳተፉ ታይተዋል። በተጨማሪም ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች በመንግስት ትምህርት ቤት በሦስት ጊዜ ድግግሞሽ ተግባሩን ሲፈፅሙ በግል ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረጋቸው በምልከታው ሊረጋገጥ ችሏል።

በአንፃሩ የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በቡድን ያደራጁበት ጊዜ ውስን ስለነበረ ምልከታዎቹ በተካሄዱባቸው ቀናት በተሟላ ሁኔታ ተማሪዎቹን የቡድን ተሳትፎ ፈቃደኝነት ለማየት አልተቻለም ነገር ግን በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የቡድን ስራ በነበረበት ወቅት ለመሳተፍ ያሳዩት ፈቃደኝነት ጠንካራ እንደነበረ ለማረጋገጥ ተችሏል።

የተማሪዎች ተነሳሽነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ አንድን ነገር ለማወቅ ለመተግበርና በነገሩ እርካታን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት እንደሚገለፅ Brown (1987፣ 14-16)፣ Noels ( 2003) ገልፀዋል። ይህም ጥያቄ በመጠየቅ፣ በመመለስ፣ የቤት ሥራዎችን በመስራት፣ በቡድን ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተነሳሽነትን ማሳየት ይቻላል። Petty (2004፣ 50-55)። በመሆኑም ከመመምህራን የተገኘው የቃለመጠይቅ ምላሽ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች በፈቃደኝነት ለመጠየቅና ለመመለስ የቃላት እጥረት ስለሚያጋጥማቸው አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው አመልክተዋል። ይኸንንም በምልከታ ወቅት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ቃላት እያጠራቸው ከአፍመፍቻ ቋንቋቸው ቃላትን እየቀላቀሉ ሲጠቀሙ ተስተውለዋል። በተጨማሪም አንድአንድ ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቁ አስተያየት መስጫ ክፍል ላይ መጠይቁ ከተፃፈበት ቋንቋ ውጪ፡- በአፍመፍቻ ቋንቋቸው አስተያየት ሰጥተዋል። ስለሆነም በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በፈቃደኝነት የመሳተፍ ተግባር በተገቢው ሁኔታ ሊከናወን አልቻለም።

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው የቤት ስራዎችን በተደጋጋሚ ባለመስጠታቸው ምልከታው በተካሄደባቸው ቀናት ተማሪዎቹ ተግባሩን ሲፈፅሙ አልታዩም። የቤት ስራ በተሰጠባቸው ቀናትም ቢሆን በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ደብተር በክፍል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ

ስላልተቆጣጠሩ የቤት ስራቸውን ሰርተው የተገኙ ተማሪዎች ጥቂቶች ነበሩ። ይህንንም ማረጋገጥ የተቻለው የቤት ስራ ሳይሰሩ የመጡ ተማሪዎች አጠገባቸው ካለው ተማሪ መልሶችን ሲገለብጡ በመታየታቸው ነው።

በአጠቃላይ ከምልከታውና ከመጠይቆቹ ውጤቶች መገንዘብ የሚቻለው በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በፈቃደኝነት የሚመልሱና የተሰጧቸውን የቤት ስራዎች ሰርተው የሚመጡ ተማሪዎች በግል ትምህርት ቤት በቁጥራቸው ብዛት ያላቸው ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት ግን አነስተኛ ሆኖ ታይቷል። ስለሆነም በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት የተሻለ ተነሳሽነት አሳይተዋል ማለት ይቻላል።

ሠንጠረዥ አስራ ስምንት፣ የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ብቃት በሚመለከት ከክፍል ምልከታ የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | የተጠኚ መምህራን ትምርት ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የመንግስት | የግል |
| 5.9 | ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ፍርሃት ይታይባቸዋል። | አዎ | 3 | 1 |
| | | አይደለም | 3 | 5 |
| 5.10 | ተማሪዎች ጥያቄ በሚመልሱበት ጊዜ ሥህተት ሲፈፅሙ የመደንገጥ ሥሜት ይታይባቸዋል። | አዎ | 1 | 1 |
| | | አይደለም | 5 | 5 |
| 5.11 | ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ የመረጋጋት ሥሜት ይታይባቸዋል። | አዎ | 2 | 4 |
| | | አይደለም | 4 | 2 |
| 5.14 | ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው የተሳሳተ መልስ ሲሰነዘር ይስቃሉ | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |
| 5.15 | በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎቹ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሳይፈሩ ሲወያዩ ታይተዋል። | አዎ | 1 | 2 |
| | | አይደለም | 5 | 4 |

ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው፣ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ሲመልሱ በሦስት የክፍል ምልከታ ጊዜያት ፍርሀት የታየባቸውን ተማሪዎች ማየት ሲቻል በግል ትምህርት ቤት ግን በአንድ የክፍል ምልከታ ወቅት ብቻ የሚፈሩ ተማሪዎችን ማየት ተችሏል። በአንጻሩ ጥያቄ ሲጠየቁ የመረጋጋት ስሜት የሚታይባቸው ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥቂቶች

ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት ግን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ነበሩ በሌላ በኩል በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በነበራቸው የቡድን ስራ ወቅት ሳይፈሩ እርስበርሳቸው ሲወያዩ ታይተዋል፡፡ በአንፃሩ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ የመሳቅ ተግባር ከመንግስት ትምህርት ቤት ይልቅ በግል ትምህርት ቤት መፈፀሙ በምልከታው ሂደት ተስተውሏል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 17 ላይ እንደታየው በፍቃደኝነት የመሳተፍ ተግባርን አብዛኞቹ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ሥላልተገበሩት የተሳሳተ መልስ ሰጥተው ሲደነግጡ ከአንድ ጊዜ በላይ አልታየም፡፡ ይህንን ሃሳብ ከተማሪዎች መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ 60 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች ጥያቄ ለመጠየቅ የማይፈሩ መሆናቸውን ሲያመለክቱ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ 43.3 ፐርሰንት የሚሆኑ ተማሪዎች እንደማይፈሩ አመልክተዋል፡፡ በክፍል ተሳትፎ ወቅት በራስ መተማመን የሚታይባቸው መሆናቸውን የገለፁት ደግሞ ከግል ትምህርት ቤት 72 ፐርሰንት የሚሆኑት ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 57.3 ፐርሰንት የሚሆኑት ናቸው፡፡

በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ቋንቋውን ሲናገሩ እንደማይጨነቁ 70 ፐርሰንት የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲገልፁ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 57.3% የሚሆኑት ቋንቋውን ያለጭንቀት መናገርና በክፍል ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡ ይሁንና ከትምህርቱ በኋላ እርካታን እንደሚያገኙ አዎንታዊ ምላሻቸውን በመስጠት የገለጹት ከግል ትምህርት ቤት 66.6 ፐርሰንት ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 41 ፐርሰንት የሚሆኑ ናቸው፡፡ Hedge (2000) እንደገለፁት ተማሪዎች "እሳሳት ይሆን ይሳቅብኝ ይሆን" የሚል የጥርጣሬ መንፈስን በውስጣቸው ይዘው የሚማሩ ከሆነ በራስ የመተማመን በቃታቸው እየቀነሰ የመጨነቅና እርካታን የማጣት ስሜት ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ለትምህርቱ ያላቸውን ተነሳሽነት እያዳከመው ይኼዳል፡፡

በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተጠኚ መምህራን በቃለ መጠይቁ ላይ ስለተማሪዎቻቸው በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለመናገር ድፍረትና በራስ መተማመን ስለሚያጣ ጥያቄ ከመጠየቅና ከመመለስ ይቆጠባሉ፡፡ ስለሆነም "እናስጨንቃቸዋለን" በሚል ስሜት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ

እንደማያስገድዱዋቸው ገልፀዋል። በመሆኑም በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል።

## 4.4 በተማሪዎች ተነሣሶት ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ተላውጦዎች በሚመለከት የቀረበ ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በተለያዩ ሙሁራን በተገለፀው ሐሳብ ለማብራራት እንደተሞከረው የተማሪዎች ተነሳሶት ከፍ ወይም ዝቅ እንዲል ከሚያደርጉ ተላውጦዎች መካከል ቢጤዎቻቸው ወላጆቻቸውና የአካባቢው ማሕበረሰብ ይገኙበታል። እነዚህም የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹን ለማነቃቃት አጋዥ ወይም እንቅፋት ሊሆኑበት ይችላሉ። በመሆኑም ይህንን ተግባር በተመለከተ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ምላሽ ቀጥሎ ለማየት ይሞከራል።

ሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ፡- ቢጤዎች ወላጆችና ማህበረሰቡ ያላቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች |
|---|---|
| 4.1 | የክፍል ጓደኞቼ ጥያቄዎችን እንድመልስ ያበረታቱኛል። |
| 4.2 | የክፍል ጓደኞቼ በቋንቋ ትምህርት ወቅት በምፈጥረው ስህተት አይስቁብኝም። |
| 4.3 | ወላጆቼ ስለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው። |
| 4.4 | ወላጆቼ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን እንዳጠና ያበረታቱኛል። |
| 4.5 | በአካባቢዬ ያሉ ሰዎች ስለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው። |

| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመንግሥት /አዳማ/ | | የግል /አዋሽ/ | | የግል /ሆሊ.ኢንጅልስ/ | | የግል /አዳማ ፀሀይ/ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 4.1 | በጣም እስማማለሁ | 47 | 26.1 | 7 | 23.3 | 5 | 16.7 | 4 | 13.3 |
| | እስማማለሁ | 62 | 34.5 | 14 | 46.7 | 15 | 50 | 14 | 46.7 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 23 | 12..8 | 3 | 10 | 3 | 10 | 4 | 13.3 |
| | አልስማማም | 36 | 20 | 6 | 20 | 4 | 13.3 | 5 | 16.7 |
| | ምንም አልስማማም | 11 | 6.1 | - | - | 3 | 10 | 3 | 10 |
| | መልስ ያልሰጡ | 1 | 0.5 | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 4.2 | በጣም እስማማለሁ | 30 | 16.7 | 7 | 25.4 | 5 | 16.7 | 1 | 3.4 |
| | እስማማለሁ | 68 | 37.8 | 9 | 30 | 11 | 36.6 | 7 | 23.3 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 23 | 12.8 | 3 | 10 | 3 | 10 | 7 | 23.3 |
| | አልስማማም | 34 | 18.9 | 7 | 23.3 | 9 | 30 | 7 | 23.3 |
| | ምንም አልስማማም | 25 | 13.8 | 4 | 13.3 | 2 | 6.7 | 5 | 16.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | - | - | 3 | 10 |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 4.3 | በጣም እስማማለሁ | 32 | 17.7 | 5 | 16.7 | 6 | 20 | 7 | 23.3 |
| | እስማማለሁ | 45 | 25 | 10 | 33.3 | 8 | 26.7 | 9 | 30 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 40 | 22.2 | 10 | 33.3 | 7 | 23.3 | 8 | 26.7 |
| | አልስማማም | 20 | 11.1 | 5 | 16.7 | 5 | 16.7 | 4 | 13.3 |
| | ምንም አልስማማም | 30 | 16.7 | - | - | 4 | 13.3 | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | 13 | 7.3 | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 4.4 | በጣም እስማማለሁ | 36 | 20 | 9 | 30 | 6 | 20 | 5 | 16.7 |
| | እስማማለሁ | 49 | 27.3 | 10 | 33.3 | 7 | 23.3 | 8 | 26.6 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 29 | 16.1 | 4 | 13.4 | 6 | 20 | 5 | 16.7 |
| | አልስማማም | 38 | 21.1 | 6 | 20 | 5 | 16.7 | 10 | 33.3 |
| | ምንም አልስማማም | 28 | 15.5 | 1 | 3.3 | 4 | 13.3 | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | - | - | - | - | 2 | 6.7 | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |
| 4.5 | በጣም እስማማለሁ | 25 | 13.9 | 3 | 10 | 2 | 6.6 | 7 | 23.3 |
| | እስማማለሁ | 65 | 36.1 | 9 | 30 | 6 | 20 | 4 | 13.3 |
| | ለመወሰን ያስቸግረኛል | 21 | 11.7 | 10 | 33.3 | 14 | 46.6 | 12 | 40 |
| | አልስማማም | 29 | 16.1 | 7 | 23.3 | 3 | 10 | 17 | 56.7 |
| | ምንም አልስማማም | 26 | 14.4 | 1 | 3.3 | 5 | 16.7 | 2 | 6.7 |
| | መልስ ያልሰጡ | 14 | 7.8 | - | - | - | - | - | - |
| | ድምር | 180 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 | 30 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የክፍል ጓደኞቻቸው ግፊት ተፅእኖ እንደሚያደርስባቸው 60.6 ፐርሰንት የሚሆኑ የመንግስት ትምህርቤት ተማሪዎችና 65.5 ፐርሰንት የሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት አዎንታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ተማሪዎቹ በክፍል ተሳትፎአቸው ስህተት ቢፈጥሩም ጓደኞቻቸው እንደማይስቁባቸው 54.5 ፐርሰንት የሚሆኑት የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና 45.1 ፐርሰንት የሚሆኑ የግል ትምህርትቤት ተማሪዎችን ሲገልፁ 54.5 ፐርሰንት የሚሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤትና 45.1 ፐርሰንት ከግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው እንደማይስቁባቸው ገልፀዋል። ከዚህ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ እንደሚደርስባቸውና በአንፃሩ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚገኙት ተማሪዎች ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚገኙት ተማሪዎች የተሳሳተ መልሥ ሲሰጡ እንደሚስቁ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል ተማሪዎች ወላጆቻቸው ለቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው 42.3 ፐርሰንት የሚሆኑ የመንግስት እና 50 ፐርሰንት ነጥብ ስድስት ፕርሰት የሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ገልፀዋል። 22.2 ፐርሰንት የሚሆኑ የመንግስት ትምህርት ቤት እና 27.7 ፐርሰንት የሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት እንደተቸገሩ ከምላሻቸው ለመገንዘብ ተችሏል። ይሁን እና 43.3 ፐርሰንት ከመንግስት ትምህርት ቤት እና 49.9 ፐርሰንት ከግል ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆቻቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምርቱን እንዲያጠኑ እንደሚገፏፏቸው በምላሻቸው አረጋግጠዋል። በመሆኑም ወላጆች በቋንቋ ትምህርቱ ላይያላቸው አወንታዊ ተፅእኖ 50 ፐርሰንት ያልሞላ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ በአከባቢው የሚገኙት ማህበረሰቦች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ሃምሳ ፕርሰንት የሚሆኑ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥሩ እንደሆነ ሲያመለክቱ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 34.4 ፐርሰንት የሚሆኑት ተመሳሳይ ምላሽ ሰተዋል። ለዚህ ጥያቄ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ 11.7

ፐርሰንት የሚሆኑና 39.9 ፐርሰንት የሚሆኑ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መወሰን ያስቸግረኛል የሚል ምላሽ ሰተዋል፡፡

## 4.5 ከጽሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ አስተያየቶች

ለተማሪዎች በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅና ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም አስተያየቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን ፍላጎት ለምን እንደሚማሩት በማስመልከት ተጠይቀው ሲመልሱ የሚከተሉትን ሃሳቦች ዘርዝረዋል፡፡

- ቋንቋው የመግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ ወደፊት ከሰዎች ጋር የመግባባት ችግር እንዳያጋጥመኝ እማራለሁ፣
- በአማርኛ ትምህርት ውስጥ የሚገኙትን ዘይቤዎች እና ቅኔዎች ማወቅ ስለምንፈልግና የቋንቋውን ሰዋሰው አጠቃቀም መገንዘብ ስለምፈልግ እማራለሁ፣
- ከሚሰጡት ትምህርቶች አንዱ በመሆኑ እማራለሁ የሚሉ አዎንታዊ ምላሾች ከግል ትምህርት ቤቶች ሲገኙ፣

ከመንግሥት ትምህርት ቤት ደግሞ፣

- ቋንቋውን የምማረው የመማር ግዴታ ስላለብኝ፣ ፈተና ለማለፍ፣
- ቋንቋውን ለመልመድ ስለምፈልግ፣ የስራ ቋንቋ ስለሆነ፣ የሚሉ ምላሾች ተገኝተዋል፡፡

ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከውስጣዊ ተነሳሶት ይልቅ በውጫዊ ግፊት ፈተና ለማለፍ ሲሉ እንደሚማሩ ሲሆን የግል ትምርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ በቋንቋ ውስጥ የሚገኘውን ስርአት እና የቋንቋ አጠቃቀም ለማወቅ ተግባቦትን ለማሳደግ ሲሉ በፍላጎት እንደሚማሩ ነው፡፡ ተጠኚ መምህራኑ ምን አይነት የመማሪያ ስልትን ተጠቅመው ተማሪዎችን ለማነሳሳት ጥረት እንደሚያደርጉ ተጠይቀው ሲገልፁ፣

- በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን በቡድን እና በጥንድ በማሳተፍ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ በማድረግ፣

- ሌሎች አጋዥ መፃህፍትን በማጣቀስ አዝናኝ በሆነ መንገድ እንደሚያስተምሩ ሲገልፁ፣

**በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ደግሞ:**

- የክፍሉ ፀጥታ እንዳይጓደል እና ተማሪዎቹ ብዛት ስላላቸው፣ በአብዛኛው በግል፣ አልፎ አልፎ በጥንድ ተማሪዎችን በማሳተፍ ቋንቋውን እንደማሩ በማድረግ ፣
- በሚገባቸውም መልክ ምሳሌዎችን በመጥቀስ እያበረታቱ እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል።

**ተማሪዎች የመምህሮቻቸው የማስተማሪያ ሥልቶች እንደሚስማማቸው ተጠይቀው የሚከተለውን ምላሽ ሰተዋል**

- ለተማሪዎች ጥሩ አመለካከት ስላላቸው ፣
- በቀላል ቋንቋ በምሳሌ እና በቀልድ እያዋዙ ስለሚያስተምሩ፣
- በቡድን በማደራጀት ድራማ ስለሚያሰሩና ስለሚያወያዩ፣
- በፈገግታ ሳይቆጡ ጥያቄዎችን ስለሚመልሱ የማስተማር ስልታቸው ይስማማናል የሚሉ አወንታዊ ምላሾች ከግል ትምህርት ቤቶች ሲገኙ፣

ከመንግሥት ትምህርት ቤት ደግሞ

- በትሕትና ትምህርቱን ስለሚያስረዱ፣
- ማስታወሻ ስለሚሰጡ፣
- የክፍሉን ፀጥታ ስለሚያከብሩ የማስተማር ስልታቸው ይስማማናል የሚሉ አዎንታዊ ምላሾች ተገኝተዋል።

የመምህሮቻቸው የማስተማር ስልት እንደማይስማማቸው የገለፁት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ የሚከተለውን ብለዋል

- ፊት ለፊት ወጥተን እንድንናገር ስለሚያስገድዱን ፣
- የቤት ስራ ስለሚሰጡን የማስተማር ስልታቸው አይስማማንም ሲሉ ፣

ከመንግሥት ትምህርት ቤት የተገኙ ተማሪዎች ደግሞ ፡

- የሚያዝናኑ ቀልዶችን ስለማይጠቀሙ፣
- የክፍል ስራ የሚሰጡት ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ በመሆኑ እና የሰራነውን ስለማያርሙልን፣
- ከፊት የሚቀመጡትን ብቻ ስለሚያሳትፏቸው የማስተማር ስልታቸው አይስማማንም የሚሉ አሉታዊ ምላሾችን ሰጥተዋል።

ከተማሪዎቹ የተገኙት አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት በግል ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ትምህርቱን በተሻለ ሁኔታ አዝናኝ እና አስደሳች ለማድረግ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ከፍ ለማድረግ ጥረት የሚያደርጉ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራን ይህንን ተግባር ከመፈፀም ይልቅ በክፍሉ ፀጥታ መጠበቅ እና በገለፃ ላይ እንደሚያተኩሩ ማረጋገጥ ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት
# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ በመንግሥትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማነቃቃት በየትኞቹ የተነሣሶት ስልቶች እንደሚጠቀሙና እንዴት እንደሚተገብሯቸው ማጥናት ነው፡፡

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የተነሣሽነት ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በርካታ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጐትና ተነሣሽነት እንዲኖራቸው አዳዲስ እውቀቶችን እንዲያገኙና በተግባር እንዲተረጉሙአቸው የተነሣሶት ስልቶችን ተጠቅሞ የቋንቋ መምህሩ ማስተማር እንደሚገባቸው Brown (1987) ገልፀዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ Dornyel (2001) የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች በተስተምህሮቱ ወቅት ንቁ ተሣታፊ እንዲሆኑ ምቹ እና አጋዥ የክፍል ሁኔታዎችን በመፍጠር ወደ ታለመው ግብ እንዲደርሱ ማበረታታት እንደሚጠበቅባቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራኑ የተነሣሶት ስልቶችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የተማሪዎች ዳራ፣ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና አደረጃጀት የቋንቋ መምህሩ የራሱ ዳራና የማስተማር ፍላጐት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በመንግስትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትኞቹ ተማሪዎቻቸውን ለትምህርቱ የተነሣሱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ በንፅፅር ለማየት ተሞክሯል፡፡
ይህ ጥናት በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ይዞ የተነሣ ነበር፡፡ እነዚህም፡-

1. በመንግሥትና በግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ተነሣሶት እንዲኖራቸውና ያላቸውንም ተነሣሶት እንዲያጎለብቱ ምን አይነት ስልቶችን ይጠቀማሉ? በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን?

2. የተማሪዎችን ተነሣሶት ሊያዳክሙ የሚችሉ ስልቶች የትኞቹ ናቸው?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ስለተማሪዎቻቸው ውስጣዊ ተነሳሶት ምን አስተያየት አላቸው? የተማሪዎቹ ውስጣዊ ተነሣሽነትስ በምን ይገለፃል? የሚሉት በጥናቱ የተነሱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሠበሠቡት መረጃዎች ተተንትነው የተደረሠበት ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመማር–ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎች ተነሣሽነት ላይ ተፅእኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮች መኖራቸው ከመረጃ ምንጮቹ ለማወቅ ተችሏል በዚህም መሠረት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሣሽነት አንፃራዊ በሆነ መልኩ በግል ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ ተማሪዎች ዝቅ ያለ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች ያላቸው ተነሣሶት ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች አማካኝነት መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

- መምህራን መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት በክፍል ውስጥ መፍጠር አለመቻላቸው፣
- እንደ በቡድንና በጥንድ እያደራጁ በማሳተፍ ለተስተምህሮቱ አጋዥ ሁኔታን አለማመቻቸታቸው፣
- አሉታዊ ምጋቤ-ምላሾችን መጠቀማቸው፣
- መምህራኑ በአብዛኛው መምህር- መር የማስተማሪያ ዘዴን መርጠው መጠቀማቸውና ተማሪ-ተኮር ዘዴን አለመከተላቸው፣
- አዝናኝና አስደሳች የክፍል ውስጥ ሁኔታ ለመፍጠር አለመጣራቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸው አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሶት የተሻለ በመሆኑ ያለባቸው ተፅእኖ ውስን እንደሆነ የተገኘው የመረጃ ውጤት ያሣያል፡፡

በሌላ በኩል በመምህራን የተነሣሣት ሥልት አተገባበር ላይ ተፅእኖ ካስከተሉ ጉዳዩች አንዱ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ነው፡፡ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች ንፅህናቸው ያልተጠበቁ መቀመጫዎቹ ያልተሟሉና በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እስከ ሰባሰባት የሚደርሱ ተማሪዎች የሚገኙ በመሆናቸው፡ ተማሪዎችን በቡድን ለማደራጀትና በክፍሉ ውስጥ ተንቀሳቅሶ የተማሪዎችን ሥራ ለመከታተል አለመቻላቸው፣ የመሳሰሉት በመምህራን የተነሳሶነት ሥልት አተገባበር ላይ ተፅእኖ ማሳደራቸው ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም በመንግሥት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በሙያቸው በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ያነሰ ክፍያ ሥለሚያገኙና በግል ትምህርት ቤት እንደሚያስተምሩ መምህራን የመጓጓዣ አገልግሎት፣ አመታዊ ማነቃቂያ፣ ከሃላፊዎቻቸው የሚቀርብ አድናቆትን ማግኘት አለመቻላቸው በተነሳሶት ሥልት አተገባበር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር መቻሉን ከተሰጡት ምላሾች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የሚያሥተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ንፅህናቸው የተጠበቀና በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙት የተማሪዎች ብዛት ከሃምሣ አራት ያልበለጠ በመሆኑ እንዲሁም የተሻለ ክፍያና ጥቅማ ጥቅሞችን በማግኘታቸው በመጠኑም ቢሆን ከተፅእኖ ነፃ መሆናቸው ከክፍል ምልከታውና ከመጠይቁ ውጤቶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው በጥናቱ ለማረጋገጥ የተሞከረው ከመንግስትና ከግል ትምህርትቤቶች የትኞቹ ተማሪዎቻቸውን በተሻለ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርቱ ለማነቃቃትና ለማነሳሳት ይሞክራሉ የሚለውን ነው፡፡ በመሆኑም ከክፍል ምልከታውና ከመጠይቆቹ ምላሽ ማረጋገጥ እንደተቻለው የተነሳሶት ሥልቶችን በተሻለ ሁኔታ የሚተገብሩት በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤት ይልቅ በአነሳሽነታቸው የተሻሉ ሊሆኑ የቻሉት፡-

- በክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው ትሕትናን፣ ፈገግታንና ፈቃደኝነትን በማሳየት፣ ሥማቸውን እየጠሩ በማሳተፍ መልካም የሆነ የመምህር-ተማሪ ግንኙነት በመፍጠራቸው፤

- አዝናኝ ቀልዶችን በትምህርቱ ጣልቃ በማስገባትና የትምህርቱን ይዘት ከተማሪዎች ልምድ ጋር አዛምደው በማቅረባቸው፤
- ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት የውይይትና የመተጋገዝ መንፈስን በመማርያ ክፍሉ ውስጥ በመፍጠር ተማሪ - ተኮር ዘዴን መከተላቸው፤
- ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታታት አዎንታዊ ምጋቤ-ምላሾችን በመሥጠታቸው የተማሪዎችን ተነሳሶት ለመቀስቀስም ሆነ ያላቸውን ተነሳሶት ከፍ ለማድረግ የተሻሉ መሆናቸው ከመረጃዎቹ ውጤቶች ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአንፃሩ በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን የተነሳሶት ሥልቶች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ሲቸገሩ ታይተዋል። በመሆኑም መምህራኑ በክፍል ውስጥ የቁጡነት ባህሪ በማሳየታቸው ፣ የክፍሉ ፀጥታ እንዳይታወክ በሚል ሥጋት በትምህርቱ ጣልቃ ቀልዶችን የመጠቀም ብልሃታቸው ዝቅተኛ መሆኑ፣ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ አደራጅቶ ትምህርቱን ተማሪ–ተኮር ከማድረግ ይልቅ ለገለፃና ለግላዊ ተሳትፎ የላቀ ድርሻ መሥጠታቸው ከአዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ ጐን ለጐን አሉታዊ ምጋቤ - ምላሾችን ማቀበላቸው፣ የቤት ሥራ ባለመስጠታቸው ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባራቸው ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

በሌላ በኩል በመንግስትና በግል ትምህርቤቶች በተመሳሳይ መልኩ የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ አለማበረታታት፣የሽልማት ምጋቤ - ምላሾችን አለመስጠት በመቅረፀ-ድምፅ አማካኝነት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አለመጠቀማቸው ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች ናቸው ።

ሌላው ከዚህ ጥናት በተገኘው ውጤት የተረጋገጠው የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚመለከት ነው። የመጠይቆቹና የምልከታው ውጤቶች እንደሚያመለክቱት፣ የተማሪዎች ተነሳሶት በተስተምህሮቱ ወቅት በክፍል ውስጥ በሚያርጉት ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና በሚያደርጉት ጥረት የሚገለጥ ነው። በዚህም መሠረት በግል ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በፈቃደኝነት ሲሳተፉ ታይተዋል ምንም እንኳን በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ

ፍላጐት እንዳላቸው በመጠይቁ ምላሽ የገለፁ ቢሆንም ከምልከታውና ከመምህራን መጠይቅ ለመረጋገጥ እንደተቻለው ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፈቃደኝነት የሚሳተፉ፣ ማስታወሻ የሚይዙ፣ ትምህርቱን ያለሽክሽክታ በፀጥታ የሚከታተሉ፣ የጓደኞቻቸውን መልሶ በጥንቃቄ የሚያዳምጡ ጥቂት መሆናቸው ሊታወቅ ችሏል፡፡

ከመንግስት ትምህርት ቤት የተገኙት የመጠይቅ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ፍቃደኝነት ላለማሳየታቸው እንደምክንያት የተወሰደው፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋአቸው በመሆኑና በክፍል ተሳትፎ ወቅት የቃላት እጥረት ሥለሚያጋጥማቸው ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ተረጋግቶ ጥያቄ ያለመጠየቅ፣ በክፍል ተሳትፎ ወቅት ሥህተት ሲፈጥሩ መደናገጥ፡ በራስ ያለመተማማን ችግር እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል ፡፡ ሥለሆነም በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊ ምጋቤ- ምላሽ በመስጠታቸውና አሉታዊ ምጋቤ-ምላሾችን በመጠቀማቸው የተማሪዎቹም ተነሳሶት ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአንፃሩም በግል ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ተሳትፎ ወቅት ፈቃደኝነት ያላቸው፣ መረጋጋት የሚታይባቸው፣ በራስ መተማማን ያላቸው መሆናቸው ከመጠይቆቹ እናከምልከታው ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት የተሻለ ተነሳሶት እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል በሁለቱም ትምህርትቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው የሚቀበሉት ማበረታቻ፣ ወላጆቻቸውና ማህበረሰቡ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ለትምህርቱ የሚያደርጉላቸው እገዛ አነስተኛ መሆን ተመሳሳይነት እንደሚታይበት የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡

በመሆኑም መምህራን በክፍል ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩት የተነሳሶት ሥልቶች በተሻለ ሁኔታ በግል ትምህርት ቤቶች ወስጥ መተግበራቸውን በዚህጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ አጥኝዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች በመፍትሔነት አቅርባለች፤

- በአንድ የመማርያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ስፋት ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝ አለመሆን መምህሩ የእያንዳንዱን ፍላጐትና ተነሳሶት ተከታትሎ ለማነቃቃትና ከፍ ለማድረግ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ስፋት ጋር የተመጣጠነ ቢሆን፣ በተለይም በመንግስት ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ብዛት የሚቀንስበት ሁኔታ ቢመቻች ጥሩ ነው፤
- በመማርያ ክፍሎቹ ውስጥ በቂ የሆኑ መቀመጫዎች መኖርና የክፍሉ ንፅህና መጠበቅ ተማሪዎችን ለማነቃቃት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ የመማሪያ ክፍሉ ምቹ እንዲሆን ትምህርት ቤቱ መቀመጫዎችን ቢያሟላና ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍላቸውን ንጽህና እንዲጠበቁ መምህራን ቁጥጥር ቢያደርጉ መልካም ነው፤
- መምህራን በተሻለ ሁኔታ በክፍል ውስጥ የተነሳሶት ስልቶችን እንዲተገብሩ ለማድረግ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ አጫጭር ሥልጠናዎች ለመምህራን ቢሰጥ መልካም ነው፤
- በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን መካከል የልምድ ልውውጥ ቢደረግ ያላቸውን ተነሳሽነት ሊያጐለብትላቸው ይችላል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የትምህርቱን ይዘት አዝናኝና አስደሳች በማድረግ በቡድንና በግል በማደራጀት ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታታትና ተገቢውን ምጋቤ - ምላሽ በመስጠት ተማሪዎቹ ተነሳሶት እንዲኖራቸውና በቋንቋ ትምህርቱ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ቢጥሩ መልካም ነው፡፡ በተለይም በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን እነዚህን የተነሳሶት ሥልቶች ተግባራዊ ለማድረግ ቢጥሩ የተሻለ ነው፡፡ የቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለማነቃቃትና የተነሳሶት ሥልቶችን ለመተግበር በቅድሚያ ቋንቋውን ለማስተማር ሙሉ ፍላጐትና ተነሳሶት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል ለሚያሳዩትም ተነሳሶት ትምህርት ቤቱ የማበረታቻ ምስክር ወረቀቶችን፣ ሽልማቶችን አንዳንድ ጥቅማጥቅሞችን ለመምህራኑ ቢያበረክት መልካም ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሰለሞን ተሠማ(1995):: "ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው" አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማሪያ የተዘጋጁትን መርሃ ትምህርቶች ለማሻሻል ለተካሄደው ዓውደ ጥናት መነሻ የቀረበ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)::

ተስፋዬ ሸዋዩ(1981):: "ሥነ ልሣንና ቋንቋን የማስተማር ዘዴ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)::

ትምህርት ሚኒስቴር(1986) :: <u>የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አተገባበር</u>። አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ (1998)። <u>የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር</u>። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፣አልፋ፣ ማተሚያ ቤት።

Alatis,J.(1981). <u>The second language classroom: Directions for the 1980's. Cambridge: Cambridge Unversity Press.</u>

Alison, J .(1993). 'Not Brother Motivating reluctant language Learners in key stage 4' .London: Centre for Information on Language Teaching and Research( CILT).

Bayush, Tibebu. (2007). "A Study of the Motivation teachniques Employed by EFL Teachers: In the Case of two Schools two Primary Schools in Bure Wereda, West Gojjam." (Unpublished M.A Thesis) Addis Ababa University.

Benson, P.(2000). <u>Teaching and Researching Autonomy in Language Learning</u>. London: Longman.

Bill, H. (2001). <u>Educational Psychology Interactive</u>. New York: Oxford University press.

Brophy, J.E.(1998). <u>Motivating Students to Learn</u>. Boston: MC Graw-Hiw.

Brown,H.D.(1987). <u>Principle of Language Learning and Teaching (2nd ed.)</u>. New Jersey: Premier Hall.

Chambers, G.N.(1999).Motivation Language Learners. Cleve don: Multi.

Covington, M.(1999). "Caring about Learning: The Nature and Nurturing of subject-matter Appreciation" Educational Paycnologist. V. 34, pp.127-36.

Cunnings worth, A. (1984). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: A division of Heinemann Educational Books Ltd.

Dorneyei, Z. (1998). "Motivation in Second and Foreign Langua Learning". Language Learning. V. 31 pp. 117-135.

_________ (2001).Teaching and Researching Motivation. London: Person. Education Limited.

_________ (2003) "Attitudes Orientations and Motivation in language Learning: Advances in Theory, Research, and Applications" Language Learning: A Journal of Research in Language Studies. V. 53, PP.3-32.

Elliot, J.G. et al. (2005). Motivation Engagement and Educational Performance International Perspectives on the Contexts for Learning. New York: Pellagra.

Ellis, R.(1994).The Study of Second Language Acquisition. Oxford: Oxford University Press.

Gardner, R.C. (1985). Social Psychology and Second Language Learning: The Role of Attitudes and Motivation. London: Arnold.

_________ (2003). "Attitudes Motivation, and Second Language Learning." A meta- Analysis of Studies. V.53.pp.167-210

Gardner, R.C. and Macintyre, P. (1993). "Special Feature on Affective Variables in Second Language Learning" The International Abstracting Journal For Language Teachers and Applied Linguists. London: Ontario University.

Gardner, R.C. and W.E. Lambert (1972). Attitudes and motivation in second language learning. Rowley Mass: New Burn House Publisher.

Good, T.L. and J.E. Brophy (1994). Looking in Classrooms (6th ed.).New York: HarperCollins.

Habtamu Kebu (1999). "The Relalationship between Selected Home and School factors with the Achievement Motivation and Performance among High School Students in Nathret" Unpublished M.A thesis in Educational Psychology: Addis Ababa University.

Harmer, J. (1991). The Proactive of English Language Teaching. London: Longman.

——— (2001). The Practice of English Language Teaching. Edinburgh Gate: Pearson in Education Ltd.

Haris, R. (1991). "Some Ideas for Motivating Students" TESL Journal. Vol. III V No.2 November 2002. Http://www Virtual selt.com.

Haywood, H.C.(1971) "Individual Difference in Motivational Orientation: A trait Approach" in Day, H.I Berlin D.E. Intrinsic Motivation: A New Direction in Education. Toronto Holt Rinehart and Winston of Canada. pp 75-85.

Hedge, T. (2000). Teaching and Learning in the Language Classroom. Oxford: Oxford University Press.

Hutchinson, T.(1988). "Making Materials work in ESP Classroom", in Brumfit (ed) ESP in classroom: Practiced and Evaluation ELT Document: P. 128.

Janet, S.(1997)."Motivating Learners at South Korea" English Teaching Forum, Vol.35 No,1:10.

Keller,J.M.(1983). "Motivational Design of Instruction" in C.M Reigetruth (ed.) Instructional Design Theories and Models: An Overview of their Current Status. Hills doe, NJ. Lawrence Erlbaum, PP 383-434.

Kost,S. (2006). "Motivation and Foreign Language Teaching Strategies for Motivation" http://itesu org. Articles /Suslu-Teacher Motivational. Htmi

Little wood, W.(1981). Communicative Language Teaching, Cambridge: Cambridge University Press.

Mulugeta, Teka. (1997). "Motivation in Listening Classes of Colege English at Addis Ababa University." (Unpublished M.A. Thesis). Addis Ababa University.

Noels, K. A et al.(2003). "Why are you Learning a Second Language? Motivational Orientations and self-Determination Theory" Language Learning. V. 53, pp.33-61.

Nunan, D.(1989).Designing Tasks for the Communicative Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Oxford, R.L. and Young, D.J.(1993). Language Learning Strategies what every Teacher Should Know. Cambridge: Cambridge University Press .

Parrott, M.(1993) Tasks for Language Teachers: A Resource Book for Training and Development. Cambridge: Cambridge University Press.

Peety, G.(2004).Teaching Today. (3rd ed). London: Nelson Thames Ltd.

Pintrich, R. and Schunk, H. (2002). Motivation in Education Theory, Research, and Applications. New York: Mirill Prentice Hall.

Raymond, W.(1986). "Enhancing Adult Motivation to Learn" In Dornyei, (2001). Motivational Strategies in the Language Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Rogers, C.(1991). On Becoming a Person. Boston: Houghton Mifflin.

Rosenshine, B,& Stevens, R.(1986). "Teaching Functions" in M.C. Wittrock (Ed) Handbook of Research on Teaching(3rd ed.). PP 376-39). New York: Macmillan.

Rosser, R.A and G.C. Nicholson (1984).Educational Psychology. Principles in Practice. Boston: Little Brown Company.

Scheldeker, D. and F. William (1999).The Best Bringing out in Students: How Legendry Teachers Motivate Kids. Thousand, CA: Corwin Press.

Seblewangl Yonas (2007) "An Assessment of Teachers, Motivational Strategies in ELT Classroom: Two Government Universities and Two Colleges in Oromia Region in Focus." Unpublished M.A. thesis in teaching English as Foreign language: Addis Ababa University.

Stern, H.H.(1983).Fundamental Concepts of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press,

Tewodros Zeleke, (2005). "The Effect of Plasma English Lesson on Students, Motivation in Leering English ia Case of two schools preparatory class students in Illubabor Unpublished M.A Thesis. In Teaching Engl;ish as Foreign Language: Addis Ababa University Press.

Ur, P. (1996). A course in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University.

Ushioda, E(1997). "The Role of motivational Thinking in Autonomous Language Learning". In D. Little, and BL Voss (Eds.) language Centers Planning for the New Millennium. Plymouth: University of Plymouth

Vanlier, E. (1988). The Classroom and the Language Learner. London: Longman Group UK Limited.

William,M. and Burden, B.(1997). Psychology for Language Teachers: A Social Constructivist Approach. Cambridge: Cambridge University Press.

Wittrack, M.C.(1986). "Students thought Processors" In M.C Wittrock (Ed.). Handbook of research on teaching(3rd ed). pP,297-314). New York: Macmillan.

Wright, T.(1987) Roles of Teachers and Learners. Oxford: Oxford University Press.

Young, D.J. (ed)(1999). Affective in Foreign Language and Second language learning. Boston: McGraw-Hill.

# አባሪዎች

# አባሪ ሀ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## በድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል

### ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ መቆጣጠሪያ ቅጽ (Check List)

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የተነሳሶት ስልት አተገባበር በክፍል ምልከታው ለመከታተል የተዘጋጀ መረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ (Check List)

የክፍል ምልከታው አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎችን ለማነሳሳት ተግባራዊ የሚያደርጓቸውን ስልቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተገኝቶ መመልከትና መረጃ መሰብሰብ ብቻ ነው።

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1. የትምርህት ቤት ስም____________________
2. የክፍል ምልከታው የተደረገበት ክፍል እና ምድብ (Section) ________________
   ክፍለ ጊዜ ________________
   ቀን ________________
   ሰዓት ________________
   የመምህሩ መለያ ኮድ __________

መመሪያ፡- ከዚህ በታች አራት የክፍል መልከታ መከታተያ "ሊስት"ቀርበዋል። በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተስማሚ ነው ለሚሉት አማራጭ መልስ የ «√» ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።

ክፍል ሁለት

| ተ.ቁ. | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ እና አደረጃጀት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | የመማሪያ ክፍሉ ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በቂ ስፋት አለው? | | |
| 2. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙት መቀመጫዎች ለተማሪዎች በቂ ናቸው? | | |
| 3. | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህና የተጠበቀ ነው? | | |
| 4. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ንፁህ አየር በመስኮት ይገባል? | | |
| 5. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ሰሌዳው ለሁሉም ተማሪዎች በሚታይ ቦታ ላይ ተቀምጧል? | | |

ክፍል ሶስት

የመምህር-ተማሪ ግንኙነት የሚመለከት

| ተ.ቁ. | የመምህር-ተማሪ ግንኙነት የሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በሰዓቱ ወደመማሪያ ክፍሉ ገብተዋል? | | |
| 2. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ የደንብ ልብሳቸውን ለብሰዋል? | | |
| 3. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ለተማሪዎቻቸው ትህትና ያሳያሉ? | | |
| 4. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ለተማሪዎቻቸው ፈገግታ ያሳያሉ? | | |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ የቁጡነት ባህሪ ይታይባቸዋል? | | |
| 6. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸውን ይከታተላሉ? | | |
| 7. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩን/ሯ በትምህርቱ ጣልቃ አዝናኝ ቀልዶችን ያቀርባሉ? | | |
| 8. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎቻቸው ጥያቄዎችን ሲጠይቋቸው ለመመለስ ፍቃደኛ ናቸው? | | |
| 9. | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ የማበረታቻ ቃላትን ይጠቀማሉ? | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎቻቸው ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ የምስጋና ቃላትን ይጠቀማሉ? | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች የተሳሳተ መልስ ሲመልሱ የነቀፌታ ቃላት ይጠቀማሉ? | | |
| 12 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ ጥያቄ ጠይቀው ከተማሪዎቻቸው መልስ ሲያጡ የነቀፌታ ቃላት ይጠቀማሉ? | | |

## ክፍል አራት

### የመምህሩን/ሯን የተነሳሶት ስልቶችን አተገባበር የሚመለከት

| ተ.ቁ. | የመምህሩን/ሯን የተነሳሶት ስልቶችን አተገባበር የሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በቡድን እንዲደራጁ አድርገዋል | | |
| 2. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በጥንድ እንዲደራጁ አድርገዋል | | |
| 3. | በቡድን ስራ ወቅት የቡድን መሪ ነበር | | |
| 4. | በቡድን ስራ ውስጥ በአብዛኛው የሚሳተፉት ተማሪዎች ጥቂቶች ብቻ ነበሩ | | |
| 5. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ የውይይት መንፈስ እንዲኖር አድርገዋል | | |
| 6. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ለተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ እንዲኖር አድረገዋል | | |
| 7. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ከመማሪያ መፅሀፉ ሌላ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ ተጠቅመዋል | | |
| 8. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ መቅረፅ ድምጽ ተጠቅመው አስተምረዋል | | |
| 9. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ሌሎች ጽሁፎችን በክፍል ውስጥ በመረጃነት ተጠቅመዋል | | |
| 10. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲፅፉ አድርገዋል | | |
| 11. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲሳተፉ እድል ሰጥተዋል | | |
| 12. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ የክፍሉን ስነ-ስርዓት እንደአስፈላጊነቱ ተቆጣጥረዋል | | |
| 13. | የአማርኛ መምህሩ/ሯ መምህር -መር ስልትን ተጠቅመው አስተምረዋል | | |
| 14. | የአማርኛ መምህሩ/ሷ ተማሪ ተኮር ዘዴ ተጠቅመው አስተምረዋል? | | |

ክፍል አምስት

የተማሪዎችን ተነሳሽነት በሚመለከት

| ቁ. | የተማሪዎችን ተነሳሽነት በሚመለከት | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | ተማሪዎች በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ በሰዓቱ ተገኝተዋል? | | |
| 2. | ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ሲያስተምሩ በፀጥታ ያዳምጣሉ? | | |
| 3. | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ወቅት እርስ እርስ በሹክሹክታ ይነጋገራሉ? | | |
| 4. | ተማሪዎች መምህራቸው ሲያስተምሩ የግል ስራቸውን የሚሰሩ አሉ? | | |
| 5. | መምህሩ/ሯ ሲያስተምሩ ማስታወሻ የሚይዙ ብዙ ተማሪዎች አሉ? | | |
| 6. | በፍቃደኝነት እጃቸውን በማውጣት መልስ የሚመልሱ ተማሪዎች አሉ? | | |
| 7. | በፍቃደኝነት የሚመልሱ ተማሪዎች ጥቂት ናቸው? | | |
| 8. | ጥያቄ የሚጠይቁ ተማሪዎች አሉ? | | |
| 9. | ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ፍራት ይታይባቸዋል? | | |
| 10. | ተማሪዎች ጥያቄዎችን በሚመልሱበት ወቅት ስህተት ሲፈጽሙ የመደንገጥ ስሜት ይታይባቸዋል? | | |
| 11. | ጥያቄ ሲጠይቁ የመረጋጋት ስሜት የሚታይባቸው አሉ? | | |
| 12. | ተማሪዎች በቡድን ለመሳተፍ ፍቃደኝነት ይታይባቸዋል? | | |
| 13. | የክፍል ጓደኞቻቸው መልስ ሲመልሱ በጥንቃቄ ይከታተላሉ? | | |
| 14. | ከክፍል ጓደኞቻቸው የተሳሳተ መልስ ሲሰነዘር ይስቃሉ? | | |
| 15. | በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ሳይፈሩ ሲወያዩ ታይተዋል? | | |
| 16. | የቤት ስራቸውን ሰርተው የመጡት ሁሉም ተማሪዎች ናቸው? | | |
| 17. | የቤት ስራቸውን ሰርተው የመጡት ተማሪዎች ጥቂቶች ናቸው? | | |

## ክፍል ስድስት

## አስተያየት እና ሐሳብ መስጠት

1. በመቆጣጠሪያ ቅጹ ላይ ያልሰፈሩ፣ ነገር ግን በክፍሉ ውስጥ የተመለከቷቸው/ያዳመጧቸው ነገሮች ካሉ በጽሁፍ ያስፍሩ ____________________

2. በመቆጣጠሪያ ቅጹ ላይ ሰፍረው አዎ ወይመ አይደለም ለማለት አሻሚ የሚሆኑ ሃሳቦች ካሉ በጽሑፍ ያስፍሩ:: ____________________

3. ስለ ክፍለ ምልከታው አጠቃላይ የሆነ የግል አስተያየቶችዎን በጽሑፍ ያሥፍሩ ____________________

# አባሪ ለ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## በድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል

### *ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ*

የፁሁፍ መጠይቁ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን የተነሳሶት /የማነቃቂያ/ ስልት አተገባበር ለማወቅ መረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ውድ ተማሪ ይህንን የፅሑፍ መጠይቅ ስትሞላ/ስታሞይ ትክክለኛውና እውነተኛ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር ለያንዳንዱ ጥያቄ በተሰጠው ሳጥን ላይ መልስህን/መልስሽን በማክበብ እንድታመለክት/እንድታመለከቺ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ተማሪ ለምታደርግልኝ/ለምታደርጊልኝ ቀና ትብብር ከወዲሁ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡ በፅሁፍ መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም

ክፍል አንድ ፡ ግለሰባዊ መረጃ

ሀ. ፆታ ________________

ለ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ________________

ሐ. እድሜ ________________

መ. የትምህርት ቤትህ/ሽ ስም ________________

ክፍል ሁለት፡ የተማሪዎችን የግል ስሜት ለመረዳት የቀረቡ ጥያቄዎች

| | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወስን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ምንም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ፍላጐት አለኝ | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይቀለኛል | | | | | |
| የአማርኛ መምህሩ/ሯ ሲያስተምሩ ይገባኛል | | | | | |
| ጥያቄ ለመጠየቅ አልፈራም | | | | | |
| በራስ መተማመን አለኝ | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋውን ለመናገር አልጨነቅም | | | | | |
| ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ በኋላ እርካታን አገኛለሁ | | | | | |

ክፍል ሶስት፡ የመምህራንን የክፍል ውስጥ ተግባራትና መማሪያ መጻህፍት በሚመለከት የቀረቡ የፅሁፍ መጠይቆች፤

| | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ምንም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በቡድን ስራ እንድሳተፍ ያደርጉኛል | | | | | |
| የአማርኛ መምህሬ በጥንድ ሥራ እድሳተፍ ያደርጉኛል | | | | | |
| አማርኛ ቋንቋ መምህሬ በግሌ እንድሳተፍ ያበረታቱኛል | | | | | |
| የቡድን አባሎቹ የቡድን መሪ ያደርጉኛል | | | | | |
| የቡድን አባሎቹ የቡድን ፀሐፊ ያደርጉኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ አዝናኝ ቀልዶችን በመጠቀም ትምህርቱን አስደሳች ያደርጉልኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በስሜ ጠርተው መልስ እንድመልስ ያደርጉኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በፈገግታ ጥያቄዎቼን ይመልሱልኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሪ የያንዳንዱን የትምህርት ክንውን ዓላማ ያሳውቁኛል | | | | | |
| የአማርኛ የቋንቋ መምህሬ እንዳስፈላጊነቱ መቅረፀ- ድምፅ /ቴኘ ተጠቅመው ያስተምራሉ | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደአስፈላጊነቱ ከመማሪያ መፅሐፉ ውጪ የሆኑ በፅሑፍ የቀረቡ መረጃዎችን ይጠቀማሉ | | | | | |
| በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት የሚቀርቡት ይዘቶች በሕይወት ልምዴ ከማውቃቸው ጋር ዝምድና አላቸው | | | | | |
| በአማርኛ መማሪያ መፅሐፌ ላይ ያሉት ምንባቦች ያስደስቱኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የክፍሉን ሁኔታ እንዳስፈላጊነቱ ይቆጣጠራሉ | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የተሳሳተ መልስ ስሰጥ በትህትና እርማት ይሰጡኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ትክክለኛ መልስ ስሰጥ ያስጨበጭቡልኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በሚሰጡ ሙከራዎች ጥሩ ውጤት ሳመጣ እንዳስፈላጊነቱ ይሸልሙኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ እንድሳተፍ ከክፍል ጓደኞቼ እኩል እድል ይሰጡኛል | | | | | |
| የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የራሴን ፈጠራ እንድጠቀም ያበረታቱኛል | | | | | |

ክፍል አራት ፡- የክፍል ጓደኞችን፣ ወላጆች እና የአካባቢ ማህበረሰብን በሚመለከት የቀረቡ መጠይቆች

| | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ምንም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| የክፍል ጓደኞቼ ጥያቄዎችን እንድመልስ ያበረታቱኛል | | | | | |
| የክፍል ጓደኞቼ በቋንቋ ትምህርቱ ወቅት በምፈጥረው ስህተት አይስቁብኝም | | | | | |
| ወላጆቼ ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | | | | | |
| ወላጆቼ አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን እንዳጠና ያበረታቱኛል | | | | | |
| በአካባቢዬ ያሉ ሰዎች ስለ ቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ አመለካከት አላቸው | | | | | |

ክፍል አምስት፡ የተማሪዎችን አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች

ውድ ተማሪ ቀጥለው ለቀረቡልህ/ሽ ጥያቄዎች አዎ ወይም አይደለም የሚል መልስ በመስጠት በተተወት ክፍት ቦታዎች ላይ ምክንያቶቻችሁን ፃፉ/ፌ

1. የአማርኛን ቋንቋ የምማረው የመማር ፍላጎት ስላለኝ ነው፡፡

አዎ ☐ አይደለም ☐

ምክንያት ______________________________

______________________________

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ /ሽ ትምህርቱን የሚያስተምሩበት ስልት ይስማማሃል/ሻል

አዎ ☐ አይደለም ☐

ምክንያት ___________________________________________

___________________________________________

3. ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱና ስለ መምህሩ የማስተማር ስልት የምትሰጠው/ጪው አስተያየት አለህ/ሽ

አዎ ☐ አይደለም ☐

ምክንያት ___________________________________________

___________________________________________

# አባሪ ሐ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## በድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል

### ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን
### የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

**የቃለ መጠይቁ አላማ**

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-በክፍል ውስጥ ቢያስተምሩ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሶት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል እንደሆነ መረጃ ለማሰባሰብ ነው፡፡

ውድ መምህር፡- የቃለ መጠይቁ ከዚህ ሌላ የተለየ አላማ እንደሌለው በመገንዘብ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ለሚደረግልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡ አጥኝዋ

## ክፍል አንድ

ግላዊ መረጃ

1.1. ፆታ ______________

1.2. እድሜ ________________________

1.3. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት __________

1.4. የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት፣ ኡብይ ______________ ንዑስ __________

1.5. የትምህርት ደረጃ ____________________________

1.6. የአገልግሎት ዘመን _________________________

## ክፍል ሁለት

### የመምህሩን ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች

2.1. በሳምንት ምን ያህል ክፍለ ጊዜ ያስተምራሉ?

2.2. ከአማርኛ ቋንቋ ትምርህት ሌላ በተጨማሪነት የሚስተምሩት የትምህርት አይነት አለ? ____________ ምን? ____________

2.3. በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት? ____________ምን ____________

____________

____________

2.4. የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ? ____________ካለ ምን አይነት? ____________ ለስንት ጊዜ? ____________ ከሌለ ለምን ይመስልዎታል?

2.5. የአማርኛን ቋንቋ ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው? ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ።

2.6 በሞያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ ____________

## ክፍል ሶስት

### የክፍል ውስጥ ክንውንን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

3.1. በመማር ማስትማሩ ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው? ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ

3.2. የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን አይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ?

3.3. በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ? በቡንድን፣ በጥንድ፣ በነጠላ

3.4. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ /የመምህር-ተማሪ ተራክቦ/ ንቁ እና ሳቢ እንዲሆን ምን አይነት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ?

3.5. በመማር-ማስተማር ሂደት ከተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ሌላ ምን አይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ?

3.6. በመማር-ማስተማሩ ሂደት የክፍል ተማሪዎችዎ በራስ መተማመን እና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን አይነት ስልት ይጠቀማሉ?

3.7. በመማር-ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ስራ ይከታተላሉ? ለምን?

3.8. የክፍል ተማሪዎችዎ ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? አዎ ካሉ ምን ምን ቃላትን ይጠቀማሉ፤ የለም ካሉ ለምን?

3.9. የክፍል ተማሪዎችዎ መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን አይነት ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም ከስህተቶቻቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ?

3.10. የክፍል ተማሪዎችዎ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምን ምን ናቸው?

3.11. ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎችዎ ሽልመው ያውቃሉ? ምን?

3.12. በመማር-ማስተማሩ ሂደት ጥፋት የፈፀሙ ተማሪዎች አጋጥሞዎት ያውቃል? ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን ነበር? ለምን?

## ክፍል አራት

### አስተያየት

4.1. ስለ ክፍል ተማሪዎችዎ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡፡

4.2. ስለ ቋንቋ ትምርህቱ አቀረራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ፡፡

4.3. ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁሟቸው አስተያየቶች ካሉ?

# አባሪ መ

## ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከቀረበ ቃለ መጠየቅ የተገኘ ምላሽ ናሙና

## መምህር-ሀ

### ክፍል አንድ

### ግላዊ መረጃ

1.1 ጾታ ወ

1.2 እድሜ 35

1.3 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት

አዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመንግስት

1.4 የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት

አብይ አማርኛ ንዑስ እንግሊዝኛ

1.5 የትምህርት ደረጃ

B.A ዲግሪ

1.6 የአገልግሎት ዘመን

አስራሁለት

### ክፍል ሁለት

### የመምህሩን ሁኔታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች

2.1 በሳምንት ምን ያህል ክፍለ ጊዜያት ያስተምራሉ

24

2.2 ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላ በተጨማሪነት የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት አለ?

የለም

2.3 በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ ተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት?

የለም

2.4 የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ?

አላውቅም

2.5 የአማርኛን ቋንቋ ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው?

ከፍተኛ

2.6 በሙያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ?

አላገኝም

## ክፍል ሶስት

### የመምህራንን የተነሳሶት ስልት በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች

3.1 በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው?

ዝቅተኛ

3.2 የክፍል ተማሪዎች በ ቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን አይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ?

ተማሪዎችን በቡድን እያደራጁ እንዲወያዩ ማድረግ።

3.3 በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ?

በአብዛኛው በነጠላ እንዲሳተፉ ሳደርግ አልፎ አልፎ ግን በጥንድ በማደራጀት እንዲሳተፉ አደረጋቸዋለሁ።

3.4 የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ/የመምህር-ተማሪ:ተራክቦን/ ንቁና ሳቢ እንዲሆን ምን አይነትስልቶችን  ተግባራዊ ያደርጋሉ?

ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እድል እሰጣለሁ ምሳሌዎችን በማቅረብ በቀላል መንገድ እንዲረዱ አደርጋለሁ ።

3.5 በመማር-ማስተመሩ ሂደት ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ሌላ ምን አይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ?

ለሰዋስው ትምህርት የሚያግዙመጽሀፍት ስለ ድርሰትና ስለ አንቀጽማብራሪያ የሚሰጡ መጽሀፍትን እጠቀማለሁ።

3.6 በመማር-ማስተማሩ ሂደት የክፍል ተማሪዎች በራስ መተማመንእና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን አይነት ስልት ይጠቀማሉ?

ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ «አይሂችኑ፣በርቱ፣ ትክክል ናችሁ» በማለት በማበረታታት ድፍረት እንዲያገኙ አደርጋለሁ።

3.7 በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ስራ ይከታተላሉ ? አዎ። ምክንያቱም የክፍሉ ጸጥታ እንዳይታወክ ተማሪዎች ስራቸውን በጥንቃቄ እንዲሰሩ ለማድረግ እከታተላለሁ

3.8 የክፍል ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ አዎ ካሉ ምንምን አይነት ቃላትን ይጠቀማሉ የለም ካሉ ለምን?

አዎ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ« በጣም ጥሩ፣ ጥሩ ነው፣ ጎበዝ፣ በዚሁ ቀጥል/ይ» በማለት አበረታታለሁ ፡፡

8.9 የክፍል ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን ብለው በመናገር ከስህተቶቻቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ?

«መሳሳት ምንም አይደለም» በማለት ስህተታቸውን በመግለጽ እንዲታረሙ አደርጋለሁ።

3.10 የክፍል ተማሪዎችዎ ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምን ምን ናቸው?

« ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ፣ አመሰግናለሁ» የሚል ቃላትን እጠቀማለሁ

3.11 ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ሽልመው ያውቃሉ?

ምንም ሽልሜ አላውቅም።

3.12 በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥፋት የፈጸሙ ተማሪዎች አጋጥሞዎት ያውቃሉ ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን አይነት ነበር?

አዎ ተማሪዎቹ ከጥፋታቸው እንዲታረሙና ሌሎች ተማሪዎችን እንዳይረብሹ ከክፍል አስወጥቼአቸው ከጥፋት እንዲመለሱ ተገሳጽ ሰጥቻቸዋለሁ።

## ክፍል አራት

## አስተያየት

4.1 ስለ ክፍል ተማሪዎችዎ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለፁልኝ።

-የክፍል ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም አብዛኞቹ ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ለመመለስ ፈቃደኛ አይደሉም። የሚመልሱ ተማሪዎች ቢኖሩም እንኳን ቋንቋውን ለመናገር ቃላት ስለሚያጥራቸው መልሶችን ለመመለስ ሲቸገሩ ይታያሉ። አንዳንድ ጊዜ ቃላትን እየቀላቀሉ ሲናገሩ

የሚያደምጡ ተማሪዎች ስለሚንሾካሾኩባቸው በነጻነት ከመናገር ይቆጠባሉ። አንዳንዶች ተማሪዎች ደግሞ በትምህርት ወቅት በጥንቃቄ ከመከታተል የልቅ እርስ በርስ ሲያወሩና የግል ስራቸውን ሲሰሩ በማየቴ ለትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንደሆነ መገመት ችያለሁ።

4.2 ስለ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለጹልኝ።

-የቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎች በከባድ ቃላት የቀረበ ስለሆነ ተማሪዎቹ ለመረዳት ይቸገራሉ። ተማሪዎቹ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ትዛዛትና መልመጃዎች ቢኖሩም የመጽሐፉ ይዘት ስፋት ስላለው ሁሉንም መተግበር አይቻልም።

4.3 ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁማችው አስተያየቶች ካሉ፡

-የተማሪው መማሪያ መጻህፍ በቀላል ቋንቋ ቢዘጋጁ ተማሪዎቹ ሁሉንም ክሂሎች በነቃ ተሳትፎ እንዲተገብራቸው በመጽሀፍ የቀረቡ ይዘቶች መጠናቸው ቢቀንስ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት ያላቸው በመሆናቸው እንደአስፈላጊነቱ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን መፍጠር አልተቻለም። ስለዚህ ሌሎች የመማሪያ ክፍሎች ተገንብተው በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩት የተማሪዎች ቁጥር ወደ ሀምሳ ዝቅ ቢል ጥሩ ነው እላለሁ።

## ከመምህር-ሠ የተገኘ ምላሽ

### ክፍል አንድ

### ግላዊ መረጃ

1.1 ጾታ ወ

1.2 እድሜ 27

1.3 የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት፤

ሆሊ ኢንጅልስ የግል ትምህርት ቤት

1.4 የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት፤

አብይ አማርኛ ንዑስ እንግሊዝኛ

1.5 የትምህርት ደረጃ፤

B.A ዲግሪ

1.6 የአገልግሎት ዘመን፤

አራት

## ክፍል ሁለት

### የመምህሩን ሁኔታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች

2.1 በሳምንት ምን ያህል ጊዜያት ያስተምራሉ

ሀያ አራት

2.2 ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላ በተጨማሪነት የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት አለ?

የለም

2.3 በትምህርት ቤት ውስጥ ከማስተማር ስራ በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት አለዎት?

የለም

2.4 የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በተመለከተ የአጭር ጊዜ ስልጠና አግኝተው ያውቃሉ?

አላውቅም

2.5 የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለዎት ፍላጎት ምን ያህል ነው?

ከፍተኛ

2.6 በሙያዎ በቂ ክፍያ ያገኛሉ? በመጠኑ አገኛለሁ በማለት ማብራሪያቸውን እንደሚከተለው ሠጥተዋል። ወርሀዊ ክፍያዬ ከሌሎች አቻ ከሆኑ ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ እንደሆነ አውቃለሁ ከደመሞዜ በተጨማሪ በአመቱ መጨረሻ ተጨማሪ ክፍያ አገኛለሁ። እንዲሁም ጠዋት ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ የትራንስፖርት አገልግሎት ከትምህርት ቤቱ አገኛለሁ።

## ክፍል ሦስት

### የክፍል ውስጥ ክንውንን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

3.1 በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው?

መካከለኛ

3.2 የክፍል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የተነሳሱ እንዲሆኑ ምን አይነት የማስተማሪያ ስልቶችን መተግበር ጠቃቢ ነው ብለውያምናሉ?

ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከፍ እንዲል ከዚህ በፊት ዘጠነኛ ክፍልን ተምረው ባለፉ ተማሪዎች የተሰሩ አንድአንድ መልመጃወችን በምሳሌነት አሳያቸዋለሁ ትምህርቱን ከመጀመሬ በፊት አዝናኝ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወደትምህርቱ በአስደሳች ሁኔታ እንዲገቡ አደርጋለሁ በክፍል ውስጥ የውድድር መንፈስ እንዲኖር ለየቡድኑ ነጥብ በመያዝ እንዲከራከሩ አደርጋለሁ።

3.3 በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት በየትኛው የማስተማሪያ መንገድ ተማሪዎችን ያደራጃሉ? በቡድን እና በጥንድ

3.4 የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ንቁ እና ሳቢ እንዲሆን ምን አይነት ስልቶችን ተግባረዊ ያደርጋሉ?

አዝናኝ ቀልዶችን በመጠቀም ከተማሪዎች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር አስደሳች እንዲሆን አደርጋለሁ።

3.5 በመማር ማስተማር ሂደት ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ሌላ ምን አይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ?

እንደ ቅኔ ምሳሌያዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር ያሉትን በማሰባሰብ ከማስታዎሻ ጽሁፍ ላይ አስተምራለሁ። የሰዋስው መጽሀፍትና የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍትን የሰዋስውና የድርሰት መልመጃዎችን ለማስተማሪያነት እጠቀማለሁ። አልፎ አልፎ ከጋዜጣና ከመጽሄት ላይ የሚገኙ ምንባቦችንና ስዕሎችን በመርጃ መሳሪያነት እጠቀማለሁ።

3.6 በመማር-ማስተማሩ ሂደት የክፍል ተማሪዎቸ በራስ መተማመን እና ድፍረት እንዲኖራቸው ምን አይነት ስልት ይጠቀማሉ?

ተማሪዎች ከጋደኞቻቸው ጋር በመሆን ፊት ለፊት ወጥተው ጭውውት እንዲያደርጉ አደፋፍራለሁ ቃለ ምልልሶችን ከእኔ ጋር እንዲያደርጉ እጋብዛቸዋለሁ ለሚሰሩት ስራ አድናቆት እሰጣቸዋለሁ።

3.7 በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በማድረግ የተማሪዎችን ስራ ይከታተላሉ?

አዎ። ምክንያቱም ተማሪዎች የሚሠሩት የክፍል ስህተት ከሆነ እንዳርማቸውና ያጋጠማቸውን ችግር አጠገባቸው ሄጄ እንድፈታላቸው

እንዲሁም በትጋት እንዲሰሩ ለማድረግ እከታተላቸዋለሁ።

3.8 የክፍል ተማሪዎችዎ ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? «አዎ» ካሉ ምን ምን አይነት ቃላትን ይጠቀማሉ? የለም ካሉ ለምን?

አዎ። የምጠቀማአቸው ቃላት «በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፣ ለሁላችሁም የሚጠቅም ጥያቄ ነው፣ ጎበዝ ልጅ »በማለት አበረታታቸዋለሁ።

3.9 የክፍል ተማሪዎችዎ መልስ ሲመልሱ ከተሳሳቱ ምን ብለው በመናገር ከስህተቶቻቸው እንዲታረሙ ያደርጋሉ? «በጣም ጥሩ ሙከራ ነው፣ ሌላ ይሄንን መልስ የሚቃወም ካለ»በማለት የተማሪውን መልስ ቀየር በማድረግ «እንዲህ ለማለት ፈልገህ ነው» በማለት ወደ ትክክለኛው መልስ እንዲመጣና ስህተቱን እንዲያርም አደርጋለሁ።

3.10 የክፍል ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲመልሱ ለማበረታታት የሚያዘወትሯቸው የምስጋና ቃላት ምንምን ናቸው?

«በጣም ጥሩ ጎበዝ አንበሳ አግኝተኸኛል »በማለት አበረታታቸዋለሁ።

3.11 ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎችዎ ሸልመው ያውቃሉ?

ምንም ሽልሜ አላውቅም።

3.12 በመማር ማስተመሩ ሂደት ጥፋት የፈጸሙ ተማረዎች አጋጥሞዎት ያውቃሉ? ካጋጠመዎት የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ ምን አይነት ነበር ለምን?

እዎ። የወሰድኩት እርምጃ በቅድሚያ ተማሪው ጥፋቱን ሲፈጽ ሌላውን ተማሪ በማይረብሽ መልኩ በአይኔ ገርመም አድርጌው አልፋለሁ። ከዛ በኃላ ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ ጠርቼ ለምን ጥፋቱን እንዲፈጸመ በመጠየቅ ምክር እሰጠዋለሁ።

## ክፍል አራት

## አስተያት

4.1 ስለ ክፍል ተማሪዎችዎ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለጹልኝ።

የክፍል ተማሪዎቼ በቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ ተሳትፎ የሚያደርጉ ናቸው። አባዛኞቹ ጥያቄ ለመጠየቅና ለመመለስ በፈቃደኝነት ይሳተፋሉ ያልገባቸውን ጥያቄ ከመማሪያ ክፍል ውጭም ቢሆን ሲያገኙኝ ይጠይቁኛል ። በሌላ በኩል ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ጀምረው አብረው ትምህርት ቤት ውስጥ አንድ ላይ እየተማሩ እዚህ የደረሱ በመሆኖቸው መማሪያ ክፍል ውስጥ እርስ በእርሳቸው ሲረዳዱና ሲተጋገዙ ይታያሉ። ስህተት ቢሰሩም እርስ በእሰረሳቸው ይሳሳቃሉ። የሚማሩትን ትምህርት በማጥናት ጥሩ ውጤት ያመጣሉ።

4.2 ስለ ቋንቋ ትምህርቱ አቀራረብ የሚሰጡትን አስተያየት ካለ ይግለጹልኝ።

የቋንቋ ትምህርቱ ስፋት ያለው ሲሆን ሁሉንም መልመጃዎች በተረጋጋ መልኩ ለማስተማር ጊዜ ያንሳል። አንድ አንድ ተማሪዎች አረፍተነገር ስሩ ቃላት መስርቱ የሚሉ ተዕዛት ሲያጋጥሙአቸው ቀላል መስሎ ስለሚታያቸው ችላ ብለው ያልፉታል። አንዳንዶቹ ምንባቦች ስለማይስቡቸአው ሌላ ምንባብ እንዲነብብላአው ይጠይቃሉ። ስለዚህ ከተማሪዎች አካባቢ ጋር የሚስማሙ ምንባቦች ቢዘጋጁላቸው እና የትምህርት ይዘት መጠኑ አነስተኛ ሆኖ ቢቀርብላቸው ጥሩ ነው።

4.3 ለወደፊት ቢሻሻሉ ጥሩ ናቸው ብለው የሚጠቁማቸው አስተያየቶች ካሉ።

የመማሪያ መጽፍ ይዘት መጠኑ ቢቀንስ፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች አንድአንድ የሚከብዱ ቃላትና ሀረጋት ቀለል ባለ መልኩ ቢቀርቡላቸው ጥሩ ነው እላለሁ።

# ዲክላራስዮን

እኔ ከዚህ በታች በስም የተጠቀስኩት ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ምንጮች በሙሉ በትክክል የተጠቀሱ ስለመሆናቸው እንደሚከተለው በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ለወየሁ አየለ

ፊርማ: --------------

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ።

የማስረከቢያ ቀን፡- ----------------2000 ዓ.ም